# መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት

# ክፍል አንድ

## የመዳን ትምህርት

### ⇨ የወደቀው መልአክ (ሰይጣን) አፈጣጠርና አወዳደቅ

- ☞ **ሰይጣን፡-** የሂብሪው ቃል ሲሆን ትርጉሙም "አሰናካይ" ጠላት እንቅፋት የሚያኖር ማለት ነው፡፡
- ☞ **ዲያብሎስ፡-** የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙ ከሳሽ ማለት ነው፡፡

**ለምን ተፈጠረ?**

1. እግዚአብሔርን ለማመስገን ተፈጠረ **ሕዝ 28:13**
2. የእግዚአብሔርን ክብር ለመጋረድ የተቀባ (የተሾመ) ነበረ **ሕዝ 28:14**
3. ውበቱም የተፈፀመ መደምደምያ ነበር **ሕዝ 28:12**

**ለምን ወደቀ?**

1. በውበቱ ምክንያት ኮራ (ትዕቢት) **ሕዝ 28:17**
2. በልዑል እግዚአብሔር መመሰል (መሆን) ፈለገ **ኢሳ 14:12**

**የኃጢአቱ ውጤት**

1. ከነተከታዮቹ ወደምድር ተጣለ **ሕዝ 28:17**
2. ወደፊት ደግሞ ወደጨለማው ጉድጓድ ወደ እሳት ባህር ውስጥ ይጣላል **ኢሳ 14:15, ማቴ 25:41, 2ጴጥ 2:4**

### ✶ የሰው አፈጣጠርና - አወዳደቅ

- ሰው በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ ተፈጠረ **ዘፍ 1:26**
- እግዚአብሔር ከምድር አፈር አበጀው **ዘፍ 2:7**
- ሰው ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ **ዘፍ 2:7**
- አካባቢውን ሁሉ እንዲገዛ ተፈጠረ **ዘፍ 1:26**
- ገነትን ይጠብቃት ያበጃትም ዘንድ በዚያ አኖረው **ዘፍ 2:15**
- የሚመቸውን ረዳት ፈጠረለት **ዘፍ 2:18-25**
- ከዕውቀት ዛፍ እንዳይበላ አዘዘው **ዘፍ 2:16**

* **ውድቀት**
    * ሰይጣን/እባብ/ ሔቲቱን አታለላት **ዘፍ 3:1-7, 1ጢሞ 2:14**
    * ባልየው የሚስቱን ቃል በመስማት ተላለፈ **ዘፍ 3:6, 3:17**
    * **ምክንያት** - እንደእግዚአብሔር ለመሆን በመፈለግ **ዘፍ 3:5**
      - ከፈጣሪ ይልቅ የፍጥረትን ድምጽ ወይም ቃል በመስማት
      (ሴቲቱ የሰይጣንን፣ ወንዱ የሚስቱን ቃል አደመጡ)

* ዛፉ ለመብላት ያማረ → 1. የሥጋ ምኞት
* ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ → 2. የዓይን አምሮት
* ለጥበብም መልካም እንደሆነ አየች → 3. የኑሮ ትምክህት

**ዘፍ 3:6** **1ዮሐ 2:16 (የ1980 ትርጉም)**

✓ እነዚህ ሦስቱ የኃጢአት መግቢያ መንገዶች ናቸው:: ሰይጣን ሰውን ፈትኖ የሚጥለው በነዚህ 3 መንገዶች ተጠቅሞ ነው:: ጌታ ኢየሱስ የተፈተነበትን ታሪክ ከማቴዎስ 4:1-10 በማንበብ እነዚህን 3 ነጥቦች ለማገናኘት ሞክር::

* **የኃጢአት ውጤቶች በሰው ላይ**
    1. እራቁትነት /ጉስቁልና/ ነውር በሰው ላይ መጣ **ዘፍ 3:7**
    2. ፍርሃት /ሽሽት/ ተጀመረ **ዘፍ 3:8-10**
    3. እርግማን መጣ **ዘፍ 3:16-21**
    4. ከገነት ተባረሩ **ዘፍ 3:22-24**
    5. ሰው ሰውን መበደል ጀመረ **ዘፍ 4:1-8**
    6. የሰው የልቡ አሳብ ክፉ ሆነ **ዘፍ 6:5**

## ✸ ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ ሆነ

* ተወልዶ እስኪሞት ሕግን በመጠበቅ ጸንቶ የሚኖር ማንም ሰው የለም **ሮሜ 3:20** ስለዚህ ሰው ሁሉ ሕግን በመተላለፍ የተነሳ የተረገመ ሆነ **ገላ:310**
* ሰው ሕግን ሁሉ ቢጠብቅ ነገር ግን በአንዲቱ (ለምሳሌ አትመኝ) ቢስት በሁሉ ተጠያቂ በደለኛ ይሆናል:: **ያዕ 2:10**

ስለዚህ ሰው በዕድሜ ዘመኑ አንዴ ቢስት እንኳ መጽደቅ አይችልም ነበር:: ከዚህም የተነሳ በሰው ግምት ጻድቅ የሚባሉ እንኳ ሁሉን በሚያውቀው በአምላክ ፊት ኃጢአተኞች ናቸው:: **ሮሜ 3:23, ሮሜ 5:12, መክ 7:20**

- ሰው <u>በእግዚአብሔር ፊት ፃድቅ</u> ሊሆን አይችልም፡፡ **ኢዮ 4:17, 9:2, ሮሜ 3:20**
- አንድም ስንኳ ፃድቅ የለም፡፡ **መዝ(14):2, ሮሜ 3:11**
- ፃድቃን የሚባሉ እንኳ ኃጢአት ያደርጋሉ፡፡ **መክ 7:20**
- ጽድቃችን እንኳ በፊቱ በቂ አይደለም፡፡ **ኢሳ 64:6**
- ሕግን በመፈጸም <u>በእግዚአብሔር ፊት</u> መጽደቅ አይቻልም፡፡ **ሮሜ 3:20, ገላ 2:16,21, ኤፌ 2:8**
- በሰው ልጆች መካከል የጽድቅ ልዩነት የለም፡፡ **ሮሜ 3:22**
- ፀጋው በእምነት ያጸድቃል፡፡ **ሮሜ 3:22-25**

**<u>ማስታወሻ</u>** (በተጨማሪ "ሕግና ፀጋ" የሚለውን ትምህርት ተመልከት(ቺ))

## <u>አምላክ ሰውን ለማዳን ያዘጋጀው መፍትሔ</u>

- ማንም ሰው ራሱን ማዳን በምንም መንገድ አይችልምና እግዚአብሔር ራሱ ሰውን የሚያድንበት መፍትሔ አዘጋጀ፡፡
  - ልጁን መድኃኒት እንዲሆን ላከው **1ዮሐ 4:14**
  - አስቀድሞ እግዚአብሔር ልጁን ከመላኩ በፊት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለሚመጣው መድኃኒት በምሳሌ ያሳይ ነበር፡፡

**ለምሳሌ፡-** አዳም እርቃኑን ለመሸፈን ሲል በራሱ እጅ ቅጠል ሰፍቶ አገለደመ፡፡ እግዚአብሔር ግን የአዳምን ገመና ራሱ እግዚአብሔር ባዘጋጀው ቁርበት ሸፈነለት፡፡ (ይህም የአዳምን የኃጢአት ውጤት ለመሸፈን አንድ እንስሳ ሞቷል ማለት ነው፡፡ እርሱም የኢየሱስ ምሳሌ ነበር)፡፡ **ዘፍ 3:2**

  - ከሴቲቱ የሚወለደው የእባቡን ራስ እንደሚቀጠቅጥ አምላክ ትንቢት ተናገረ **ዘፍ 3:5**
  - ለእስራኤል ልጆች ለኃጢአት ስለሚሰዋው በግ በምሳሌ አስተማራቸው፡፡ **ዘሌ 4**

**ለምሳሌ፡-** በብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ውስጥ በጥላና ምሳሌ መልክ ጌታ ኢየሱስን በብዙ መቶዎች በሚቆጠር ሥፍራዎች /ጥቅሶች/ ውስጥ እናገኘዋለን፡፡ **በብሉይ የተገለጡ ነገሮት በሙሉ ጥላ** ሲሆኑ **አካሉ ግን የክርስቶስ** ነው፡፡ **ቈላ 2:16**

### የዘሌዋውያን ምዕራፍ 4 በግ ምሳሌነትና ትርጉሙ

- አንድ ሰው አንዲቱን ትዕዛዝ ቢተላለፍ ለኃጢአቱ መስዋዕት የሚሆን ነውር የሌለበት ወይፈን፣ በግ ወይም ፍየል ይዞ ይቀርባል፡፡ እጁንም በወይፈኑ ራስ ላይ ጭኖ ኃጢአቱን ለእግዚአብሔር በመናዘዝ ያሸክመዋል፡፡ ወይፈኑንም ያርደዋል፡፡ ካህኑም ደሙን ወስዶ በመገናኛው ድንኳን ፊት 7 ጊዜ ይረጨዋል፡፡

**በአዲስ ኪዳን የዚህ ምሳሌ ትርጉም**

- ነውር የሌለበት በግ ኢየሱስ ነው። **ዮሐ 1:24, ዕብ 7:26**
- ጌታ ኢየሱስ ራሱን ስለእኛ ኃጢአት አቀረበ። **ዕብ 7:27, 10:12**
- ኃጢአታችንን ሁሉ ተሸከመ **1ጴጥ 2:24, ኢሳ 53:6,12**
- የእግዚአብሔር በግ ለኃጢአታችን ታረደ (ሞተ) **1ቆሮ 5:7, ራዕ 5:9**

**የብሉይ ኪዳን የእንስሳት መስዋዕት ለምን ቀረ?**

- ጌታ ኢየሱስ እስኪሞት ድረስ በምሳሌነት የተሰጠ ነበረና **ዕብ 9:10**
- የፍየሎችና የበጐች ደም ኃጢአትን ሊያስወግድ አይችልምና። **ዕብ 10:4, 11, 9:12**
- ሥርዓቱ የተሰጠው ለዓለም ሕዝብ ሳይሆን ለእሥራኤል ብቻ ነበረ **ዘሌ 4:2**

## መፍትሔ ከአምላካችን ዘንድ

ሰው በማናቸውም ሁኔታ፣ በመልካም ሥራ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ፍፁም ሊሆን ወይም ሊጸድቅ አልቻለምና እግዚአብሔር ራሱ ዓለም ሳይፈጠር በፊት ለሚጠፋው የሰው ልጅ ያቀደውን የመዳን መንገድ ገለጠው። ይህም መንገድ "**ፀጋ**" ይባላል። ፀጋ ማለት "**ለማይገባው ማንነት እንዲሁ የሚሰጥ**" ማለት ነው። ይህም የሰውየውን ጥሩነት በማየት ሳይሆን እንዲሁ ከሰጪው ደግነት የተነሣ የሚሰጥ ነፃ ስጦታ ነው። ከሰውየውም የሚጠበቀው **በቸርነት** የተሰጠውን **ፀጋ** በእምነት መቀበል ብቻ ነው።

## የፀጋው አሠራር

- እግዚአብሔር ቃል ሥጋ ሆነ **ዮሐ 1:14**
- እግዚአብሔር ቃሉን (ልጁን) የዓለም መድኃኒት ሊሆን ላከው **1ዮሐ 4:14**
- የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ **ማቴ 16:16** ሕግን በሙሉ ፈጸመ። ከቶም ኃጢአትን አላደረገም **ዕብ 4:15, ዕብ 2:14-18** እግዚአብሔር ልጁን በእኛ ምትክ እንዲሞት፣ እኛ ደግሞ በእርሱ ጽድቅ እንዲሁ እንድንጸድቅ አደረገ።

| *የዓለም ሕዝብ* | *ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ* |
|---|---|
| - ሁሉም ኃጢአትን አድርገዋል<br>- ሕግን በመጠበቅ ሊጸድቁ ስለማይችሉ ርጉም ሆኑ። | - የሰውን ሥጋ ለብሶም ኃጢአት አያውቀውም<br>- ሕግን ሁሉ ፈጽሟል |

## *እርሱ ስለእኛ ፈንታ*

***ኃጢአት ሆነ 2ቆሮ 5:21***

***ርግማን ሆነ ገላ 3:13***

በእኛ ላይ ያለውን ኃጢአታችንን በመሸከም ኃጢአት የሚያመጣውንም ርግማን እና ሞት ለራሱ በመውሰድ እኛ ነፃ እንድንሆን አደረገ:: ኢየሱስ የዓለምን ኃጢአት ሁሉ ተሸክሟል:: ነገር ግን ሰው ለመዳን ከፈለገ በኢየሱስ ሥራ ብቻ እንደሚጸድቅ ማመን አለበት::

አንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ሲያምን ምን ይሆናል?

በኢየሱስ ያመነ ሰው:-

1. የዘለዓለም ሕይወት አለው /አይጠፋም/ **ዮሐ 3:16,18**
2. ከሞት ወደ ሕይወት ተሻግሯል ወደፍርድ አይመጣም **ዮሐ 5:24**
3. ኩነኔ የለበትም **ሮሜ 8:1**
4. በሕግ ጉዳይ አይጠየቅም **ሮሜ 6:14**
5. ከኃጢአቱ ታጥቧል፣ ጸድቋል፣ ተቀድሷል **1ቆሮ 6:11**
6. ዳግመኛ ተወልዷል **ዮሐ 1:12**
7. የእግዚአብሔር ልጅ ሆኗል **ሮሜ 8:14-17, ገላ 4:6**
8. አዲስ ፍጥረት ሆኗል **2ቆሮ 5:17**
9. ኃጢአቱ ተሰርዮለታል **1ዮሐ 2:12, ሮሜ 4:5-8**
10. የዘለዓለም ፍፁም ሆኗል **ዕብ 10:14**
11. ያለምንም ሥራ በእምነት ብቻ ጸድቋል **ኤፌ 2:8**
12. የፀጋ ስጦታ ተሰጥቶታል **1ቆሮ 12:4-11, ቁ 27-28**
13. በመንፈስ ቅዱስ ታትሟል **ኤፌ 1:13**
14. መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ገብቶበታል **ዮሐ 7:38, 14:15-17**
15. በአብ ቀኝ ተቀምጧል **ኤፌ 2:4-8 ወዘተ...**

## ለመዳን

***ጌታ ኢየሱስን ብቻ ለምን መረጥን?***

**ምክንያቱም:-**

- እርሱ ብቻ አዳኝ ስለሆነ **ኢሳ 43:11, ሐዋ 4:12**
- ለኃጢአታችን የሞተው እርሱ ብቻ ስለሆነ **ዮሐ 3:15, 1ቆሮ 15:3**
- ከኃጢአት የሚያነፃው የእርሱ ደም ብቻ ስለሆነ **1ዮሐ 1:17**
- በእርሱ ብቻ ወደ አብ ስለሚደረስ **ዮሐ 14:5-6, ኤፌ 2:18**
- ሕይወት እርሱ ብቻ ስለሆነ **ዮሐ 14:6**

# ***ክፍል ሁለት***

## ***የውኃ ጥምቀት***

**ጥምቀት**፡- በግሪክ "ባኘቲዞ" ሲባል የቃሉ ትርጉም "ማስጠም" ማለት ነው፡፡

"**Baptism**":- Immersion - አንድ ነገር ሙሉ በሙሉ በውኃ ሲሸፈን (ሲሰወር) ማለት ነው፡፡

- ቤተክርስቲያን አህዛብን ሁሉ እያስተማረች እንድታጠምቅ በጌታ ታዛለች፡፡ **ማቴ 28፡19, ማር 16፡15**
- የዘለዓለም ሕይወት ፈጽሞ በጥምቀት አይገኝም፡፡ ሰው ለመጠመቅ የግድ በቅድሚያ በኢየሱስ በማመን መዳን ይኖርበታል፡፡

### ***በውኃ የመቀበሩ (የመጠመቁ) ትርጉም ምንድ ነው?***

***ሀ.*** ከኢየሱስ ጋር መቀበር ነው፡፡ **ሮሜ 6፡4, ቆላ 2፡12**

አማኙ ከጌታ ኢየሱስ ጋር አብሮ ለመቀበር እንኳ የተስማማ (የተባበረ) መሆኑን ይገልጽበታል፡፡ ይህም ከውኃው በሚጠልቅበት ቅጽበት ይገለጣል፡፡

**ለ.** ከኢየሱስ ትንሣኤ ጋር መተባበሩን ያሳያል፡፡ **ሮሜ 6፡4-5**

ይህም ከውኃው በሚወጣበት ቅጽበት ይገለፃል፡፡

ጌታ ኢየሱስ በመቃብር ውስጥ

አማኙ በጥምቀት አብሮ ሲቀበር

**ሐ.** ከዚያ በኋላ በአዲስ ሕይወት መመላለስ ይገባል፡፡ **ሮሜ 6፡8,4,11**

### **ከጌታ ኢየሱስ ጥምቀት መማር ማቴ 3፡1-17**

- ዮሐንስ የንስሐ ጥምቀት ያጠምቅ ነበር፡፡ **ማቴ 3፡11**
- ሰዎች ሁሉ ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ ይጠመቁ ነበር **ማቴ 3፡5**
- ያን ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ሊጠመቅ ከገሊላ - ዮርዳኖስ /60 miles ተጉዞ መጣ፡፡/

**<u>አስታውስ(ሽ)</u>** ጌታ ኢየሱስ ፈጽሞ ኃጢአትን አያውቅም።

- ነገር ግን ኃጢአተኞች የሚጠመቁትን ጥምቀት ሊጠመቅ መጣ። **ማቴ 3:13**
- ዮሐንስም ይከለክለው ጀመር /**ማቴ 3:14**/ ዮሐንስ ፈጽሞ ትክክል ነበር። ምክንያቱም ኢየሱስ ኃጢአት የለበትምና።
- ለኢየሱስ ቢጠመቅ የሚጨምርለት፣ ባይጠመቅ የሚጐድልበት ነገር አልነበረም።
- ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ አጥጋቢ ምክንያት ነበረው።

***"እንግዲህ ፍቀድልኝ፣ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ ልንፈጽም ይገባናልና" ማቴ 3:15 አለው።***

**<u>አስታውስ(ሽ)</u>** ደህንነት ወይም የዘለዓለም ሕይወት የሚገኘው በጌታ ኢየሱስ ለኃጢአታችን መሞትና መነሳት እንዲሁም የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን **በማመን** ብቻ ነው።

- ሰው አምኖ ከዳነ በኋላ ጊዜ ካለው ግን የውኃ ጥምቀት በመውሰድ ከጌታ ጋር በመቃብር እንኳ ለመተባበር ፈቃደኛ መሆኑን ማሳየት ይኖርበታል።

## እነማን ይጠመቁ?

- አንድ ሰው የውኃ ጥምቀትን ከመውሰዱ በፊት ሊያሟላቸው የሚያስፈልጉ ሦስት ቅድመ ሁኔታዎች አሉ። ወይም ደግሞ የውኃ ጥምቀትን የሚቀድሙ 3 ነገሮች አሉ።
  1. የወንጌል ትምህርት 2. እምነት 3. ንስሐ/መናዘዝ
- ሐዋርያት እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች ያላሟሉ ሰዎችን ፈጽሞ አያጠምቁም ነበር።
  **ለምሳሌ ጴጥሮስ ሐዋ 2:14-47**

1. ጴጥሮስ ወንጌልን ሰበከ **ሐዋ 2:14-36**
2. ሰዎቹ ልባቸው ተነካ (አመኑ) **ሐዋ 2:37**
3. ንስሐ እንዲገቡ (ኢየሱስን እንዲናዘዙ) ታዘዙ **ሐዋ 2:38**
4. ተጠመቁ **ሐዋ 2:41**

**<u>አስታውስ(ሽ)</u>**: ቃሉን የተቀበሉ (ብቻ) ተጠመቁ **ሐዋ 2:41**

ሕፃናት ወንጌል አይሰበክላቸውም እነርሱም፣ ተረድተውት ልባቸው አይነካም፣ እንዲሁም ንስሐ ግቡ የሚባሉበትም ሁኔታ የለም።

## ዲያቆን ፊልጶስ ሐዋ 8:26-40

1. ስለኢየሱስ ወንጌልን ሰበከለት ቁ 35
2. ሰውየው ለመጠመቅ እንኳ ዝግጁ ሆነ ቁ 36
   ፊልጶስ ግን መጠመቅ ትችላለህ አላለውም፡፡ ይልቅስ በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዶአል አለው፡፡
3. ተናዘዘ ቁ 38
4. ተጠመቀ ቁ 38, 39

✓ በአጠቃላይ ጥምቀት አማኙ ኢየሱስን በማመን ብቻ የዘለዓለምን ሕይወት ተስፋ ከተቀበለ በኋላ የቤተክርስቲያን /የአጥቢያ/ አባል ለመሆንና፣ እንደሌሎች ወንድሞቹ ሁሉ ለኃጢአት መሞቱን እና ከጌታ ኢየሱስ ጋር መቀበሩን፣ መነሣቱን፣ እንዲሁም በአዲስ ሕይወት ለመመላለስ መወሰኑን የሚያሳይበት ነው፡፡

# ***ክፍል ሦስት***

## ***የጌታ ራት***

***"... ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠባት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንስቶ አመሰገነ ቈርሶም:- እንካችሁ ብሉ ይህ ስለእናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፣ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ:: እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው:: በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት" አለ::*** **1ቆሮ 11:23-26**

***ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ አምነው ለዳኑት አማኞች ሁሉ ከጥምቀት ቀጥሎ ይፈጽሙት ዘንድ በቋሚነት ከሰጣቸው ሥርዓቶች ሁለተኛው ነው:: የጌታ ራት ለሁሉም አማኞች የጌታን ሞት ያስቡበት ዘንድ የተሰጠ ቅዱስና ክቡር ሥርዓት ነው::***

### ***ስያሜዎች:-***

1. ***የጌታ ራት*** ***1ቆሮ 11:20 (የቆሮንቶስ ሰዎች ግን ሳቱ)***
2. ***የጌታ ማዕድ*** ***1ቆሮ 10:21 (ከሌላ ማዕድ መካፈል አይቻልም)***
3. ***እንጀራውን መቁረስ*** ***ሐዋ 2:42 (ከተጠመቁ በኋላ ይተጉ ነበር)***

### ***ዓላማው:-***

**1. *የጌታ ሥጋና፣ በደሙ የተፈጸመው የአዲስ ኪዳን መታሰቢያ***

***ጌታ ኢየሱስ ለዓለም ሁሉ ኃጢአት ተላልፎ ከመሰጠቱና ኃጢአታችንን ተሸክሞ ከመሞቱ በፊት የፋሲካን ራት በሚበሉበት ምሽት ላይ የሚበላውን ቂጣ እንጀራ አንስቶ በመባረክ ለደቀመዛሙርቱ እንዲካፈሉት ቆርሶ ሰጣቸው:: ነገ በመስቀል ላይ የሚሰቀለውንና የሚሞተውን ቅዱስ ሥጋውን በዚያ ቂጣ እንጀራ አማካይነት እንዲያስቡት ለመታሰቢያነት ሰጣቸው:: እንዲሁም ከእራት በኋላ ደግሞ ለዓለም ኃጢአት የሚፈሰውን ክቡር እና ንጹህ ደሙን እንዲሁም በዚህም ደም የተፈጸመውን አዲስ ኪዳን ያስታውሱበት ዘንድ በጽዋ ውስጥ የተሞላውን ወይን ጠጅ ባርኮና አመስግኖ ሰጣቸው:: ይህም ከዚያን ሌሊት ጀምሮ (ለቤተክርስቲያን) እርሱ እስኪመጣ ድረስ የጌታን ሞት የምናስብበትና ያን በእንጨት ላይ የዋለ ሥጋውንና የፈሰሰውን የሚያነፃ ደሙን የምናስታውስበት መታሰቢያ ነው::***

***ይህ ማለት ቂጣ እንጀራው አሁን በአብ ቀኝ ያለውን እውነተኛ ሥጋውን ያስታውሰናል እንጂ ራሱ ቂጣው ሥጋ ነው ወይም ይሆናል ማለት አይደለም:: እንዲሁም ጽዋው የዛሬ 2000 ዓመት ለዓለም ሁሉ ኃጢአት የፈሰሰውን ደሙን ያስታውሰናል እንጂ በራሱ ወይን ጠጁ ደም ነው ማለት አይደለም:: ቂጣውንና የወይን ጠጁን ተለውጦ ሥጋ ይሆናል፣ ደም ይሆናል ማለት እጅግ የተሳሳተ መረዳት ሲሆን በአብ ቀኝ የተቀመጠውንም ያን ክቡር ኢየሱስ ማክፋፋት ነው:: እርሱ ሁልጊዜ ይሠዋል እንደማለት ነው::*** ***ዕብ 9:26***

***ምሳሌያዊ ማብራሪያ***:-ለምሳሌ አንድ ወንድማችን ፎቶግራፉን ቢሰጠንና ይህ እኔ ነኝ ይህን ለማስታወሻ ውሰዱት ቢለን ፎቶግራፉ በራሱ ግን ልጁ ራሱ አለመሆኑን እናውቃለን:: ነገር ግን ለወንድማችን ባለን አክብሮትና ፍቅር መጠን ለፎቶግራፉ ያለን ክብር ይወሰናል:: ለፎቶግራፉ ያለን ከበሬታ ከጠፋ ለወንድማችን ያለንን ጥላቻ ገለጽን ማለት ነው::

**2. የጌታን መከራና ሞት ማስታወሻ**

"ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት" **ሉቃ 22:20** በዚህ መሠረት ቤተክርስቲያን ቂጣ እንጀራ እና የወይን ጠጅ በማዘጋጀት የጌታን መከራና ሞት በማሰብ በዚህም ለእርሷ የተደረገላትን መዳን እያሰበች ጌታን ታመሰግንበታለች:: እንጀራውንም በመብላት ጽዋውንም በመጠጣት የጌታን ሞት እርሱ እስኪመጣ ድረስ ትናገራለች:: **1ቆሮ 11:26**

**3. የቤተክርስቲያንን አንድነት መግለጫ**

አንድ እንጀራ ስለሆነ እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ ሥጋነን ሁላችን ያን አንዱን እንጀራ እንካፈላለንና **1ቆሮ 10:17** እግዚአብሔርና ቃሉ የሚያውቁት አንዲት ቤተክርስቲያን እንዳለች ብቻ ነው:: በጌታ ኢየሱስ ያመኑና የዳኑ በሙሉ አንድ ላይ አንዲት ቤተክርስቲያን ተብለው ይጠራሉ:: አማኞች በቁጥር ብዙ ቢሆኑም ስንኳ ነገር ግን አንድ አካል /ቤተክርስቲያን/ ናቸው:: ይህን የሚገልጹትም በአካል ምንም ብዙዎች ቢመስሉም ግን አንድ ሥጋ መሆናቸውን አንዱን ቂጣ እንጀራ በመቁረስ ያረጋግጣሉ:: **1ቆሮ 12:12-28**

## እነማን ይካፈሉ? ይቁረሱ?

የጌታ ራት ሥርዓት የተሰጠው አምነው ለዳኑ አማኞች በሙሉ ሲሆን ክርስቲያኖች ሁሉ ጌታን እንዲያስቡበት ጌታ አጥብቆ ይፈልጋል:: ይህ ማለት ግን አማኞች ለመታሰቢያው ያላቸው ክብር ዝቅ እንዳይል ሊጠነቀቁ ይገባቸዋል:: ከዚህም የተነሣ አማኞችን እንጀራውን እንዳይቆርሱ ሊያግዷቸው የሚችሉ ነገሮች መኖራቸውን ማወቅ ጠቃሚ ነው::

## እንጀራውን ከመቁረስ የሚያግዱ ሁኔታዎች

የጌታ ራት የብሉይ /አሮጌ/ ኪዳኑን የፋሲካ በዓል ተክቶ ለቤተክርስቲያን የተሰጠ ሥርዓት ነው:: በብሉይ ኪዳኑ የፋሲካ በዓል በጥላነት የተገለጹና አማኙን እንዲጠነቀቅ የሚያስተምሩ ነገሮች ተገልጸዋል::

**1. ከእርሾ አለመጠበቅ ከጌታ ራት ያግደናል**

በአሮጌው ኪዳን ዘመን ፋሲካን ለማክበር የሚፈልጉ ሰዎች በሙሉ በዓሉ ከመድረሱ አስቀድሞ 7 ቀናት ሙሉ (1 ሳምንት) በቤታቸው ውስጥ እርሾ እንዳይገኝ እግዚአብሔር አስጠንቅቆ ነበር፡፡ **ዘፀ 12:14-20**

- **በአዲስ ኪዳን የእርሾ ትርጉም፡-**

**ሀ. የተሳሳተ ትምህርት**

ከማናቸውም ቅንጣት ታክል ስህተት /ዓመጽ/ ካለበት ትምህርት ሳምንቱን በሙሉ ራስን መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡ **ማቴ 16:6,12, 1ዮሐ 4:1-3, 2ዮሐ ቁ 9, 2ጢሞ 2:19**፡፡ ያለበለዚያ ጥቂቱ እርሾ ብዙውን ሊጥ ያቦካልና ከእግዚአብሔር እውነት ሊያርቀንና ከተወደደው የጌታ ማዕድ ሊያግደን ይችላል፡፡

**ለ. የከፉ የሥነ-ምግባር /ኃጢአት/ ችግሮች ወይም የተገለጡ ኃጢአቶች፡፡**

መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉም የሰው ዘሮች ያለልዩነት ኃጢአተኞች እንደሆኑ ይገልፃል፡፡ ለዚህ መፍትሔ ይሆን ዘንድም ኢየሱስ ለኃጢአተኞች ሞቷል፡፡ አንድ አማኝ አምኖ ከዳነ በኋላ ግን በጣም በተገለጡ እና የሕይወት ምስክርነቱን በሚያበላሹ ጉዳዮች ከተጠላለፈ ይህ የክፋት እርሾ ፋሲካን እንዳያከብር/የጌታ ራትን እንዳይቆርስ ያደርገዋል፡፡ **1ቆሮ 5:13, 1ጢሞ 5:24**

## መፍትሔ

አማኞች የጌታ ራትን ከመቁረሳቸው በፊት ራሳቸውን በጥሞና መንፈስ ሊመረምሩና ሊናዘዙ በራሳቸውም ላይ ሊፈርዱ እና ምህረት ሊለምኑ ይገባቸዋል፡፡ በራሳችን ላይ ቀድመን ከፈረድን ጌታ አይፈርድብንም ከዚህ በኋላ አማኙ እንጀራውን መቁረስ ይችላል፡፡ **1ቆሮ 11:27-32**

## ፍርድ

ወንድማችን ለመታሰቢያነት የሰጠንን ፎቶግራፍ አግባብ ባልሆነ ሥፍራ ብናስቀምጠው ወይም ትኩረት ሳንሰጠው ብንጥለው ይህ በቀጥታ ለእርሱ የነበረንን ክብርና ፍቅር እንደቀነስን ያሳያል፡፡

ጌታ ለመታሰቢያነት የሰጠውን ይህን ሥርዓት የሚያናንቅ ወይም ክብር ባለመሥጠት ዓላማ እንደሌለው ተራ የምግብ ዳቦ እና ጽዋ ቆጥሮት ቢበላው ወይም ቢጠጣው የጌታን ሥጋ ምሳሌ ስለማይለይ እንዲሁም ደሙን ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላል፡፡

በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ በራሳቸው ላይ ሳይፈርዱ/ምህረት ሳይጠይቁ/ እንዲሁም ዓላማውን ባለመረዳት በእንጀራነቱና በጽዋነቱ ብቻ የበሉና የጠጡ ሰዎች በድካም፣ በበሽታ፣ እና በእንቅልፍ/ሞት/ ተቀጥተው ነበር:: **1ቆሮ 11:30**

## *የጌታ ራት "ጊዜ"*

ከሳምንቱ በ*መጀመሪያ ቀን* /Sunday እሁድ/

እንጀራ ለመቁረስ ተሰብስበን ሳለን ... **ሐዋ 20:7** *የመጀመሪያዎቹ* ክርስቲያኖች በየሳምንቱ በፊተኛው ቀን /እሁድ/ *ለጌታ ራት ሥርዓት* ይሰበሰቡ ነበር:: ስለዚህ ለእግዚአብሔር ቃል በፍርሃት ለምትታዘዝ ቤተክርስቲያን ይህ ሳምንታዊና ቀጣይ የሆነ የተወደደ *ሥርዓት* ነው::

## ፀሎት (አምልኮት) ቃል ንባብ ወዘተ

በጌታ *ራት ሥርዓት* ላይ ሌሎች ምድራዊና *ሥጋዊ* እንዲሁም የኑሮ ጉዳዮች በርዕስነት አይነሱም:: ለነዚህ የራሳቸው የሆነ የፀሎት ኘሮግራም አላቸው:: በጌታ *ራት* ጊዜ አማኞች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር በመሆን መንፈስ እንደመራቸው የጌታን ሞት፣ መከራ፣ የማስታረቅ *ሥራ* ወዘተ የሚመለከቱ ዝማሬዎችን፣ ፀሎቶችን ያቀርባሉ:: እንዲሁም ተዛማኝ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ይነበባሉ:: ከዚያም እንጀራውን በመቁረስ ይካፈላሉ፣ ከጽዋውም ይጠጣሉ:: በመቀጠልም ለአብ የሚሆኑ ውዳሴዎችን በኢየሱስ ያቀርባሉ::

**"ኢየሱስ ብቻ ያድናል"**

## <u>ማስታወሻ</u>

የጥምቀትም ይሁን የጌታ *ራት ሥርዓቶች* **ለመዳን የተሰጡ** ሳይሆኑ **ለዳነ** ሰው ብቻ የተሰጡ *ሥርዓቶች* ናቸው:: ከዘላለም ሕይወት /*መዳን*/ *ጋር* ፈጽሞ ግንኙነት የላቸውም::

# ***ክፍል አራት***

## ***ፀጋ እና ሕግ***

- ኃጢአት አይገዛችሁምና ከፀጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁምና፡፡ **ሮሜ 6:14**
- ሕግና፣ ፀጋ በተለያዩ መጠሪያዎች ተነፃጽረዋል፡፡

| ***ሕግ*** | ***ፀጋ*** |
|---|---|
| 1. የኃጢአትና የሞት ሕግ | ▪ የሕይወት መንፈስ ሕግ **ሮሜ 8:2** |
| 2. አሮጌው የፊደል ኑሮ | ▪ አዲሱ የመንፈስ ኑሮ **ሮሜ** 7:6 |
| 3. በድንጋይ ላይ በፊደል የተፃፈ | ▪ በመንፈስ በልብ ፅላት ላይ **2ቆሮ 3:1-18** |
| 4. የሞት አገልግሎት | ▪ የመንፈስ አገልግሎት **2ቆሮ 3:7** |
| 5. የኩነኔ አገልግሎት | ▪ የጽድቅ አገልግሎት **2ቆሮ 3:7-11** |
| 6. አጋር /ብሉይ ኪዳን/ | ▪ ሳራ /አዲስ ኪዳን/ **ገላ 4:21-31** |
| 7. የሰዎች ጽድቅ | ▪ የእግዚአብሔር ጽድቅ **ሮሜ 3:21, 10:3, ኤፌ 2:18** |
| 8. የሥራ የሆነ ጽድቅ | ▪ የእምነት የሆነ ጽድቅ **ሮሜ 9:30-33 ሮሜ10:5-13** |
| 9. ሞግዚት | ▪ ክርስቶስ/እምነት/ **ገላ 3:21-29** |
| 10. የምትደክም /የማትጠቅም/ | ▪ የተሻለ ተስፋ **ዕብ 7:18** |
| 11. ፊተኛው /ብሉይ ኪዳን/ | ▪ ሁለተኛው /አዲስ ኪዳን/ **ዕብ 8:6-13** |
| 12. የናቀው ሞት ይገባዋል | ▪ ይልቅ የሚብስ ቅጣት ይገባዋል **ዕብ 10:28** |
| 13. በሙሴ ተሰጥቶ <u>ነበር</u> | ▪ በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ **ዮሐ 1:17** |

## ***ሕግ ለምን ተሰጠ?***

- ሰው ቢያደርገው ኖሮ በሕይወት እንዲኖር **ሕዝ 20:10, ገላ 3:12**
- በደል እንዲበዛ ሮሜ 5:21
- ኃጢያት እንዲታወቅ ሮሜ 7:7

ነገር ግን
1. በሕግ መጽሐፍት በተፃፈው ሁሉ ፀንቶ የማይኖር/አንድ ቀን የሚስት/ ሕጉን ሁሉ የማያደርገው የተረገመ ይሆናል፡፡ **ገላ 3:10**
2. ሁሉን ጠብቆ ነገር ግን አንዲቷን ቢተላለፍ በሁሉ በደለኛ ይሆናል፡፡ ***ያዕ* 2:10**
3. ይህም ቢሆን እንኳ ሕጉ የተሰጠው ለእሥራኤል ሕዝብ ብቻ ነበር፡፡ **ሮሜ 9:4**

- ይህም ስለሆነ ደግሞ

  - *ሥጋ* የለበሰ ሁሉ ሕግን ሙሉ በሙሉ መፈፀም አይችልም። **ሮሜ 3:20**
  - በእግዚአብሔር ፊት ፃድቅ መሆን አይቻልም። **ኢዮ 4:17, 9:2**
  - ተወልዶ እስኪሞት ሰው ጽድቅን ብቻ ማድረግ አይችልም። **መዝ 13:2**
  - አንድ ስንኳ ፃድቅ የለም **መዝ 13:2, ሮሜ 3:11**
  - ፃድቅ የሚባል እንኳ ኃጢአትን ያደርጋል። **መክ 7:20**
  - የሕግን *ሥራ* በመሥራት መጽደቅ አይቻልም **ሮሜ 3:20, 3:27, 4:2, 7:14, 6:14, ገላ 2:16, 3:10, 3:21, 4:21, 5:4, ኤፌ 2:8**

## "*ፀጋ*"

"*ፀጋ*" ማለት ለማይገባው ማንነት የተሰጠ ስጦታ ማለት ነው። ይህም እንዲሁ በእግዚአብሔር ደግነት ላይ ተመስርቶ ኃጢአተኛ ለሆነው ሰው ያለምንም ምክንያት ከእግዚአብሔር ከፍቅር የተነሳ ብቻ የሚሰጠው ስጦታ ነው።

ፀጋና፣ ስጦታ ሁለት የተለያዩ ትርጉም ያዘሉ ቃላት ናቸው። ስጦታ ከእኛ ጋር መልካም ወዳጅነት ላለው ሰው የምንሰጠውን መታሰቢያ የሚያካትት ሲሆን ፀጋ ግን ለሚጠላንና ክፉ ለሆነብን ሰው እንዲሁ ወደነው የምናደርግለት ስጦታ ነው። እንግዲህ የፀጋ ስጦታ ማለት ሰውየው ከራሱ ተገቢነት የሚቀበለው ሳይሆን እንዲሁ የተሰጠው ነው ማለት ነው።

በዚህ መሠረት የዛሬ 2000 ዓመት የእግዚአብሔር ፀጋ ይኸውም በሕግ *ሥራ* ሊጸድቅ ያልቻለውን ሰው የሚያድን የእርሱ ፀጋ ተገልጧል። ይህም ፀጋ ሰዎችን ሁሉ ማዳን ይችላል። ነገር ግን ሰው ለመዳን ከፈለገ የግድ ይህንን ፀጋ በእምነት መቀበል ይኖርበታል። **ቲቶ 2:11**

- ሰው የሚድነው ሕግን በመፈጸም ሳይሆን ፀጋውን በእምነት በመቀበል ብቻ ነው። **ሮሜ 3:28**
- ኢየሱስ ፀጋንና እውነትን ተመልቶ መጥቷል **ዮሐ 1:14**
- ይህ ፀጋ ዓለምን ሁሉ ያድናል **ቲቶ 2:11**
- ፀጋው የሚያድነን ኢየሱስ *ሥራ*ችንን ሁሉ እንደሠራልን፣ ሕጉ ከእኛ የሚጠይቀውን እርሱ እንደፈጸመው በማመን፣ እንዲሁም በእኛ ሳይሆን በእርሱ *ሥራ* ወደ እግዚአብሔር እንዳቀረበን በማመንና በመቀበል ነው። **ኤፌ 2:4-8, 2:18**
- የእግዚአብሐር ጽድቅ እንጂ የሰው ጽድቅ አያድንም **ሮሜ 3:21**

- እንዲያው መዳን /ያለምንም እኔነት/ **ሮሜ 3:21-28**
- ኃጢአተኛን እንደሚያጸድቅ ማመን ጽድቅ ሆኖ ይቆጠራል **ሮሜ 4:4-8, ሮሜ 4:9-25**
- ኃጢአታችን በጣም ብዙ ቢሆንም የወረደው ፀጋ ግን ከኃጢአታችንና ከበደላችን ሁሉ በጣም ይበዛል **ሮሜ 5:15-21, ሮሜ 4:9-25**
- በሕግ እንዳንጠየቅ ለሕግ ሞተናል **ሮሜ 7:1-6**
- በእምነት እንጂ በሥራ አይደለም **ሮሜ 9:30, 10:3-13**

***ተጨማሪ 2ቆሮ 3:4-17, 2ቆሮ 4:1-6, ገላ 2:16-21, ገላ 3:21-29, ቈላስ 2:16-23, ገላ 3:6-14***

- እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን ሰላምን እንያዝ **ሮሜ 5:1-11**
- ፀጋው ኃጢአተኛውን አድኖ ብቻ አያበቃም። በዳነው አማኝ ውስጥ ሌሎች ተከታታይ ሥራዎችን ይሠራል። አማኙ ራሱ እስኪደነቅ ድረስ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በአማኙ ሕይወት ውስጥ ልዩ ልዩ ሥራዎችን በመሥራት ባለብዙ ፍሬ ያደርገዋል። **ቲቶ 2:11-15**
    - ይኸው ፀጋ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊ ምኞትን በማስካድ እውነተኛ የቅድስና ሕይወት እንድንኖር ያስተምረናል።
    - **2ቆሮ 4:13-15, 2ቆሮ 6:1-10 -** በዚህ ውስጥ እያለፍን ወንጌልን መናገር ያስችለናል።
    - ጌታም ለዚህ የፀጋ ቃል የታመነ ነው። **ቲቶ 3:3-7**

# አሜን።

# ክርስቲያን ምንድነው

ተዘጋጀ፡- በዳዊት ፋሲል
2002/ጅማ

# <u>ክርስቲያን ምንድነው?</u>

- ❖ ክርስቲያን ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ የተለያዩ የግለሰቦችና፣ የሃይማኖቶች፣ መላምቶች እንዲሁም ግምቶች በምላሽነት ይቀርባሉ።
- ❖ መጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛው የእግዚአብሔር ቃል ሲሆን ክርስቲያን ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ የራሱ የሆነ መልስ አለው።

## <u>ክርስቲያን በመጽሐፍ ቅዱስ ምንድነው</u>?

### 1. <u>*ዳግመኛ (ለ2ኛ ጊዜ) የተወለደ ነው።*</u>

- ➢ ዳግመኛ የተወለደው ከእግዚአብሔር ነው (ዮሐ 1:13)
- ➢ ዳግመኛ መወለድ የሚለው ቃል አማኙ አስቀድሞ ከሌላ ወገን ተወልዶ እንደነበር ያሳያል። ተወልዶ የነበረውም ከሥጋና ከደም ፈቃድ በመሆኑ ፍፁም ሥጋዊ የነበረ እና መንፈስ ከሆነው ከእግዚአብሔር ጋር ምንም ዓይነት ሕብረት ያልነበረው ነበር። (ዮሐ 3:6)
- ➢ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ “መወለድ” ወይም “ልጅነት” የሚለው ቃል ሃሳብ “ቤተሰብነትን”፣ “የወላጅን ባህርይ መካፈልን”፣ እና “ፍፁም ሕብረትን“ ያሳያል በመሆኑም በሰውና ሰው መካከል ካለው የመዋለድ ሥርዓት ፈፅሞ የተለየ ነው።

  <u>ለምሳሌ</u> ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ስንል ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት ያለው፣ ባህርዩን የሚካፈል ማለታችን ነው።
- ➢ አማኝ ዳግመኛ የተወለደው በውሃና በመንፈስ አማካኝነት ነው (ዮሐ 3:5)

  <u>ሁለት ዓይነት ውሃዎች</u>

  ሀ) ቋሚ ውሃ = የእግዚአብሔር ቃል (የመጽሐፍ ቅዱስ) ምሳሌ (ኤፌ 5:26 ዮሐ 15:3, ዘፀ 30:17-21)

  ለ) ወራጅ ወንዝ = የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ማለትም ዮሐ 7:37-39, ዮሐ 4:14
- ➢ ዳግመኛ የተወለደበት ውሃ የወንጌሉ ቃል ነው (1ጴጥ 1:23, ያዕ 1:18)
- ➢ እንዲሁም ከመንፈስ ቅዱስ ተወልዷል (ኤፌ1:13)
- ➢ ከመንፈስ ቅዱስ በመወለዱ ምክንያት ሙት የነበረው መንፈሱ ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ማድረግ ችሏል።

## ድጋሚ የተወለደበት ምክንያቶች

❖ የእግዚአብሔር ልጅ እንዲሆን (ዮሐ 1፡13)፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ በመሆኑም የሚከተሉት ነገሮች ተፈጽመውለታል፡፡

ሀ) የቀደመው የትውልድ መሥመር (በሥጋና፣ ደም ፍቃድ መመራት) ቀርቶለታል (ሮሜ 8፡14፣2ጴጥ 1፡3, ዮሐ 1፡13)

ለ) አይሁዳዊም፣ ግሪካዊም መሆን አይችልም (ቈላ 3፡10-11፣ ራዕ 5፡9-10)

***ማስታወሻ*፡-** *ግሪክ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚወክለው በዓለም ላይ ያሉትን የአህዛብ አገሮች በሙሉ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ኢትዮጵያዊ ግሪካዊ የሚለውን ንባብ ኢትዮጵያዊ ብሎ ቢረዳው ተገቢውን ትርጉም ያገኛል፡፡*

ሐ) ሰማያዊ ዜግነትን አግኝቷል፣ይኸውም በዳግመኛ መወለድ ያገኘው መብት (Birth Right) ነው፡፡ በምድር ላይ ሥራው ልዑክነት (Ambassador) ነው (2ቆሮ 5፡18-21)

መ) የእግዚአብሔር ወራሽ ሆኗል፡፡ (ዮሐ 3፡5፣ ሮሜ 8፡17፣ ገላ 4፡7 1ጴጥ 1፡3-5)

## *2. ክርስቶስን ወደ መምሰል የሚለወጥ ነው፡፡*

- እግዚአብሔር አስቀድሞ አዳምን ፍጹም በራሱ የክብር መልክና የባህርይ ምሳሌ ፈጠረው
- **መልክ** የእግዚአብሔር የገዢነት **ክብር** ማለት ነው (2ቆሮ 3፡18)
  **ምሳሌ** የእግዚአብሔር **ባህርይ** ማለት ነው (ዕብ 1፡3)
- ሰው ኃጢአትን በማድረጉ የእግዚአብሔር ክብር (መልክ) ጐደለው (ሮሜ 3፡23)
- አዳም ከኃጢአት በኋላ የገዥነት መልኩን (ክብሩን) አጣ እንዲሁም የኃጢአት ባህርይ (ምሳሌ) መገለጫ ሆነ ፡፡ ምድርም ጌታ እስኪመጣ ድረስ (ራዕ 20) ገዥ ስላጣች የዚህ ዓለም ገዥ ዲያብሎስ ሆነ፡፡
- አዳም ከገነት ከተባረረ በኋላ ልጆቹን በራሱ መልክ (የእግዚአብሔር ክብር የጐደላቸው) እና በራሱ ምሳሌ (ኃጢአተኛ ባህሪይ ያላቸው) አድርጐ ወለደ (ዘፍ 5፡3)
- ከዚያ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ሥጋ ከለበሰ ወገን ጌታ ኢየሱስ "እኔን ያየ አብን አየ" ሲል እርሱ ብቻ የእግዚአብሔርን መልክ (ክብር) እና ምሳሌ (ባህሪይ) እንደሚያሳይ ተናገረ (ዮሐ 14፡8-10)
- ምክንያቱም እርሱ ብቻ የእግዚአብሔር የክብሩ (መልኩ) መንፀባረቅ ወይም መገለጫ እንዲሁም የባህርዩ ምሳሌ ነበረና ነው፡፡ (ዕብ 1፡3)

## ከዘላለም ዘመናት በፊት የነበረ የእግዚአብሔር ዕቅድ

ሀ) አዳም መልኩንና ምሳሌውን እንደሚጥል እግዚአብሔር አስቀድሞ በሁሉን አዋቂነት (Omniscience) ባህርዩ ያውቅ ነበረ።

ለ) በመሆኑም ጌታ ኢየሱስ ብቻ የእርሱ የመልኩ (ክብሩ) መንፀባረቂያ ወይም መገለጫ እና የባህርዩ ምሳሌ እንዲሆን አስቀድሞ ወሰነ።

ሐ) በመቀጠልም በጌታ ኢየሱስ ብቸኛ አዳኝነት የሚያምኑ ሁሉ የልጁን መልክ እንዲመስሉና የጠፋውን የገዥነት መልክ እና መንፈሳዊ ባህርይ መልሰው እንዲያገኙ አዳምን ሳይፈጥር በፊት አስቀድሞወሰነ። (ሮሜ 8፡29)

መ) በዚህም ምክንያት አማኝ ድጋሚ ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ ያንን የተወሰነለትን መልክ (ክብር) ለመምሰል ከክብር ወደ ክብር ይሸጋገራል። (2ቆሮ 3፡18)

### *3. <u>የክርስቶስን ፍለጋ (Steps) የሚከተል ነው።</u>*

- ጌታን ለመከተል በመጀመሪያ እርሱን ብቻ መመልከት ያስፈልጋል (ዕብ 3፡1)
- በእግዚአብሔር ቃል ብርሃንነት ፍለጋውን እየተከተሉ መሄድ (1ጴጥ 2፡21) የጌታ በጐች (እውነተኛ አማኞች) መለያቸው ድምጹን እየሰሙ ከእርሱ በኋላ መከተል ነው (ዮሐ 10፡27)
- ጌታን ብቻ እያዩ የሕይወትን ሩጫ በትዕግስት መሮጥ የአማኞች ድርሻ እና መብት ነው (ዕብ 12፡2)

### *4. <u>ከክርስቶስ ጋር የተሰቀለ ነው።</u>*

- የኃጢአት ሥጋው (አሮጌው ሰው) ይሻር ዘንድ (ሮሜ 6፡6)
- እኔው (Self) ሕያው ሆኖ እንዳይኖር (ገላ 2፡20)
- ክርስቶስ በእርሱ እንዲኖር (ገላ 2፡20)
- በዓለም ካለው ጋር ሕብረት እንዳይፈጥር (ገላ 6፡14)
  - በዓለም ያለው(1 ዮሐ 2፡15-16)
    - ሀ) የሥጋ (ክፉ) ምኞት (Disordered bodily desires) (NJB)
    - ለ) የዓይን አምሮት (Disordered desires of the eyes, (NJB)
    - ሐ) ስለገንዘብ መመካት (The boasting of what he/she has (NIV)

*<u>ማስታወሻ</u>፡- አማኝ ሥጋህን ስቀል ተብሎ አይታዘዝም፤ ነገር ግን "እንደተሰቀለ" እንዲያውቅና መሰቀሉን አሜን ብሎ እንዲቀበል ማስተማር ይገባል።*

## *5. ከክርስቶስ ጋር አብሮ የሞተ (የተገደለ) ነው::*

*በመሆኑም:-*

ሀ) ዋነኛው ሕይወቱ በሰማይ ከክርስቶስ ጋር ተሠውሮለታል (ቈላ 3:3)

ለ) ለኃጢአት ተገዢ መሆኑ አብቅቷል (ሮሜ 6:2,11)

ሐ) ከሕግ ተፈትቶ ለክርስቶስ (ጸጋ) ሆኗል:: (ሮሜ 7:1-6)

መ) ለሰዎች ሥርዓትና ት/ት አይገዛም (ቈላ 2:16-23፣ ገላ 4:8-11)

ሠ) ለእግዚአብሔር ሕያው ሆኗል (ሮሜ 6:11)

ረ) ከእርሱ ጋር በሕይወት ይኖራል (2ጢሞ 2:11)

- *በመሆኑም በየቀኑ ይገደላል (ሮሜ 8:36)*

## *6. ከክርስቶስ ጋር አብሮ ተቀብሯል::*

- መቀበር መሰወር ነው:: በመሆኑም የአማኙ የቀድሞው ሕይወት አሮጌው ማንነት ተቀብሯል::
- መቀበሩንም በውሃ ጥምቀት አረጋግጧል (ቈላ 2:12፣ ሮሜ 6:4)
- በመሆኑም የሥጋ (የኃጢአት) ሰውነት ተገፍፎ ተቀብሯል (ቈላ 2:11)
- አሁን በእርሱ የሚኖረው ክርስቶስ ነው (ገላ 2:20)

## *7. ከክርስቶስ ጋር አብሮ በትንሣኤው የተነሣ ነው::*

- እግዚአብሔር በጸጋው (ነፃ ሥጦታው) ሀብታም መሆኑን ለማሳየት አማኞችን ሁሉ ከክርስቶስ ጋር አስነሣ (ኤፌ 2:7)
- አማኙ ለኃጢአት ሞቶ ለጽድቅና ለእግዚአብሔር ሕያው ሆኖ እንዲኖር (ሮሜ 6:4-11)
- በምድር ያለውን ሳይሆን በላይ ያለውን ለመሻት ተነስቷል:: (ቈላ 3:1)

## *8. ከክርስቶስ ጋር በእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠ ነው::*

- እግዚአብሔር በጸጋው ባለጠጋ መሆኑን ለማሳየት አማኙን ከኢየሱስ ጋር በቀኙ አስቀምጦታል:: (ኤፌ 2:6-7)
- ምክንያቱም የአማኙ ማንነት ፍጹም በክርስቶስ ውስጥ ተሰውሯልና:: (ቈላ 3:3)
- የተዋረደ መንፈስ ያላቸው ማለትም ኃጢአተኛ መሆናቸውን በመረዳት ኢየሱስን አማራጭ የሌለው አዳኝ አድርገው የተቀበሉ ሁሉ በዚህ የከፍታ ሥፍራ ላይ ተቀምጠዋል:: (ኢሳ 57:15)
- በአብ ቀኝ የተቀመጠ ሰው ምድራዊውን ነገር እንደትንሽ ነገር ይቆጥራል:: (ቈላ 3:1-4)
- የተቀመጠ ሰው የደህንነት ሥራው የተጠናቀቀለት ነው፣ መቆም ግን የኃጢአትን ሥርየት ገና አለመቀበልን ያመለክታል (ዕብ 10:11-12)
- በሰማይ የተቀመጠ ሰው በሰማይ ባለው ሀብትና በረከት ሁሉ የተባረከ ነው (ኤፌ 1:3)

### *9. ጌታ በክብር በሚገለጥበት ጊዜ አብሮ በክብር የሚገለጥ ነው:: (ቈላ 3:4)*

- አሁን የክብር ጊዜ ሳይሆን የልቅሶ፤ የምጥ ጊዜ ነው (ዮሐ 16:20-22)
- አሁን ስለስሙ የመነቀፊያ ጊዜ ነው (ሉቃ 6:22-23፣ ዮሐ 16:1-4)
- ቤተክርስቲያን በዓለም ውስጥ ክብርና ተቀባይነት የላትም:: (ዮሐ 17:14) ምክንያቱም አሁን መስቀል የመሸከሚያ ጊዜ እንጂ ሙገሳ የመቀበያ ጊዜ አይደለምና:: (ሉቃ 14:27)
- ጌታ መንግሥቱን ለመግለጥ ሲመጣ ግን አማኙም ነጭ ልብስ ለብሶ ከእርሱ ጋር በክብር ይገለጣል:: (ራዕ 19:7-16፣ ቈላ 3:4)

### *10. ከክርስቶስ ጋር ሺህ ዓመት የሚነግሥ ነው::*

- ጌታ ቤተክርስቲያን ከተነጥቀች ከ7 ዓመታት በኋላ ተመልሶ ከቅዱሳን ጋር ወደ ምድር ይመጣል:: (ራዕ 19:7-16)
- ክርስቶስ ጠላቶቹን ሁሉ ከተበቀለ በኋላ የሺህ ዓመት መንግሥቱን በምድር ላይ ይመሠርታል:: (ራዕ 20)
- ቤተክርስቲያን (ንግሥቲቱ) የበጉ ሚስት ከምድር በላይ ሆና ከንጉሡ ክርስቶስ ጋር ሺህ ዓመት ትነግሣለች:: (ራዕ 20:4-6፣ መዝ 45)
- ከእርሱ ጋር በዚህ እምነት ብንጸና እንነግሣለን (2ጢሞ 2:11)
- በፊተኛው ትንሣኤ የሚነሱ ሁሉ ይነግሣሉ (ራዕ 20:6)

"የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ አዎንና አይደለም አልነበረም:: ነገር ግን በእርሱ አዎን ሆኖአል:: እግዚአብሔር ለሰጠው የተስፋ ቃል ሁሉ አዎን ማለት በእርሱ ነውና፣ ስለዚህ ለእግዚአብሔር ስለክብሩ በእኛ የሚነገረው አሜን በእርሱ ደግሞ ነው" (2ቆሮ 1:18-20)

_የአዘጋጁ አድራሻ፡-_ ዳዊት ፋሲል
**ስ.ቁ. 0917804407**
*ፖ.ሣ.ቁ. 67 ጅማ*
**E-mail – niguye2004@yahoo.com**

# መጽሐፍ ቅዱስ







***በዳዊት ፋሲል***

# <u>ክፍል ፩</u>

## 1. <u>የስሙ ትርጉም</u>

ቅዱስ የሚለው ቃል ከግዕዙ "ቀደሰ" የሚል ግስ የወጣ ሲሆን ትርጉሙም "መረጠ፣ ለየ" እንደማለት ነው:: ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ስንል "የተመረጠ"፣ "ልዩ"፣ መጽሐፍ ማለታችን ነው::

*<u>ማስታወሻ</u>:- በግዕዝ ፊደል ውስጥ ሁለት ዓይነት ሠ እና ሰ አሉ:: በተለያየ አገባብ ሲጠቀሙባቸውም የትርጉም ልዩነት ያመጣሉ **<u>ለምሳሌ</u>** ቀደሠ - አመሰገነ*

*ቀደሰ - ለየ*

***<u>ለምሳሌ:-</u>*** *"**ተቀደሱ**" ሲል ከመካከላቸው ውጡና "**የተለያችሁ**" ሁኑ እንደማለት ነው::*

*2ቆሮ 6:17*

መጽሐፍ ቅዱስ ቅዱስ የተባለበት ምክንያቶችም

1. ሰጪው እግዚአብሔር ራሱ ቅዱስ በመሆኑ
2. ስፍር ቁጥር ከሌላቸው የዓለማችን ልዩ ልዩ መጽሐፍቶች እጅግ በጣም የተለየ መጽሐፍ በመሆኑ ነው:: (ወ.ዘ.ተ.)

## 2. <u>መጽሐፍ ቅዱስ ምንድነው?</u>

1. መጽሐፍ ቅዱስ ራሱን የእግዚአብሔር ቃል በማለት ይጠራል:: ማር 7:13 ሮሜ 10:17 ይህም ማለት የእግዚአብሔር ቃል ከመሆኑ የተነሳ እግዚአብሔርም ፃድቅ ወይም እውነተኛ እንደመሆኑ መጠን መጽሐፉም ምንም ዓይነት ግድፈት የሌለበት (Innerant) እና ፈጽሞ ስህተት አልባ (Infallible) ነው ማለት ነው:: **(ምሳ 30:5፣ 2ጴጥ 1:21፣ ዮሐ 10:35 መዝ 19:7)**

2. እጅግ በጣም ረዥም እድሜ ያለው መጽሐፍ ሲሆን በስርጭትም ረገድ የመጽሐፍ ቅዱስን ያህል ስርጭት ያለው የኃይማኖትም ይሁን ሌላ ዓይነት መጽሐፍ በዓለም ላይ ከቶ የለም:: ያም ብቻ ሳይሆን በዓለማችን ቋንቋዎች ሁሉ የተተረጐመ መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ በመሆኑ ልዩ ያደርገዋል::

*<u>ማስታወሻ</u>:- መጽሐፍ ቅዱስ ከ2000 በላይ በሚሆኑ ቋንቋዎች የተተረጐመ ሲሆን በዓለም ሁሉ ያልደረሰበት አገር ፈጽሞ የለም::*

3. ለዘለዓለም ሕይወት የሚሆነው የአምላክ የማዳን ኃይል (ወንጌል) የሚገለጥበት ብቸኛው መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስ ነው:: ሮሜ 1:16 እንዲሁም በሥጋ ሕይወት ስንኖር በዚህ ምድር ለሥጋችን፣ ለነፍሳችን፣ ለመንፈሳችን የሚሆን በረከት የምናገኝበት መጽሐፍ ነው:: (ዮሐ 15:7) ለየትኛውም ዓይነት ሥጋዊና መንፈሳዊ ኑሮአችን መመሪያ እና መልስ አለው:: (2ጢሞ 3:16)
4. መጽሐፍ ቅዱስ ለሽማግሌዎች፣ ለሕፃናት፣ ለምሁራን፣ ለመሃይምናን፣ ለወንዶች፣ ለሴቶች ሁሉ የሚሆን ሁሉም ሊያነቡት የሚችሉት ብቸኛ መጽሐፍ ነው:: እንዲሁም በየትኛውም ባህል ውስጥ በየትኛውም ግለሰብ ወዘተ ሊነበብ የሚችልና ለውጥ ማምጣት የሚችል (Revolutionary) መጽሐፍ ነው::
5. በውስጡ ያለው ታሪክ እውነተኛነት ደግሞ ይበልጥ ከየትኛውም የኃይማኖት መጽሐፍ ልዩ አድርጐታል:: በውስጡ ያሉት ግለሰቦች፣ የእግዚአብሔር ታላላቅ ሥራዎች ወዘተ እውነተኛ ስለሆኑ ለማንኛውም ሰው እውነተኛና ተጨባጭ የሆነን የሕይወት መመሪያ ሊሰጥ ችሏል:: ከዚያም ባሻገር ስለሚመጣው ቀጣይ ሕይወትም በእርግጠኝነት ዋስትና መስጠት ችሏል:: (ዮሐ 3:16)
6. የእግዚአብሔርን ቀጥተኛ ሀሳብ ለሰዎች መግለጥ የቻለ ብቸኛው መጽሐፍም እርሱ ነው:: ይህንን ማሟላት የሚችል የኃይማኖት መጽሐፍም በዓለም ላይ ፈጽሞ የለም:: በማንኛ ውም ጉዳይ ላይ ቀጥተኛ የሆነ የእግዚአብሔር ፈቃዶችና፣ ፍላጐቶች የሚገኙት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብቻ ነው::
7. የመጽሐፍ ቅዱስ ዋነኛ ጭብጥ (grand theme) ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው:: ከመጽሐፉ መጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዋናው ገፀባሕርይ እና መጽሐፉ ሊገልጠው የፈለገው ማንነት ነው:: ሰው መጽሐፉን አንብቦ ወደ ኢየሱስ ካልመጣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቱ ግቡን አልመታም ማለት ነው:: (ዮሐ 5:39)
8. የዓለምን ጅማሬ፣ ያሳለፈችውን ታሪክ፣ አሁን እያሳለፈች ያለውን ሁኔታ ገና ሊመጣ ያለውን የዓለምን ታሪክ፣ የዓለምን ፍፃሜ፣ የሚመጣውን አዲስ ሰማይና ምድር መግለጥ የቻለ መጽሐፍም መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው:: (ኤፌ 1:9)

## 3. <u>የመጽሐፍ ቅዱስ ዋነኛ ዓላማዎች</u>

1. ሰዎች ወደእግዚአብሔር የሚቀርቡበትንና፣ የሚታረቁበትን፣ የሚድኑበትን መንገድ ማሳየት (ዮሐ 14:6 ዕብ 7:25)
2. ከእግዚአብሔር ጋር የታረቁ እነዚህ ደግሞ እንዴት ባለ ሥጋዊና መንፈሳዊ ኑሮ መኖር እንደሚገባቸው መመሪያና፣ ምክር መስጠት (2ጢሞ 3:14-17)

## 4. <u>የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሞች</u>

መጽሐፍ ቅዱስ የተየለሌ የሌለው ጥቅሞችን ለሰዎች ልጆች ይሰጣል:: ግለሰቦችን፣ ሕብረተሰቦችን፣ አገራትን አስደናቂ ለውጦች እንዲያመጡ ያደረገ ታላቅ መጽሐፍ ነው:: ምክንያቱም ቃሉ ሕይወት ያለው (The living word) እና የሚሠራ (Operative) ስለሆነ ነው:: (ዕብ 4:12) የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት ከሚሰጠው መንፈሳዊና ሥጋዊ ጥቅሞች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው::

1. ከእግዚአብሔር ዳግመኛ ለመወለድ (1ጴጥ 1:23-25, ያዕ 1:18)
2. በማንኛውም ጉዳይ ላይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ (ሐዋ 17:11)
3. መንገዳችን እንዲከናወንልን (ኢያ 1:7-9, መዝ 1:2-3)
4. እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት (1ሳሙ 15:22)
5. ኃጢአትን በማድረግ እግዚአብሔርን ከመበደል ለመጠበቅ (መዝ119:11, ዮሐ8:31-35)
6. መንገዳችንን ለማንጻት (መዝ 119:9 , 105)
7. የልብ ደስታ እና ሀሴት ለማግኘት (መዝ 119 62, ኤር 15:16, ኢሳ 66:5)
8. አስተዋይ ለመሆን (መዝ 119:97 -104, 130)
9. እግዚአብሔርን ለመፍራት እና ክብር ለመስጠት (ምሳ 2:1-5)
10. በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት (ምሳ1:23 ,ሐዋ10:44)
11. እንደ እግዚአብሔር ሀሳብ በመፀለይ ፀሎታችን መልስ እንዲያገኝ (ምሳ15:7,28:9,ዮሐ15:7)
12. በአምላክ ፊት ለመታጠብና ለመንፃት (ኤፌ 5:26, ዮሐ 15:3)
13. ከሰዎች ወግና ሥርዓት ነፃ ለመውጣት (ማር 7:6-13, ማቴ 15:1-14)
14. መንፈሳችንን እየመገብን በመንፈስ ለማደግ (ሉቃ 4:4 ,1ጴጥ2:2 ,ዕብ 5:12-14)
15. በሕይወታችን በማገጥሙን መከራና ፈተና ጊዜ በፅናት ለመቆም እና ታላቅን አወዳደቅ ላለመውደቅ (ማቴ 7:24-27)
16. ዲያብሎስን ለመዋጋት እና ለማሸነፍ (ማቴ4:1-11 ኤፌ 6:17)
17. ከስህተት ለመጠበቅ (ማቴ 22:29)
18. ከአገልጋዮች ስህተት ራስን ለመጠበቅ (1ነገ 13:1 -32, 2 ዜና 18:21)
19. በእግዚአብሔር የተናቅን እንዳንሆን (1 ሳሙ 15:23)
20. በእግዚአብሔር የተጠላን እንዳንሆን እና በእርሱ ለመወደድ (ሆሴ 4:6)
21. ከሚመጣው የእግዚአብሔር ፍርድ ለማምለጥ (2ነገ 22:8 -20, ምሳ 1:24-32)
22. የተረጋጋ ሕይወት ለመምራት (ምሳ 1:33)
23. ብፁዕ ለመባል ማለትም በእግዚአብሐር ፊት ምስጉን ለመሆን (ራዕ 1:3)
24. ለሚጠይቁን ሁሉ መልስ ለመስጠት (1ጴጥ3:15, ምሳ 22:17-21)
25. ሌሎች ብዙ ጥቅሞች (መዝ 19:7-11) ወዘተ

## 5. መጽሐፍ ቅዱስ የተጠራባቸው ስያሜዎች

1. መጽሐፍ (መጻሕፍት) /Scriptures/ማር 15:28, ሉቃ 24 :27, ዮሐ5 :39, ሮሜ15:4 "መጽሐፉ" /The Scripture/ የሚለው ቃል መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል ሲሆን ለሌሎች መጽሐፍት አለመዋሉ መጽሐፍ ቅዱስን ልዩ ያደርገዋል:: (ዮሐ 10:35)
2. ብሉይ (አሮጌ) ኪዳንና አዲስ ኪዳን (2ቆሮ 3:6,14)
3. ፊተኛውና ኋለኛው ኪዳን (ዕብ 8:7, 13)
4. ሕይወት ያላቸው /የእግዚአብሔር/ ቃላት (ሐዋ 7:38, ሮሜ3:2, ዕብ 5:12)
5. የመንፈስ ሰይፍ (ኤፌ 6:17)
6. የእግዚአብሔር መጽሐፍ (ኢሳ 34:16)
7. የእግዚአብሔር ቃል (ቈላ 3:16, ማር7:13, ሮሜ 10:17)
8. በመዝሙር (119) ውስጥ ብቻ መጽሐፍ ቅዱስ ከ6 ባላነሱ የተለያዩ ስያሜዎች ተጠርቷል:: (ከመዝሙር (19) ጋር አነፃጽር

   1) ሕግ 2) ምስክር 3) ትዕዛዝ 4) ሥርዓት 5) ቃል 6) ፍርድ

*ማስታወሻ፦ አይሁድ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ሲጠሩ በሦስት በመክፈል ሲሆን በምህፃር ቃል "ታናክ" ይሏቸዋል::*

*ይህም ማለት ታ- ተውራት (ሕግ)*

*ና- ነቢም (ነቢያት)*

*ክ- ኬቱቢም (መዝሙራትና መጻሕፍት) ናቸው::*

*በአንድ ላይም ሲጠሯቸው በሕግ፣ በነቢያትና፣ በመዝሙራት መጻሕፍት እያሉ ነበር፣ ጌታም የተጠቀመው በዚሁ አጠራር ነበር (ሉቃ 24:44, ቁ.27)*

## 6. መጽሐፍ ቅዱስ የተመሰለባቸው ምሳሌዎች

1. መብራት እና ብርሃን (መዝ 119:105)



2. ድንጋዩን የሚያደቅቅ መዶሻ (ኤር 23:29)



3. ምግብ (ኤር 15:16, ኢዮ 23:12, ኢ.መ.ት, ማቴ 4:4, ዕብ 5:14)



4. ወተት (1ጴጥ 2:2)



5. **ማርና ወለላ (መዝ 119:103) (ራዕ 10:9-10)**



6. **እሳት (ኤር 23:29)**



7. **ውኃ (ኤፌ 5:26, ዮሐ**15:3)



8. **መስተዋት (ያዕ 1:23-25)**



9. **ሰይፍ (ኤፌ 6:17)**



10. **ዘር (ሉቃ 8:5-15)**



## 7. <u>በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጠው አጠቃላይ የሆነ የእግዚአብሔር ተደጋጋሚ ፍላጎት</u>

1. **እርሱ ብቻውን አምላካችን ለመሆን መፈለጉ፣**
2. **እኛ የእርሱ ብቻ ሕዝብ እንድንሆን መፈለጉ እና**
3. **በመጨረሻም እርሱ ራሱ በመካከላችን ለመኖር መፈለጉ ነው።**

**"እኔ አምላካችሁ እሆናለሁ፣ እናንተም ሕዝቤ ትሆናላችሁ፣ እኔም በመካከላችሁ አድራለሁ።"** (**ዘሌ 21:12, ራዕ** 21:3)

## 8. የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ

### 1.1. የተፃፈበት ዘመን

መጽሐፍ ቅዱስ ተፅፎ ለማለቅ የፈጀው ጊዜ 1600 ዓመታት ያህል ይሆናል ይህም ማለት የመጀመሪያዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች (የሕግ መጽሐፍት) መጻፍ የጀመሩት ከ.ክ.ል በፊት 1400-1500 ዓ.ዓ ገደማ ሲሆን የመጨረሻው የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል (የዮሐንስ ራዕይ) የተፃፈው ደግሞ ከ96-100 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ነበረ፡፡ ይህ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስን ተፅፎ ለማለቅ እጅግ በጣም ረዥም ዘመን የፈጀ ብቸኛው መጽሐፍ አድርጎታል፡፡

**ብሉይ ኪዳን**

**ብሉይ ኪዳን**፡- መጻፍ የጀመረው ከክ.ል.በ ከ1400-1500 ዓ.ዓ. ባለው ጊዜ ውስጥ ሲሆን፣ የመጨረሻው የብሉይ ኪዳን ነቢይና ፀሐፊ ደግሞ ሚልኪያስ ነበረ፡፡ ሚልኪያስ የትንቢቱን መጽሐፍ የፃፈው በ425 ቅድመ ክርስቶስ (ዓ.ዓ.) ሲሆን ከትንቢተ ሚልኪያስ በኋላ እግዚአብሔር በየትኛውም ነቢይ በኩል መልዕክትን አላመጣም፣ መጽሐፍም አላፃፈም ነበር፡፡ ስለሆነም ከሚልኪያስ እስከ ክርስቶስ መምጣት ድረስ ያለው የ400 ዓመታት ጊዜ "**የዝምታ ዘመን**" ተብሎ ይጠራል፡፡

**የዝምታ ዘመን (The Period of Silency)**

ይህ ዘመን ነቢዩ ሚልኪያስ የመጨረሻውን የብሉይ ኪዳን መፅሐፍ ፅፎ ካጠናቀቀ በኋላ እስከምጥምቁ ዮሐንስ መነሳት ድረስ የነበረውን የ400 ዐመታት ጊዜ የሚያሳይ ነው በዚህ ዘመን ውስጥ እግዚአብሔር ከቶ ለየትኛውም ሰው ትንቢትን ወይም መጽሐፍን አልሰጠም፡፡ ይህ ዘመንም ከብሉይ ኪዳን ወደ አዲስ ኪዳን የመሸጋገሪያ ጊዜ ነበር፡፡

**ማስታወሻ፡-** 1. በካቶሊክ እና በኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከጊዜ በኋላ ተቀባይነት ያገኙት የአዋልድ (Deutrocanonical) መጽሐፍት መፃፍ የጀመሩት በዚህ የዝምታ ዘመን አጋማሽ ላይ በ200 ዓ.ዓ. ቅድመ ክርስቶስ ላይ ሲሆን ተጽፈው ያለቁት ደግሞ ከ.ክ.ል በኋላ ከ100-200 ዓ.ም. ገደማ ነበር፡፡ ይህ የሚያሳየው መጻሕፍቱ እንደሌሎቹ መጻሕፍት በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት ያልተፃፉና፣ እንዲሁም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ቢባሉም እንኳ በአዲስ ኪዳን ዘመንም የተፃፉ ስላሉባቸው የዘመናት እና የታሪክ ግጭት ሊፈጥሩ ችለዋል፡፡

2. ኪዳን፡- የሚለው ቃል ውል፣ ስምምነት የሚለውን ሐሳብ የሚገልጥ ሲሆን በግሪክ ቋንቋ ሁለት ዓይነት ኪዳኖች ይኖራሉ፡፡ እነዚህም "ሱናቲኬ" በሁለት እኩልነት ባላቸው ወገኖች የሚፈጸም ኪዳን ሲሆን "ዳያቲኬ" ደግሞ እኩል ባልሆኑ ሁለት ክፍሎች መካከል የሚደረግ ኪዳን ነው፡፡ በመሆኑም የመጽሐፍ ቅዱስ ኪዳኖች "ዳያቲኬ" ናቸው፡፡

## አዲስ ኪዳን

የመጀመሪያዎቹ የአዲስ ኪዳን መፃሕፍት (የያዕቆብ መልዕክት እና ወደ ገላትያ ሰዎች) መፃፍ የጀመሩት ከ45-50 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ሲሆን የመጨረሻው የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ደግሞ ከ96-100 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ተጽፏል::




## 9. መጽሐፍ ቅዱስን ለማጻፍ አምላክ የተጠቀመባቸው ሰዎች

እግዚአብሔር ይህን የእርሱን ሀሳብ የተሞላ መጽሐፍ ቅዱስ ለማጻፍ ከ40 ያላነሱ ሰዎችን ተጠቅሟል:: በአንዳንድ መጻሕፍት ላይ ከአንድ የሚበልጡ ፀሐፊዎች ተሳትፈዋል::

**ለምሳሌ:-** ሀ. ዘዳግም መጽሐፍን ሙሴ ቢጽፈውም የመጨረሻውን ክፍል ግን የፃፈው እርሱ አይደለም (ዘዳ 34:5-8)

ለ. መዝሙር መጽሐፍ ላይ የተሳተፉ ፀሐፊዎች (ከዳዊት ሌላ)
አሳፍ (73)፣ የቆሬ ልጆች (84) ፣ ኤማን (88)፣ ኤታን (89)፣ ሙሴ (90)

ሐ. መጽሐፈ ምሳሌ ላይ የተሳተፉ (ከሰለሞን ሌላ)
አጉር (ምሳ 30)፣ ልሙኤል (ምሳ 31)

መ. ትንቢተ ኤርምያስ ላይ የተሳተፉ
ባሮክ (ኤር 36)

አምላክ መጽሐፍ ቅዱስን ለማፃፍ የተጠቀመባቸው ሰዎች በሙሉ እጅግ በጣም በተራራቀ ዘመን እና ሁኔታ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ እንዲሁም የተለያየ ዓይነት የኑሮ ደረጃ ላይ የነበሩና በዕውቀት ደረጃም ፈጽሞ ልዩነት የነበራቸው ነበሩ:: ሆኖም ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ እየተነዱ በመፃፋቸው ምክንያት አንድ ዓይነት ሀሳብና ግብ ያለውን መጽሐፍ ሊጽፉ ችለዋል:: (2ጴጥ 1:21::)

1. **<u>የዘመን ልዩነት</u>:-** ለምሳሌ ያህል በመጀመሪያው ፀሐፊ በሙሴና በመጨረሻው ፀሐፊ በዮሐንስ መካከል ከ1600 ዓመታት ያላነሰ የዘመን ልዩነት ነበር:: ሁለቱ ሰዎች በነበሩባቸው ረዥም የዘመናት ርቀት የተነሳ የአመለካከት፣ የባህል፣ የፖለቲካ፣ የኃይማኖት፣ የቴክኖሎጂ ሰፊ ልዩነት ቢኖርም ጽሁፎቻቸው ግን ፈጽሞ አንዱ ከአንዱ የተስማሙ ናቸው::

2. **<u>የኑሮ ደረጃ</u>:-** ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የነበሩ ሰዎችን ተጠቅሟል::
ለምሳሌ:- አሞፅ - ላም ጠባቂና ወርካ ለቃሚ (አሞ 7:14)
ጴጥሮስ እና ዮሐንስ - አሳ አጥማጅ የነበሩ (ማቴ 4:18-22)

:- ከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የነበሩትንም ሰዎች ተጠቅሟል
*ዳዊት - ንጉሥ*
*ሰለሞን - ንጉሥ*
*ሙሴ - መስፍን የነበረ::*

3. **<u>የዕውቀት ደረጃ</u>:- እጅግ በጣም የተማሩ**
ሙሴ የግብጽን ጥበብ ሁሉ የተማረ (ሐዋ 7:22)
ጳውሎስ ከገማልያል የተማረ (ሐዋ 22:3)

:- **ያልተማሩ ሰዎች**
ጴጥሮስና ዮሐንስ - (ሐዋ 4:13)

## 10. <u>መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት ተፃፈ?</u>

**<u>የጽሕፈት መሣርያዎች</u>**

መጽሐፍ ቅዱስ ዛሬ በእጃችን እንደምንይዘው ዓይነት ቅርጽ እና መልክ አልነበረውም:: ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ በተፃፈበት ዘመን እንደዛሬው ዓይነት የጽሕፈት መሣርያዎች (ወረቀት፣ ማተሚያ ማሽን ወዘተ...) አልነበሩምና ነው::

*<u>**ማስታወሻ**</u>- ወረቀት ለመጀመሪያ ጊዜ የተሠራው ከክ.ል. በኋላ በ2ኛ መቶ ክፍለ ዘመን በቻይናዎች አማካይነት ሲሆን በኋላም በ8ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአረቦችና በ10ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአውሮፖዎች ሊታወቅ ችሏል:: የጽህፈት ማሽን ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሠራው በ1450 ዓ.ም. በጀርመናዊው ጉተንበርግ አማካኝነት ነበር::*

በመሆኑም መጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያ የተፃፈው በዘመኑ በነበሩት ጥንታውያን የጽሕፈት መሳሪያዎች ነበር::

**ብራና (Purchment)** - እንደወረቀት የተጠቀሙበት ዋነኛ የጽሕፈት ዕቃ ብራና ነበር፡፡ ብራና ከፍየል፣ ከበግ ከመሳሰሉት እንስሳት ቆዳ የሚሠራ እንደወረቀት ለመፃፍያነት የሚያገለግል ነው፡፡ መጽሐፉ ሰፊ ምንባብ የሚይዝ ከሆነ ብራናዎቹ ተቀጣጥለው ይሠሩና ጫፍና ጫፋቸው ላይ በሚደረጉት መጠቅለያዎች ይጠቀለላሉ፡፡ አብዛኛዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተፃፉትም በብራና ላይ ነበር፡፡

***ለምሳሌ፡-*** - *የሙሴ 5ቱ ጥቅልሎች (Pentateuch)*
- *ትንቢተ ኢሳይያስ ወዘተ...*



**ጥንታዊው የመጽሐፍ ጥቅልል**

እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ አሁን እኛችን ላይ እንደምናየው በዘመናዊ መልኩ አንድ ላይ ከመጠረዙ በፊት እያንዳቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ለየብቻቸው የተጠቀለሉ ነበሩ፡፡ ማንበብ የሚፈልግም ሰው አንዱን ጥቅልል ብቻ አንስቶ በመተርተር ያነብና ከጨረሰም በኋላ ጠቅልሎ ማስቀመጥ ነበረበት፡፡

***ለምሳሌ፡-*** *ጌታ ኢየሱስ በምኩራብ ሲያነብ ሉቃ 4፡16-20 ተመልከት*
*ተጨማሪ፡- ዕብ 10፡7 2ጢሞ 4፡13*

**ደንገል (Papyrus)** - የደንገል ተክል እንደብራናው ሁሉ ለጽሕፈት *ሥራ* የዋለ የወረቀት ዓይነት ነበር፡፡ በተለይ ደግሞ ትንንሽ ይዘት ያላቸው መልዕክቶችና ጽሁፎች የተፃፉት ከደንገል ተክል በሚዘጋጁት ወረቀቶች ላይ ነበር፡፡

***ለምሳሌ፡-*** *የጴጥሮስ፣ የያዕቆብና የዮሐንስ መልዕክቶች ወዘተ... በደንገል ወረቀት ላይ ተጽፈዋል፡፡*

***ማስታወሻ፡-*** *የደንገል ተክል በአገራችን ለታንኳ መስሪያነት ያገለግላል፡፡*

በእነዚህ የወረቀት ዓይነቶች ላይ ከቅጠላ ቅጠሎች፣ ከጥላሸት ወዘተ... ከመሳሰሉት ነገሮች በሚቀመሙ ቀለማት ከመቃ በተሰሩ ብዕሮች አማካይነት ይጽፉ ነበር፡፡

***የመፃፍያ ቋንቋዎች***

በዋነኛነት በመፃፍያ ቋንቋነት ያገለገሉት የዕብራይስጥ (Hebrew) እና የግሪክ ቋንቋዎች ናቸው:: የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተፃፉት በዕብራይስጥ ቋንቋ ሲሆን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ደግሞ በዘመኑ የሳይንስና የፍልስፍና ቋንቋ በነበረው ግሪክ ነበር::

***ማስታወሻ***:- *በአንዳንድ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ የተወሰኑ ጥቂት ቁጥሮች በአረማይክ ቋንቋ ተጽፈዋል::*

***ምዕራፍና ቁጥሮች***

የመጽሐፍ ቅዱስ ፀሐፊዎች በመንፈስ እየተነዱ በሚጽፉበት ጊዜ ፈጽሞ ምዕራፍና ቁጥር አይጠቀሙም ነበር:: ስለዚህ መጽሐፋቸው ምንም ክፍልፋይ የሌለው ወጥ እና ተከታታይ ነበር:: በመሆኑም ጥቅስ መጥቀስ የፈለገ ሰው የመጽሐፉን ስም በመጥቀስ ብቻ "በእከሌ መጽሐፍ እንደተፃፈ" ይላል እንጂ በዚህ ምዕራፍ እና ቁጥር ብሎ አይጠቅስም ነበር::

በኋላ ግን ቤተክርስቲያን ለአጠቃቀም ይመቻት ዘንድ በማሰብ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1228 ዓ.ም. በእንግሊዝ አገር በምዕራፍ ብቻ ተከፈለ:: በዚህ ሁኔታ ከ300 ዓመታት በላይ በምዕራፍ ተከፍሎ የቆየ ሲሆን አጠቃቀሙ የበለጠ ቀላል ይሆን ዘንድ በ1551 ዓ.ም. በፈረንሳይ አገር በቁጥሮች ተከፋፈለ:: እንግዲህ ከዚያ ዘመን በፊት በ1500 ዓመታት በላይ የነበሩት ክርስቲያኖች ምዕራፍና ቁጥር የሚባል ፈጽሞ አያውቁም ነበር ማለት ነው::

## 11. <u>የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና (Canonicity)</u>

ቀኖና ከግሪኩ "ካኖን" የተወሰደ ቃል ሲሆን ትርጉሙ በዘመኑ ለመለኪያነት ወይም ለመስፈሪያነት እንደሜትር የሚጠቀሙበት ከሸንበቆ የሚሠራ በትር ነበር:: የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና ስንል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን 66 መፃሕፍት በዚያን ዘመን ከነበሩ ብዙ መንፈሳዊ ከሚመስሉ መፃሕፍት ለመለየት የቤተክርስቲያን ዋኖችና የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን (Scholars) የተጠቀሟቸውን መስፈርቶች ለማሳየት ነው::

### 1.1. <u>የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና ለምን አስፈለገ?</u>

1. የሐሰት መጽሐፍቶች እና መልዕክቶች በሰፊው እየተሰራጩ ስለመጡ አማኞች የራሳቸውን እውነተኛ የመጽሐፍት ክፍሎች ማወቅ ስለነበረባቸው
2. ሁሉም ትውልድ የተጠናቀቀና ፍጹም የሆነን የእግዚአብሔር ቃል እንዲያገኝ
3. በጽሑፍ የሰፈረ እና በመንፈሳዊ ጉዳዮች ሁሉ ላይ ሙሉ ስልጣን ያለው (Authoritative) የእግዚአብሔር ቃል እንዲኖር በማስፈለጉ
4. ጠላት መጽሐፍቶቹን ለማጥፋት በተደጋጋሚ እንዲቃጠሉ ስላደረገ መጽሐፍቶቹን ሰብስቦ መጠበቅ አስፈላጊ ስለነበረ ነው::

***ለምሳሌ***:- *ንጉሥ ዲዮቅልጥያኖስ ክርስትናን ለማጥፋት በሚል የተጠቀመው አንዱ ዘዴ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን እየሰበሰበ ማቃጠል ነበር::*

## 2.2. <u>የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና መስፈርቶች</u>

ቤተክርስቲያን የመጽሐፍቱን ዓይነትና ብዛት ለመወሰን የተለያዩ መስፈርቶችን ተጠቅማለች፡፡

1. **<u>እስትንፋሰ እግዚአብሔር (Inspiration)</u>:-** መጽሐፉ በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት ለመፃፉ፣ በይዘቱ፣ በጭብጡ በመልእክቱ፣ በጥቅሙ ወዘተ መረጃ ማግኘት (2ጴጥ 1:21)

ሀ. **<u>ውስጣዊ ምሥክርነት</u>**:- በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙትን ስለመጽሐፉ ምንነት፣ ስለፀሐፊው ማንነት የሚገልጹ መረጃዎችንና የእግዚአብሔርንና የነቢያቱን ምስክርነት መፈለግ (ዘዳ 31:24-26, ኢያሱ 1:8, መሳ 3:4, ኤር 36, ነህ 8:1-8, ዳን 9:2, ዘካ 7:12 የጳውሎስ መልዕክቶች በሙሉ, 2ጴጥ 3:15 ወዘተ...)

ለ. **<u>ውጫዊ ምሥክርነት</u>**:- የሥነ ጽሁፍ ይዘቱ፣ የተፅእኖውና የመለወጥ ብቃቱ፣ የትምህርት ይዘቱ ታላቅነትና ጥልቀት፣ የማያዳላው ሥልጣኑ፣ ወዘተ... (እስትንፋሰ እግዚአብሔር የሚለውን ተመልከት)

2. **<u>የአዲስ ኪዳን ምስክርነት (Apostolicity)</u>:-** ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስና ሐዋርያት በመረጃነት የጠቀሷቸውና ዕውቅና የሰጧቸው መጽሐፍት በሙሉ ተቀባይነት አግኝተዋል፡፡
3. **<u>በአይሁድ ዘንድ ያላቸው ተቀባይነት</u>**:- ለአዲስ ኪዳንመጻሕፍት የተቀመጡት መስፈርቶች እንዳሉ ሆነው በዋነኛነት ግን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተሰጡት ለአይሁድ እንደመሆኑ መጠን እነርሱ የተቀበሏቸውን መጻሕፍት ሁሉ መቀበል ግዴታ ነው፡፡ በመሆኑም አምላክ ለእነርሱ በቀጥታ የሰጣቸውን እና በእነርሱም ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ዛሬ በእኛ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት ሰላሳ ዘጠኝ መጽሐፍት ናቸው፡፡
4. **<u>የመንፈሳዊ ተፅእኖው ብቃት (Recognition)</u>:-** በተጠቃሚው ላይ የሚያመጣው የመንፈሳዊ ሕይወት በጎ ተፅዕኖ እና ለአማኙ የሚሠጠው ሁለንተናዊ አገልግሎት (ለሥጋ፣ መንፈስ፣ ነፍሱ) የሚሰጠው ጠቀሜታ 2ነገሥ 22:8 - 23:3, ነህ 8
5. **<u>የተስማሚነት መስፈርት (Consistency)</u>:-** በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት ሌሎች መጽሐፍት ጋር ያለምንም ተቃርኖ መስማማት መቻል አለባቸው፡፡

## 3.3. <u>የተለያዩ ውሳኔዎች</u>

ጥንታዊቷ ቤተክርስቲያን ተደበላልቀው የነበሩትን መጽሐፍቶች በማጣራት በአራት ከፋፈለቻቸው፡፡ እነዚህም፡-

1. ስምምነት ያላቸው /Homologoumena/ እነዚህም አሁን በመደበኛው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን በብዛት ያጠቃልላሉ
2. ስምምነት የሌላቸው /Antilegomena/ በይዘታቸው ከሌሎቹ መጽሐፍት ለየት ያሉ

3. **የሐሰት ጽሑፎች** /Pseudepigrapha/ **(የአዋልድ መጽሐፍት የሚለውን ተመልከት)**
4. **ድብቅ ጽሑፎች** /Apocrypha/ **ናቸው:: (የአዋልድ መጽሐፍት የሚለውን ተመልከት)**

በመሆኑም ጥንታውያን የቤተክርስቲያን አባቶች ዛሬ በኦርቶዶክስና በካቶሊክ ተቀባይነት ያገኙትን የአዋልድ መጽሐፍት አይቀበሏቸውም ነበር::

*__ለምሳሌ__:- አትናቴዎስ:- በ367 ዓ.ም. በፋሲካ በዓል የቡራኬ መልዕክቱ ሲጽፍ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት 27 ብቻ መሆናቸውን ገፈ:: እንዲሁም የአዋልድን መጽሐፍት ፈጽሞ አልተቀበለም ነበር::*

*አውሳብዮስ:- የአዋልድ መጽሐፍትን ፈጽሞ አይቀበልም::*

በኋላ ግን በ393 በ "ሂፖ" የተሰበሰበው ጉባኤ የአፖክሪፋን መጽሐፍት አጸደቃቸው:: በኋላም በ405 ዓ.ም. "ጀሮም" /Jerome/ መጽሐፍ ቅዱስን በላቲን ሲተረጉም "በፖፕ ደማሱስ" ትዕዛዝ መጽሐፎቹን ጨምሯቸዋል:: ጥንታዊውን የእንግሊዝኛ ትርጉም "ዋይክሊፍ" ሲጽፍ ግን እነዚህን የአፖክሪፋ መጽሐፍት አስወጥቷቸዋል:: በመጨረሻም ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን በ"ትሬንት" ባደረገችው ተከታታይ ስብሰባ (ከ1545-64) እና በ"ቫቲካን ጉባኤ" (1870) የአፖክሪፋን መጽሐፍት ተቀብላቸዋለች:: በፕሮቴስታንቶች በኩል ግን በ1647 በእንግሊዝ ዌስት ሚኒስቴር የእምነት መግለጫ ላይ ሁሉም ዓይነት የአዋልድ መጽሐፍት ውድቅ ተደርገዋል::

## 12. <u>የአዋልድ መጽሐፍት (Deutrocanonicals)</u>

### 1.1. <u>የአዋልድ መጽሐፍ ምንድናቸው?</u>

በመደበኛወ መጽሐፍ ቅዱስ ያሉት መጻሕፍት ብዛት 66 ሲሆን በካቶሊካዊትና በኦርቶዶክስ አብያተክርስቲያናት ደግሞ እንደመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ተደርገው የተጨመሩ ሌሎች ጽሑፎች ናቸው:: ጌታ ኢየሱስ ፈጽሞ ከእነዚህ መጽሐፍት ጠቅሶ የማያውቅ ሲሆን ከላይ በተጠቀሱት ቤተእምነቶች ግን ተቀባይነትን አግኝተዋል::

**የአዋልድ (Deutro Canonical) መጽሐፍት በዋነኛነት በሁለት የሚከፈሉ ናቸው**

1. አፖክሪፋ (Apocrypha)
2. ሲውዶፒግራፋ (Pseudepigrapha) በመባል ይታወቃሉ::

1. **<u>አፖክሪፋ (</u>**<u>Apocrypha</u>**):- "ስውር" ወይም "ድብቅ" ማለት ነው::** ምናልባትም እንደመጽሐፍ ቅዱስ አካል በአብዛኛው ስለማይታዩና አሁንም ግን ተጠብቀው ያሉ በመሆኑ የተሰጣቸው ስያሜ ነው:: የአፓክሪፋ መጽሐፍት 15 ያህል ሲሆኑ ሁሉም የተፃፉት በአይሁድ ፀሐፍት አማካኝነት ነው:: የተፃፉበትም ጊዜ ከ200 ቅድመ ክርስቶስ እስከ 100 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ነበር:: ዋናዎቹ (Original) ጽሁፎች በዕብራይስጥ፣ አረማይክና ግሪክ ቋንቋዎች የተፃፉ ሲሆን እስከአሁንም ድረስ በግሪክ፣ በላቲን፣ በኢትዮጵያ፣ በግብጽ፣ በአረብ፣ በሶሪያና በአርመንያ ተጠብቀው አሉ:: መጽሐፍቶቹ በይዘታቸው በስድስት ይከፈላሉ:: በ250 ቅ.ክ. ወደ ግሪክ በተተረጐመው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ባይገቡም ቀስ በቀስ ግን በሌሎቹ ግልባጮች ላይ አንድ በአንድ እየተጨመሩ የመጡ ነበሩ:: ነገር ግን የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ከአምላክ በተሰጣቸው አይሁዶች ዘንድ ፈጽሞ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አካል ተደርገው አልተቆጠሩም::

| የመጽሐፉ ይዘት | | የመጽሐፉ ዓይነት (ስም) | የተፃፈበት ዘመን |
|---|---|---|---|
| ትምህርታዊ | 1 | መጽሐፈ ጥበብ | 30 ቅ.ክ. |
| | 2 | መጽሐፈ ሲራክ | 132 ቅ.ክ. |
| ኃይማኖታዊ | 3 | ጦቢት | 200 ቅ.ክ. |
| የፍቅር ታሪክ | 4 | ዮዲት | 150 ቅ.ክ. |
| ታሪካዊ | 5 | ዕዝራ (1ኛ) | 150 - 100 ቅ.ክ. |
| | 6 | 1ኛ መቃብያን | 110 ቅ.ክ. |
| | 7 | 2ኛ መቃብያን | 110 - 70 ቅ.ክ. |
| ትንቢታዊ | 8 | ባሮክ | 150 - 50 ቅ.ክ. |
| | 9 | የኤርሚያስ መልዕክት | 300 - 100 ቅ.ክ. |
| | 10 | ዕዝራ (2ኛ) | 100 ዓ.ም. |
| ትረካ | 11 | ተረፈ አስቴር | 140 - 130 ቅ.ክ. |
| | 12 | ፀሎተ ሠለስቱ ደቂቅ | 2ኛ/1ኛ ክ/ዘ ቅ.ክ. |
| | 13 | ሶስና | 2ኛ/1ኛ ክ/ዘ ቅ.ክ. |
| | 14 | ቤልና ድራጎኑ (ዳንኤል) | 100 ቅ.ክ. |
| | 15 | ፀሎተ ምናሴ | 2ኛ/1ኛ ክ/ዘ ቅ.ክ. |

2. **<u>ሲውዶፒግራፋ (Pseudepigrapha)</u>:-** እነዚህ መጽሐፍት የሚታወቁበት ባህሪያቸው ደግሞ ፈጽሞ የፀሐፊዎቻቸው ማንነትና የተፃፉበትን ዘመን በቅጡ ማወቅ አለመቻሉ ነው፡፡ ቢሆንም በጠቅላላ መልኩ ግን የተፃፉት ከ200 ቅ.ክ. እስከ 200 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ወስጥ ነበር፡፡ በአምስት ዓይነት ይዘት ይከፈላሉ:-

| የመጽሐፉ ይዘት | | የመጽሐፉ ዓይነት (ስም) |
|---|---|---|
| ትረካ | 1 | መጽሐፈ ኢዮቤልዩ |
| | 2 | የአርስጢያስ መልዕክት |
| | 3 | መጽሐፈ አዳም ወሔዋን |
| | 4 | የኢሳያስ ሰማዕትነት |
| ራዕይ | 5 | መጽሐፈ ሄኖክ |
| | 6 | የ12ቱ አባቶች ኪዳን |
| | 7 | ዜና ነቢያት እንስት |
| | 8 | መጽሐፈ ሙሴ |
| | 9 | መጽሐፈ ባሮክ |
| ትምህርታዊ | 10 | መቃብያን (1ኛ) |
| | 11 | መቃብያን (2ኛ) |
| | 12 | የአሂቃር ታሪክ |
| ቅኔያዊ | 13 | መዝሙረ ሰሎሞን |
| | 14 | መዝሙር 151 |
| ታሪካዊ | 15 | የሳዶቃውያን ሥራ |

ምንም እንኳ እነዚህ መጽሐፍት በቀኖናዊ መጽሐፍት ውስጥ ባይካተቱና በአይሁድም ተቀባይነት የሌላቸው ቢሆኑም መጽሐፍቱ ግን በወቅቱ ብዙ ሥርጭት የነበራቸውና በአይሁዶችም በክርስቲያኖችም ዘንድ የታወቁ ነበር፡፡ ለምሳሌ ያህል ይሁዳ በፃፈው መልዕክት ውስጥ ከመጽሐፈ ሄኖክ የተጠቀሱ ምንባቦችን እናገኛለን፡፡ ይሁዳ 9,14-15

## 2.2. የአዋልድ መጽሐፍት ችግሮች

1. **የፀሐፊዎቹ ማንነት በውል አለመታወቅ፡-** ሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሁፎችን ማን እንደፃፋቸው ለማወቅ ብዙም አስቸጋሪ አይደሉም፡፡ የአዋልድ መጽሐፍት ግን ፈጽሞ ፀሐፊያቸው አይታወቅም፡፡ እንደውም ባለታሪኩ በሕይወት በሌለበት ዘመን የተፃፉት ይበዛሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ተረፈ ኤርምያስ፣ ተረፈ ዳንኤል
2. **የዘመን አገላለጽ-** በተለይ ደግሞ የሲውዶፒግራፋ መጽሐፍት የተፃፉበትን ወቅት ማወቅ አዳጋች ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የአዋልድ መጽሐፍት በምንባቦቻቸው ውስጥ የጊዜ ወይም የዘመናት አጠቃቀም ስህተት ይገኝባቸዋል፡፡ **ለምሳሌ፡-** ኢየሱስ ሳይወለድ "የአብ ልጅ ኢየሱስ" ብሎ መግለጽ መጽሐፉ በነቢዩ በራሱ ሳይሆን ጌታ ከተወለደ በኋላ ለመፃፉ ማረጋገጫ ነው፡፡ ተ.ኤር 11:46
3. **የታሪክ ግጭት፡-** የአዋልድ መጽሐፍትን ዕውቅና በመስጠት ከመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ብንጨምራቸው ከዋናው መጽሐፍ ጋር ብዙ የታሪክ ግጭቶችን ይፈጥራሉ፡፡
   ለምሳሌ፡- **በዋናው፡-** ዳንኤል ፀሎት መፀለይ ባለማቆሙ በአንበሶች ጉድጓድ ተጣለ፡፡ (ት.ዳን 6)
   **በአዋልድ፡-** ዳንኤል ዘንዶ በመግደሉ ጉድጓድ ተጣለ (ተ.ዳን 13:26)

   **በዋናው፡-** ዳንኤል አንድ ቀን ብቻ በአንበሶች ጉድጓድ ሲያድር (ት.ዳን 6:17-23)
   **በአዋልድ፡-**ዳንኤል ለሰባት ቀናት በአንበሶች ጉድጓድ ውስጥ ቆየ (ተ.ዳን 13:39)
4. **የአስተምህሮ (Doctrine) ግጭት፡-**
   **በዋናው፡-**ገንዘብ መውደድ የጥፋት ሁሉ ስር ነው፡፡ ኑሮዬ ይበቃኛል... (1ጢሞ 6:8-10)
   **በአዋልድ፡-** ገንዘብ በቃኝ አትበል (መጽ. ሲራክ 11:24, 5:1)

   **በዋናው፡-** ጉልበት ሁሉ ለኢየሱስ ስም ይንበረከካል ... (ፊል 2:9-11)
   **በአዋልድ፡-**ወደ ጫጉላ ቤት በገባህ ጊዜ የደቀቀ ዕጣን፣ ከዚህም ዓሳ፣ ከልቡ ከጉበቱ አምጥተህ አጢስበት፡፡ ያንን ጋኔኑ በሸተተው ጊዜ ይሸሻል ለዘለዓለም አይመለስም (ጦቢት 6:16)
5. **ግነት ይታይበታል፡-** ሀ. የሰዎች ቁመት ሦስት ሺህ ክንድ ያክል ነበር፡፡ (ሄኖክ 2:12) ይላል፡፡

   ☞ **(ሦስት ሺ ክንድ፡- አንድ ሺ አምስት መቶ ሜትር ገደማ ወይም 1 ኪ.ሜ. ተኩል ያህል መሆኑን ልብ ይሏል፡፡)**

   **ለ.** አቤሜሌክ ለ66 ዓመታት ያህል እንቅልፍ ተኛ፡፡ (ተ.ኤ 9:1)

**6. ሌሎች ልዩ ልዩ ስህተቶች፦**

**1. በዋናው፦-** *ዳዊት ቤተመቅደስ "እሠራለሁ" ብሎ ሲያስብ እግዚአብሔር ግን "አትሠራልኝም" ብሎ ከለከለው* **(2ሳሙ 7:1-6, 1ዜና 28:3)**

**በአዋልድ፦-**እግዚአብሔር ቤተመቅደስ *"ሥራ"* አለው ይላል **(**ዕዝ ስቱኤል **1:22-23)**

**2. በዋናው፦-** *አዳም በበለስ ቅጠል እርቃኑን ሸፈነ እንጂ የበላው የእውቀትን ዛፍ ነው* **(ዘፍ 2:17, ዘፍ 3:7)**

**በአዋልድ፦-** *አዳም የበላው የበለስ ዛፍ ነው* **(**ዕዝ ስቱኤል **1:7** 1መቃ **27:15)**

**3.** *ኢየሱስ ክርስቶስ "ኡርኤል" የሚባል መልአክ እንደሆነ ያለጥንቃቄ ተጽፏል::* **(**ዕዝ ሱቱ **3:15, 31, 38 -** ምዕራፍ **4:1** ተመልከት**)**

**4.** *ይኸው መልአክ እንደ "እግዚአብሔር አብ" ሆኖም ተጽፏል* **(**ዕዝ ሱቱ **5:1, 28, 29)**

**5.** *ሥላሴ የሚለው ቃል የቤተክርስቲያን አባት በነበረው "ተርቱሊያን" ከክ.ል. በኋላ የተሰጠ ስያሜ ቢሆንም የብሉይ መጽሐፍ ነው በተባለው በዚህ መጽሐፍ ቃሉ ተጽፏል* **(**ዕዝ ሱቱ **4:5,** ዮዲት **11:19,** ሲራ**3:22)**

**6. በዋናው፦-** በኢየሱስ ስም ስንጸልይ መልስ እናገኛለን:: **(**ዮሐ **14:13, 16:23)**

**በአዋልድ፦-** *የሥጋ ጉስቁልና ጸሎት እንዲሰማ ያደርጋል* **(**ዕዝ ስቱኤል **8:24)**

**7.** *መልአክ ውሸት ሲናገር* **(**ጦቢት **5:11-12)**

**8.** *ምጽዋት ታፀድቃለች* **(**ጦቢት **14:11,** ከሮሜ **4:4-6,** ገላ **2:21** አስተያይ**)**

**9.** *የመቃብያን ፀሐፊ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት አጠያያቂ ነው* **(1**መቃ **19:9, 14, 23:1-2)**

**10.** "ጸሐፊው ኢትዮጵያዊ ይሆንን?" **(**ሲራ **4:25,** ሄኖ **21:31)**

**11.** "እሳቱ የማይጠፋ ትሉ የማያንቀላፋ" የብሉይ ኪዳን ቃል ነውን? **(**ሲራ **7:17)**

**12.** እውነት ፀሐፊው የብሉይ ኪዳን ዘመን ሰው ነውን? **(**ሲራ **24:1-34,** ጥበብ **5:1-6)**

**13.** *ማርያም፣ ጴጥሮስ፣ እግዚአብሔር አብ የሚለው ስያሜ በብሉይ ኪዳን ፈጽመ አይታወቁም:: ነገር ግን* **(**ሲራ **24:10, 12, 28,** በጥበብ **2:12-18** ተመልከት**)**

**14.** *ንስር እና ሰው ሲነጋገሩ* **(**ተ. ኤር **10:23-11:8)**

**15.** *ተዝካር በማውጣት ደህንነት* **(**ሲራክ **7:33)**

**16.** *ለሙሴ የተሠጠው ጽላት ከድንጋይ የተሠራ ቢሆንም "ከዕንቁ" ተብሎ ተጽፏል* **(**ኩፋሌ **1:1,** ዘፀ **34:1, 2**ቆሮ **3:7** አስተያይ**)**

**17.** *እግዚአብሔር ከመላእክት ጋር ሲመካከር* **(**ኩፋሌ **4:4,** ከኢሳ **40:13-15** አስተያይ**)**

**18.** *አዳም ሔዋንን በገነት ውስጥ እያለ አወቃት* **(**ኩፋሌ **4:6,** ከዘፍ **4:1** ጋር አስተያይ**)**

**19.** *እንስሳት ሁሉ በአንድ ቋንቋ ይናገሩ ነበር ይላል* **(**ኩፋ **5:2)**

**20.** *እሁድ በብሉይ ኪዳን እንዴት ተመረጠች?* **(**ሄኖክ **16:3)**

**21.** *ታቦቷ እንደጠፋች ቀረች* **(**ዕዝ.ቁቱ **9:21-23)** *ይህም በባቢሎናውያን ታቦቷ መማረኳንና መጥፋቷን የሚናገረው ክፍል ቤተክርስቲያኗ በልማድ ከምታስተምረው ታቦቷ "አክሱም መጥታለች" ከሚለው ትምህርት ጋር ይጋጫል::*

*በአጠቃላይ ይህንን በሚመሳስሉ ብዙ ስህተቶች የተሞላ ነው፣ ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ሌሎቹ መጽሐፍት ያሟሉትን የቀኖና መስፈርቶች ሊያሟሉ አልቻሉም:: የቀኖና መስፈርቶች የሚባሉትም፦-*

1. *ሐዋርያዊ (ትንቢታዊ) መስፈርት* (Apostolicity)
2. *በአይሁድ እና በጥንቷ ቤተክርስቲያን ያላቸው ተቀባይነት*
3. *የተስማሚነት መስፈርት* (Consistency)
4. *ውስጣዊና ውጫዊ ምስክርነት* (Inspiration)
5. *በቤተክርስቲያን ላይ ያለው ተጽዕኖ* (Recognition)

*እንግዲህ የትኛውም የአዋልድ መጽሐፍ እነዚህን ፈተናዎች ማለፍ አይችልም::*

# ክፍል ፪

## 1. መጽሐፍ ቅዱስ ፍጹም "የእግዚአብሔር ቃል" ነው

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን የሚደግፉ ሁለት ዓይነት ማረጋገጫዎች አሉ፡፡

1. ውስጣዊ ማረጋገጫ እና
2. ውጫዊ መረጋገጫ ናቸው፡፡

**1.1 ውስጣዊ ማረጋገጫ:-** የምንለው በመጽሐፍ ቅዱስ በራሱ ውስጥ የተመለከቱት እውነታዎች እና መጽሐፉ በራሱ የሚሰጣቸው ምስክርነቶች ናቸው፡፡

**1.1.1 መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን በብዙ መቶ በሚቆጠሩ የንባብ ክፍሎቹ ያረጋግጣል፡፡** ለምሳሌ ያህል ዘፍጥረት 1 እና 2 "እግዚአብሔርም ... አለ"

ዘዳግም 6:6 - 9 "እኔ ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል"

ኢያሱ 1:8 "የዚህን ሕግ መጽሐፍ ... ብዬ አላዘዝሁምን?"

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "እግዚአብሔርም አለ" "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" የሚሉ ቃላት እጅግ በጣም በመደጋገም ተጽፈዋል፡፡ ይህም የተናገረው ቃል ከራሱ አፍ በቀጥታ መውጣቱን ያሳያል፡፡ ሌሎችም ጥቅሶች የመጽሐፍ ቅዱስን የእግዚአብሔርን ቃልነት ያረጋግጣሉ፡፡

2ሳሙ 22:31, መዝ 1:2, 12:6, ምሳ 30:5-6, ኢሳ 55:10, ኤር 15:16, ዳን 10:21, ዘኑ 22:38, ዘዳ 18:18-20, ኤር 1:9 23:16-22, ሕዝ 2:7

**1.1.2 ጌታ ኢየሱስ ከብሉይ ኪዳን መጽሐፍት በመጥቀስ የእግዚአብሔር ቃልነቱን አረጋግጧል፡፡**

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተፃፉትን ታሪኮች፣ ተአምራቶች፣ በመጥቀስ እውነተኛነታቸውን አረጋግጧል፡፡ **ለምሳሌ:-**

- የፍጥረት ታሪክ በዘፍጥረት እንደተፃፈው መሆኑን (ማቴ 19:4)
- የአዳምና የሔዋንን ታሪክ እውነተኛነት (ማቴ 19:4-6)
- ስለአቤል (ማቴ 23:35)
- ስለሰይጣን (ሉቃ 11:18, ሕዝ 28:11-19)
- ስለኖህ (ማቴ 24:37,38)
- ስለዮናስ (ማቴ 12:39)
- ስለሎጥ ሚስት (ሉቃ 17:32) ወዘተ ...

ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍትን በመጥቀሱና በርሱም ላይ የሚፈጸሙ ትንቢታዊ ጥቅሶች እውነተኛነት በማረጋገጡ የመጽሐፍቱን የእግዚአብሔር ቃልነት ይበልጥ አሳይቷል፡፡

### 1.1.3 ቀጥተኛ የሆነ የእግዚአብሔር ቃል በፀሐፊዎቹ ነቢያት በኩል ተላልፏል

እግዚአብሔር በተደጋጋሚ በነቢያት አፍ ውስጥ በማለፍ ተናግሯል:: እንዲሁም ራሱ እየነዳቸው ቃሉን ሳይጨምሩ ሳይቀንሱ ጽፈዋል::

**ለምሳሌ**:-1ኛነገ 14:18, 16:12,34, 2ኛነገ 9:36, 14:25, ኤር 37:2, ዘካ7:7,12

በዚህም ምክንያት የነቢያቱን ቃል የማያከብር የእርሱን ቃል እንዳላከበረ ተጽፏል:: ዘዳ 18:19, 1ሳሙ 10:8, 13:13-14, 15:3, 19, 23, 1ኛነገ 20:35, 36, ወዘተ... 1ቆሮ 11:23, 14:37, 1ቆሮ 7:12 (ጳውሎስ የራሱን ቃል ከጌታ ቃል ለይቶ አስቀምጧል) ከዚህም በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች በራሳቸው ለሰዎች የፃፉት ሳይሆን በእግዚአብሔር መንፈስ በመነዳት ቅዱሳን ሰዎች የፃፉት እንደሆነ ይናገራል:: 2ጴጥ 1:20, 21

ስለሆነም በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ላይ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ሊያርፍበት እና የእግዚአብሔር ቃልም መሆኑ ሊረጋገጥ ችሏል::

## 1.2 ውጫዊ ማረጋገጫዎች:- መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን በራሱ ብቻ የሚያስረግጥ ሳይሆን፣ ተጠራጣሪዎችን እንኳን ለማሳመን በሚችሉ ብዙ መረጃዎች የተሞላ ነው::

**1.2.1 የመጽሐፍ ቅዱስ ተከታታይነት እና ወጥነት**:- መጽሐፍ ቅዱስ ተፅፎ ለማለቅ የፈጀው ጊዜ ወደ 1600 ዓመታት ያህል የሚጠጋ ነው:: እንግዲህ በዘፍጥረት ፀሐፊና በራዕይ ፀሐፊ መካከል ይህን ያህል የዘመን ርቀት አለ:: እንዲሁም አምላክ ቃሉን ለማፃፍ የተጠቀመባቸው ሰዎች የተለያየ የዕውቀት፣ የአኗኗር፣ የሥፍራ፣ ወዘተ ልዩነት ያላቸው ሲሆኑ ታዲያ በተለያየ ዘመናት ላይ የነበሩየማይተዋወቁ ሰዎች እንዴት ተከታታይነት ያለውና ወጥነት ያለው መጽሐፍት ሊፅፉ ቻሉ? ይህ ማንም ሊከራከረው ያልቻለና የተፃፈው በአንድ መንፈስ መሪነት ብቻ መሆኑን ያረጋገጠ እውነት ነው::

**1.2.2 የመጽሐፍ ቅዱሳዊ መገለጥ ጥልቅነት**:- መጽሐፍ ቅዱስ እውነትን በሙላትና በረቂቅነት የሚያሳየንን ያህል የሚያሳይ ሌላ መጽሐፍ በዓለም የለም:: ፀሐፊዎቹ ስለዘመናዊ ግኝቶች ምንም ዕውቀት ሳይኖራቸው የፃፏቸው ነገሮች ዛሬ በሳይንሳዊ ምርምሮች በከርሠ ምድር ቁፋሮዎች የበለጠ ሊረጋገጡ ችለዋል:: የእግዚአብሔርን ረቂቅ ሥራዎች፣ ዕቅድና ዓላማውን በመግለጥ እንዲሁም ትንቢታዊ ቃሎቹ ሲፈፀሙ በማየት የእግዚያአብሔር ቃልነቱን በቀላሉ ማረጋገጥ ይቻላል:: የምድርን ክብነት፣ የዝናብን ዑደት፣ የምድርን በሕዋ ላይ መንሳፈፍ ፣የድብ ኮከብ፣ (polar bear)፣ የተፈጥሮን ቅደም ተከተል፣ ምድር ቅርጸ አልባ እንደነበረች፣ በውኃ የተሸፈነች እንደነበር፣ ተክሎች የሕይወት ጅማሬ (The beginning of life on earth) መሆናቸውን ሌሎች የተፈጥሮ ጥበቦችን ወዘተ... ገና ከጅማሬው በጥንቱ ዘመን የተፃፈ ሲሆን ዛሬ እንደብርቅ ግኝት በሳይንሱ ዓለም ተረጋግጠዋል::

**1.2.3 የመጽሐፍ ቅዱስ ሉዓላዊ ባህሪይ**፡- የተፃፈ ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስና ሕያው ሥጋ የሆነው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ በተመሳሳይ መልኩ ሥልጣናቸው ተገልጧል፡፡ ይህም ማለት ሥጋ የሆነው ቃል በጽሑፍ የሰፈረውን ቃል መለኮታዊ ቃል እንደሆነና በመንፈሳዊ ነገሮች ሁሉ ላይ የመበየን ሥልጣን እንዲሁም ማንም ሊቃወመው የማይችል ሉዓላዊነት እንዳለው አመልክቷል፡፡

**1.2.4 የመጽሐፍ ቅዱስ የማያዳላው ሥልጣን**፡- መጽሐፍ ቅዱስ በማንኛውም የሰው ልጅ ላይ በሥልጣን ይናገራል፡፡ የሰውን ሁሉ ኃጥያተኝነት እና ደካማነት አጋልጧል፡፡ በሰዎች ብዕር ቢፃፍም ከሰዎች ወደ ሰዎች ሳይሆን ከእግዚአብሔር ወደ ሰው የሆነ የሥልጣን ቃል ያስተላልፋል፡፡ በነገሥታት ላይ በድሆች ላይ፣ በባለጠጐች፣ በመላዕክት ላይ በልዩ ፍጥረት ላይ የፍርድን ቃል የማሳለፍ ሥልጣን አለው፡፡

**1.2.5 የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ታላቅነት**፡- መጽሐፍ ቅዱስ ከሰው እውቀት በላይና ውጪ የሆኑትን ምስጢር ይገልጣል፡፡ በማንኛውም ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ትምህርታዊ ገለጣ እጅግ በጣም ፍፁምና ትክክል ሲሆን ጊዜ የማይለዋውጠው፣ ቴክኖሎጂ የማይሽረውን እውቀት ይገልጣል፡፡ ከዚህም የተነሳ ጥንታዊ መጽሐፍ ወይም ዘመናዊ መጽሐፍ ነው ለማለት ስለሚያስቸግር «ዘለዓለማዊ ቃል» ሊባል ችሏል፡፡

**1.2.6 በሥነፅሁፍ ይዘቱ**፡- በዚህ ረገድ ሲታይ በእርግጥ በሰዎች በራሳቸው ችሎታ አለመፃፉን በፍጥነት ማወቅ ይቻላል፡፡ በውስጡ የሚገኘው ይዘት ሁሉንም የስነፅሁፍ ዘርፎች ያካተተ ነው፡፡ የታሪክ ዘገባዎች፣ ትንቢቶች፣ ቅኔዎች፣ ተውኔት፣ የጦርነት፣ የፍቅር ታሪኮችን የያዘ ነው፡፡ ይህም በየትኛውም የእውቀት ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎችን የመማረክ ኃይል እንዲኖረው አድርጎታል፡፡

**1.2.7 የመጽሐፍ ቅዱስ የመለወጥ ኃይልና የሕትመት ብዛት**፡- በዓለማችን የመጽሐፍ ቅዱስን ያህል ለተለያዩ ሕዝቦችና ቋንቋዎች የተተረጐመ መጽሐፍ የለም፡፡ በሕትመትም ብዛት አንፃር ፈጽሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚወዳደር አይገኝም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባለው መልዕክትና፣ ትምህርት ሰዎች ሥር ነቀል የሆነ የሕይወትና የዓላማ ለውጥ ማምጣታቸው መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ቃል ለመሆኑ ማስረጃ ነው፡፡ ከቃሉም የተነሳ የብዙ እልፍ ግለሰቦች እንዲሁም ሀገራት ታሪክ ተለውጧል፡፡ ሰውን የማንፃት፣ የመቀደስ፣ የመለወጥ ችሎታው ያለጥርጥር የእግዚአብሔር ቃል ለመሆኑ ማስረጃ ነው፡፡

## 2. <u>መጽሐፍ ቅዱስ ፍፁም "የእግዚአብሔር እስትንፋስ" ነው።</u>

መጽሐፍ ቅዱስ እስትንፋሰ እግዚአብሔር ነው ስንል አምላክ ለመፃፍ የተጠቀመባቸውን ሰዎች ፍፁም በሆነ ምሪት እንዲጽፉ ማድረጉን ለማሳየት ነው። እስትንፋሰ እግዚአብሔር (Inspiration) የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ Theopneustos ተብሎ የተፃፈው ሲሆን ትርጉሙም "አምላክ እፍ አለ" እንደማለት ነው ይህ በተፃፈበት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ በተለያየ አተረጓጎም ተቀምጧል። (2ኛ ጢሞ 3:16)

"የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ... " (1954 ትርጉም)

"ቅዱስ መጽሐፍ በሙሉ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተፃፈ ነው" (1980 ትርጉም)

"ቅዱሳት መጽሐፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው" (አ.መ.ት)

**"All scripture is given by inspiration of God" (KJV)"**

**"Every part of scripture is God – breathed" (The Message)**

በተለያዩ የአተረጓጎም ስልቶች ቢቀመጥም መሠረታዊው የ"ቲዮኒውስቶስ" ሀሳብ ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሁፎች በሙሉ በእግዚአብሔር ተጽዕኖና ሙሉ ተሳትፎ የተፃፉ መሆናቸውን ለማሳየት ነው። ከዚህም በተጨማሪ "መጽሐፍት ሁሉ" የሚለው ቃል "graphe" የሚለው ሲሆን ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን መጽሐፍት ብቻ የሚገልጽ እንጂ ለሌሎች መንፈሳዊ ሕትመቶች (መጽሐፎች፣ መጽሔቶች ወዘተ...) የሚያገለግል አይደለም። በዚሁ ጉዳይ ላይ የተለያዩ ንድፈ ሀሳቦች (theories) አሉ። አምላክ ቅዱሳት መጽሐፍቱን ለማፃፍ ወይም የእርሱን እስትንፋስ የተጠቀመው በተለያየ መጠን እና ደረጃ ነው በሚሉ አመለካከቶች ላይ የተደገፉ ንድፈ ሀሳቦች ናቸው።

### <u>የእስትንፋሰ እግዚአብሔር አመለካከቶች (ንድፈ ሀሳቦች)</u>

**ለምሳሌ:- 1. የቃል/ምሉዕ ንድፈ ሀሳብ (Full inspiration of words)**

የመጀመሪያዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፎች በተፃፉበት ወቅት እግዚአብሔር ፀሐፊዎቹን በቃላት አመራረጥ ሳይቀር መርቷቸዋል ማለት ነው። ይህም ያለ መንፈስ ምሪት የተፃፈ ክፍል የለም ለማለት ነው።

**2. የቃል በቃል ንድፈ ሀሳብ (Mechanical and word inspiration)**

አምላክ ቃሉን ያፃፋቸው ፀሐፊዎችን ምንም ተሳትፎ እንዳያደርጉ አድርጓል ስለዚህ የፀሐፊዎቹ ምንም ስሜት አልተፃፈም የሚል ነው። ይህ ደግሞ የፀሐፊዎቹን ሐዘን፣ ደስታ፣ ቁጣ ወዘተ... የማያካትት ንድፈ ሀሳብ ያደርገዋል።

**3. ጽንሰ - ሀሳባዊ (Idealistic approach)**

እግዚአብሔር ትክክለኛ ቃሎቹን ሳይሆን ለፀሐፊዎቹ የሰጣቸው ጽንሰ ሀሳቡን ብቻ ነውና የሰዎች ጽሑፍ ነው የሚል አመለካከት ሲሆን የመጽሐፍ ቅዱስ ባለቤት ሰዎች እንደሆኑ ያስተምራል።

4. **ከፊል እስትንፋስ እግዚአብሔር** (Partial inspiration)

ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰኑ ክፍሎች ብቻ ናቸው በእግዚአብሔር መሪነት የተፃፉት የሚል ንድፈ ሀሳብ ነው::

5. **አዲሱ ኦርቶዶክሲ** (Neo-orthodoxy)

ካርል ባርት የተባለ ሰው ያቀረበው ንድፈ ሀሳብ ሲሆን መጽሐፍ ቅዱስ በሚፃፍበት ጊዜ የመለኮታዊ እስትንፋስ ድርሻ ቢኖርም መጽሐፉ ውስጥ ግን ስህተት ይገኝበታል የሚል ንድፈ ሀሳብ ነው::

6. **ተፈጥሮአዊ እስትንፋስ** (Natural Inspiration theory)

ከሁሉ የከፋና መጽሐፍ ቅዱስን እንደማንኛውም ተራ መጽሐፍ የሚቆጥር አስተምህሮ ነው::

## የእስትንፋስ እግዚአብሔር ማረጋገጫዎች

**የክርስቶስ ምስክርነት**:- መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ለመሆኑ ዋናውን ማስረጃ የምናገኘው ከራሱ ከኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ከሁሉም በላይ ደግሞ እርሱ ከመጽሐፍት መጥቀሱና ማስተማሩ መጽሐፍት ያላቸውን ሥልጣን አረጋግጧል:: በማቴ 5:18 መሠረት ከሕግ አንዲት ነጥብ እንኳ እንደማታልፍ በመናገር ቃሉ የእግዚአብሔር እስትንፋስ መሆኑን አስረድቷል:: «አንዲት ነጥብ» ወይም ቃል አታልፍም በማለቱም እያንዳንዲቷ ቃል የአምላክ እስትንፋስ መሆኗን አጉልቷል::

በዮሐ 10:35 መጽሐፉ ሊሻር አይችልምና

በማቴ 1:22-23 የብሉይ ኪዳን ቃላት ሲፈጸሙ በማየት... ወዘተ በዚህ ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ጽሁፎች የሰው ፈጠራ ሳይሆኑ በመንፈስ በመነዳት መፃፋቸውን ማወቅ ይቻላል:: 2 ጴጥ 1:21

**የምንባቦች ምስክርነት**:- በ2ጢሞ 3:16 ላይ በቀጥታ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ሁሉ የእግዚአብሔር እስትንፋስ (መንፈስ) እንዳለባቸው ተጽፏል:: ይህም ቃላቶቹ ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች በሙሉ እስትንፋሰ እግዚአብሔር እንዳለባቸው ያረጋግጣል:: እንዲሁም በ2ጴጥ 1:21 ላይ ሰዎች በምንም ሁኔታ በራሳቸው ተነሳሽነት ወይም ዕውቀት እንዳልፃፉትና ጽሁፎቹ በሙሉ የተፃፉት በእግዚአብሔር መንፈስ ተነድተው እንደሆነ ተጽፏል:: ይህም ካመነዳትካ የሚለው ቃል ፀሐፊዎቹ የራሳቸውን ቀጥተኛ ሀሳብ ያለምንም ግፊት መፃፍ እንደማይችሉ ያሳያል:: ከዚህም የተነሳ የመጀመሪያዎቹ (Original manuscripts) ጽሑፎች ፈጽሞ ስህተት የሌለባቸው ናቸው::

## 3. የመጽሐፍ ቅዱስ ውስጣዊ ይዘትና አወቃቀር

አይሁድ የመጻሕፍት መምህራን 39ኙን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ለሦስት ይከፍሏቸዋል:: ይህንንም አከፋፈል ጌታ ራሱ በትምህርቱ ተጠቅሞበታል:: አይሁዶች ይህንን አከፋፈላቸውን በአጭሩ 'ታናክ' ብለው ይጠሩታል:: ይህም ማለት

1. ታ - ተውራት (ሕጐች)
2. ና - ነቢም (ነቢያት)
3. ክ - ኬቱቢም (መዝሙራትናመጻሕፍት) ማለት ነው:: ሉቃ 24:44

የሥነ መለኮት ምሁራን በበኩላቸው ደግሞ መጻሕፍቶቹ በውስጣቸው ካለው ይዘት በመነሳት ብሉይ ኪዳንን በአራት አዲስ ኪዳንንም በአራት ይዘቶች አዋቅረዋቸዋል::

| ተ.ቁ. | የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አወቃቀር | ብዛት | የመጻሕፍቶቹ ዓይነት |
|---|---|---|---|
| 1 | የሕግ መፃሕፍት | 5 | ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ኦሪት ዘዳግም |
| 2 | የታሪክ መፃሕፍት | 12 | ከመጽሐፈ ኢያሱ እስከ መጽሐፈ አስቴር |
| 3 | የቅኔ መፃሕፍት | 5 | ከመጽሐፈ ኢዮብ እስከ መኃልየ መኃልይ |
| 4 | የትንቢት መፃሕፍት<br>- ታላላቅ የትንቢት መፃሕፍት<br>- ትንንሽ የትንቢት መፃሕፍት | <br>3<br>14 | <br>ከትንቢተ ኢሳይያስ እስከ ትንቢት ሕዝቅኤል<br>ከትንቢተ ዳንኤል እስከ ትንቢት ሚልክያስ |
| | **ጠቅላላ** | **39** | |

| | የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት አወቃቀር | ብዛት | የመጻሕፍቶቹ ዓይነት |
|---|---|---|---|
| | የወንጌል መፃሕፍት | 4 | ከማቴዎስ ወንጌል እስከ ዮሐንስ ወንጌል |
| | ታሪክ | 1 | የሐዋርያት ሥራ |
| | መልዕክቶች<br>- የጳውሎስ መልዕክቶች<br>- የዕብራውያን መልዕክት<br>- ጠቅላላ መልዕክቶች | <br>13<br>1<br>7 | <br>ከሮሜ መልዕክት እስከ ፊልሞና መልዕክት<br>የዕብራውያን መልዕክት<br>ከ1ኛ ጴጥሮስ እስከ ይሁዳ መልዕክት |
| | ትንቢት | 1 | የዮሐንስ ራዕይ |
| | **ጠቅላላ** | **27** | |
| | **ብሉይና አዲስ አጠቃላይ** | **66** | |

**የብሉይ ኪዳን መፃሕፍት አወቃቀር በዝርዝር**

| ይዘት | ተ.ቁ. | የመጽሐፍት ሥም | ፀሐፊው | የተፃፈበት ዘመን |
|---|---|---|---|---|
| የሕግ መፃሕፍት | 1 | ኦሪት ዘፍጥረት | ሙሴ | 1500/1400 ቅድመ ክርስቶስ አካባቢ |
| | 2 | ኦሪት ዘፀአት | | |
| | 3 | ኦሪት ዘሌዋውያን | | |
| | 4 | ኦሪት ዘኍልቁ | | |
| | 5 | ኦሪት ዘዳግም | | |
| የታሪክ መፃሕፍት | 6 | መጽሐፈ ኢያሱ | ኢያሱ | 1440 ቅ.ክ. |
| | 7 | መጽሐፈ መሳፍንት | ሳሙኤል | 1000-721 ቅ.ክ. |
| | 8 | መጽሐፈ ሩት | ሳሙኤል | 1000 ቅ.ክ. |
| | 9 | መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ | የናታን ልጅ ዛቡድ ወይም ሳሙኤል | 930-722 ቅ.ክ. |
| | 10 | መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ | የናታን ልጅ ዛቡድ ወይም ሳሙኤል | 930-722 ቅ.ክ. |
| | 11 | መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ | ኤርምያስ | 560-538 ቅ.ክ. |
| | 12 | መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ | ኤርምያስ | 560-538 ቅ.ክ. |
| | 13 | መጽሐፈ ዜናመዋዕል ቀዳማዊ | ዕዝራ | 450-400 ቅ.ክ. |
| | 14 | መጽሐፈ ዜናመዋዕል ካልዕ | ዕዝራ | 450-400 ቅ.ክ. |
| | 15 | መጽሐፈ ዕዝራ | ዕዝራ | 440 ቅ.ክ. |
| | 16 | መጽሐፈ ነህምያ | ዕዝራ | 440 ቅ.ክ. |
| | 17 | መጽሐፈ አስቴር | ምናልባት መርዶክዮስ ወይም ዕዝራ | 450-400 ቅ.ክ. |
| የቅኔ መፃሕፍት | 18 | መጽሐፈ ኢዮብ | ምናልባት ሙሴ? | 1440-440 ቅ.ክ. |
| | 19 | መዝሙር | ዳዊት፣አሳፍ ቆሬያውያን፣ሙሴ፣ ሰሎሞን፣ኤታን | 1000 ቅ.ክ. |
| | 20 | መጽሐፈ ምሳሌ | ሰሎሞን | 971-931 ቅ.ክ. |
| | 21 | መጽሐፈ መክብብ | ሰሎሞን | 971-931 ቅ.ክ. |
| | 22 | መኃልየ መኃልይ | ሰሎሞን | 971-931 ቅ.ክ. |
| የትንቢት መፃሕፍት | 23 | ትንቢተ ኢሳይያስ | ኢሳይያስ | 740-681 ቅ.ክ |
| | 24 | ትንቢተ ኤርምያስ | ኤርምያስ/ባሮክ | 627-575 ቅ.ክ |
| | 25 | ሰቆቃወ ኤርምያስ | ኤርምያስ | 586-575 ቅ.ክ |
| | 26 | ትንቢተ ሕዝቅኤል | ሕዝቅኤል | 597-571 ቅ.ክ |
| | 27 | ትንቢተ ዳንኤል | ዳንኤል | 605-536 ቅ.ክ |
| | 28 | ትንቢተ ሆሴዕ | ሆሴዕ | 760-723 ቅ.ክ |
| | 29 | ትንቢተ አሞጽ | አሞጽ | 760-750 ቅ.ክ |
| | 30 | ትንቢተ ሚክያስ | ሚክያስ | 735-700 ቅ.ክ |
| | 31 | ትንቢተ ኢዩኤል | ኢዩኤል | 835/500 ቅ.ክ |
| | 32 | ትንቢተ አብድዩ | አብድዩ | 586 ቅ.ክ |
| | 33 | ትንቢተ ዮናስ | ዮናስ | 785-750 ቅ.ክ |
| | 34 | ትንቢተ ናሆም | ናሆም | 660-630 ቅ.ክ |
| | 35 | ትንቢተ ዕንባቆም | ዕንባቆም | 605-598 ቅ.ክ |
| | 36 | ትንቢተ ሶፎንያስ | ሶፎንያስ | 640-620 ቅ.ክ |
| | 37 | ትንቢተ ሐጌ | ሐጌ | 520 ቅ.ክ |
| | 38 | ትንቢተ ዘካርያስ | ዘካርያስ | 520-515 ቅ.ክ |
| | 39 | ትንቢተ ሚልክያስ | ሚልክያስ | 433-420 ቅ.ክ |

## የአዲስ ኪዳን መፃሕፍት አወቃቀር በዝርዝር

| ይዘት | | ተ.ቁ. | የመጽሐፍት ሥም | ፀሐፊው | የተፃፈበት ዘመን |
|---|---|---|---|---|---|
| የወንጌል መፃሕፍት | | 1 | የማቴዎስ ወንጌል | ማቴዎስ | 70-80 ዓ.ም. |
| | | 2 | የማርቆስ ወንጌል | ማርቆስ | 65 ዓ.ም. |
| | | 3 | የሉቃስ ወንጌል | ሉቃስ | 70-85 ዓ.ም. |
| | | 4 | የዮሐንስ ወንጌል | ዮሐንስ | 90-100 ዓ.ም. |
| ታሪክ | | 5 | የሐዋርያት ሥራ | ሉቃስ | 70-85 ዓ.ም. |
| የመልዕክት መፃሕፍት | የጳውሎስ መልዕክት | 6 | ወደ ሮሜ ሰዎች | ጳውሎስ | 55-56 ዓ.ም. |
| | | 7 | ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1ኛ | ጳውሎስ | 54 ዓ.ም. |
| | | 8 | ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 2ኛ | ጳውሎስ | 55 ዓ.ም. |
| | | 9 | ወደ ገላትያ ሰዎች | ጳውሎስ | 49-50 ዓ.ም. |
| | | 10 | ወደ ኤፌሶን ሰዎች | ጳውሎስ | 60-62 ዓ.ም. |
| | | 11 | ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች | ጳውሎስ | 60-62 ዓ.ም. |
| | | 12 | ወደ ቈላስይስ ሰዎች | ጳውሎስ | 60-62 ዓ.ም. |
| | | 13 | ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 1ኛ | ጳውሎስ | 50-51 ዓ.ም. |
| | | 14 | ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2ኛ | ጳውሎስ | 50-51 ዓ.ም. |
| | | 15 | ወደ ጢሞቴዎስ 1ኛ | ጳውሎስ | 62-64 ዓ.ም. |
| | | 16 | ወደ ጢሞቴዎስ 2ኛ | ጳውሎስ | 65-67 ዓ.ም. |
| | | 17 | ወደ ቲቶ | ጳውሎስ | 62-64 ዓ.ም. |
| | | 18 | ወደ ፊልሞና | ጳውሎስ | 60-62 ዓ.ም. |
| | | 19 | ወደ ዕብራውያን | ጳውሎስ ወይም አጵሎስ ወይም በርናባስ | 67-68 ዓ.ም. |
| | አጠቃላይ የመልዕክት መፃሕፍት | 20 | የጴጥሮስ መልዕክት 1ኛ | ጴጥሮስ | 62-64 ዓ.ም. |
| | | 21 | የጴጥሮስ መልዕክት 2ኛ | ጴጥሮስ | 65-67 ዓ.ም. |
| | | 22 | የዮሐንስ መልዕክት 1ኛ | ዮሐንስ | 90-100 ዓ.ም. |
| | | 23 | የዮሐንስ መልዕክት 2ኛ | ዮሐንስ | 90-100 ዓ.ም. |
| | | 24 | የዮሐንስ መልዕክት 3ኛ | ዮሐንስ | 90-100 ዓ.ም. |
| | | 25 | የያዕቆብ መልዕክት | ያዕቆብ (የጌታወንድም) | 48/62 ዓ.ም. |
| | | 26 | የይሁዳ መልዕክት | ይሁዳ (የጌታወንድም) | 67-80 ዓ.ም. |
| የትንቢት መጽሐፍ | | 27 | የዮሐንስ ራዕይ | ዮሐንስ | 90-100 ዓ.ም. |

## 4. ስለመጽሐፍ ቅዱስ ጠቃሚ ነጥቦች

የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት ብዛት ....................................66
የምዕራፎች ብዛት ...............................................................1,189
አጠቃላይ የቁጥሮች ብዛት ....................................................31,102
የተስፋ ቃሎች ......................................................................1,260
የተለያዩ ትዕዛዛት ..............................................................6,468
ረጅሙ የሰው ስም ...............................................................ኢሳ 8:4 (13 ፊደላት)
ረጅሙ ቁጥር (Verse)..........................................................አስቴር 8:9
አጭሩ ቁጥር ......................................................................ዮሐ 11:35
ብዙ ምዕራፍ ያለው መጽሐፍ .................................................መዝሙር
ትንሹ መጽሐፍ ...................................................................3ኛ ዮሐንስ
ረጅም ምዕራፍ ....................................................................መዝሙር 119 (176 ቁጥሮች)
አንድ ምዕራፍ ብቻ ያላቸው 5 መጽሐፍት ..................................አብድዩ፣ፊልሞና፣2ኛና3ኛዮሐንስ ይሁዳ
የእግዚአብሔር ስም የሌለባቸው መጽሐፍት ........................አስቴርና መኃልየመኃልይ (አ.መ.ት)

- ኢየሱስ ክርስቶስ ከ22 የብሉይ ኪዳን መጽሐፍቶች ጥቅሶችን በመውሰድ አስተምሯል።
- በማቴዎስ ወንጌል 19 ጊዜ፣ በማርቆስ ወንጌል 15 ጊዜ፣ በሉቃስ ወንጌል 25 ጊዜ፣ በዮሐንስ ወንጌል 11 ጊዜ ብሉይ ኪዳንን ጠቅሷል።
- የዕብራውያን መጽሐፍ 85 ዓይነት ምሳሌዎችንና ማብራሪያዎችን ይጠቀማል።
- የራዕይ መጽሐፍ 245 ምሳሌዎችን (Figures) ይጠቅሳል።

## 5. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መመሪያዎች

መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት የሚፈልግ ሰው ሁሉ የሚከተሉትን አጠቃላይ መመሪያዎች በጥብቅ ሊያውቅ ያስፈልገዋል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ዋነኛ ዓላማ የአንባቢውን ፍላጎት ማርካት ሳይሆን የእግዚአብሔርን እውነትና መንገድ ብቻ ማሳየት እንደሆነ ማወቅ፣

መጽሐፍ ቅዱስን እጅግ በማክበር ለቃሉም ትሁት መሆን ያስፈልጋል። ማናቸውንም የራስ ዕውቀት ወይም መረዳት በመጽሐፉ ቃል ብርሃንነት መለካት እንጂ ቃሉን በራሳችን መረዳት መለካት አይገባም።

መጽሐፉን እንደተፃፈ ማንበብ እንጂ ለገዛ ጥፋት ማጣመም፣ ከተፃፈው ማለፍ ወይም ቃሉን ለድርድር ማቅረብ ወዘተ በአምላክ ፍርድ እንደሚያውል ማወቅ ያስፈልጋል

ያለመንፈስ ቅዱስ እርዳታ መጽሐፍ ቅዱስን መተርጐም ስለማይቻል አንባቢው ጌታ ኢየሱስን እንደግል አዳኝ አድርጐ በመቀበል መንፈስ ቅዱስን ማግኘት ይገባዋል።

ቃሉን ካጠኑ በኋላ በዘወትር ሕይወት ላይ በተግባር ማዋልና መለማመድ ያስፈልጋል።

## 6. ልዩ ልዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴዎች

**መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ**:- የመጽሐፉን የተወሰነ ምንባብ ማንበብ፣ ወይም ምዕራፍ፣ ወይም አንዱን ሙሉ መጽሐፍ ማንበብ ራዕ 1:3 ይህ የንባብ ልማድ ባለማቋረጥ፣ በየጊዜው፣ በተመስጦ እና በእምነት እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስና በመታዘዝ ሊሆን ይገባዋል:: መዝ 1:3

**መጽሐፍ ቅዱስን መስማት**:- ሌሎች መጽሐፍ ቅዱስን ሲያነቡ መስማት ለምሣሌ በምንባብ ክፍለጊዜዎች፣ በራዲዮ፣ በተቀረፁ ካሴቶች ወዘተ... ሮሜ 10:17

**መጽሐፍ ቅዱስን በጥልቀት ማጥናት**:- የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በጥልቀት በመመርመር ትርጉማቸውን ወይም መልዕክቶቻቸውን ለማግኘት መሞከር ነው:: ሐዋ 17:11 ይህም ዘዴ በውስጡ ሦስት ነገሮችን ያካትታል::

**ምልከታ (Observation)**:- በንባቡ ውስጥ ያሉትን ዋነኛ ነገሮች መለየት

- ✞ ዋነኛው ገፀባሕርይ ማንነው?
- ✞ የተፈፀመው ዋነኛ ድርጊት ምንድነው?
- ✞ ድርጊቱ የተፈፀመው በየትኛው ሥፍራነው?
- ✞ ድርጊቱ መቼ ተፈፀመ?
- ✞ ድርጊቱ ለምን ተፈፀመ?
- ✞ በምንባቡ (Passage) ውስጥ ያሉት አሳቦች እንዴት ይቀራኛሉ?

**ትርጓሜ (Interpretation)**:- በአጠቃላይ የምንባቡ መልዕክት ምንድነው?

**ትግበራ (Application)**:- በምንባቡ ውስጥ ያለውን መልዕክት ካገኙ በኃላ በዘወትር ሕይወታችን ላይ ተፈፃሚ ማድረግና መለማመድ:: ለምሳሌ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማንሳት ትግበራን ማዳበር ይቻላል::

- ✞ ስለእግዚአብሔር፣ ስለኢየሱስ ክርስቶስ፣ ስለመንፈስ ቅዱስ ምን ተማርኩ?
- ✞ በምንባቡ ውስጥ ያገኘሁት ልለማመደው የሚገባ ጥሩ ምሳሌ እና ላስወግደው የሚገባኝ መጥፎ ልምምድ ምንድነው?
- ✞ ከምንባቡ ያገኘሁት በእግዚአብሔርና በሰው ፊት የተጣለብኝ ኃላፊነት ምንድነው?
- ✞ ካለኝ የክርስትና ልምምድ የሚበረታታው ጥሩ ጐኔ የቱ ነው
- ✞ በምንባቡ ውስጥ የተሰጠኝ የተስፋ ቃል ምንድነው?

**ጥቅሶች ማጥናት (Memorization)**:- ጥቅሶችን በቃላችን እስክንይዛቸውና እስክንናገራቸው ድረስ ደጋግሞ ማጥናት::

**የመጽሐፍ ቅዱስ ተመስጦ (Meditation)**:- ስናነብ፣ ስናጠና ወዘተ... ባገኘናቸው መልዕክቶች ላይ በፀጥታ ማሰላሰል እና ቃሉን ማዋሃድ (መዝ 1:2, ኢያ 1:8)

**ማስታወሻ**:- መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት የሚፈልግ ሰው በተቻለ መጠን ለጥናት የሚሆኑ መርጃ መጽሐፍትን ማዘጋጀት ይኖርበታል::

*ለምሳሌ:-* የተለያዩ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱሶች፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣

**ማብራሪያዎች** (Commentaries) **ወዘተ...**

**<u>የአዘጋጁ ጸሎት</u>፡-** ***መጽሐፍ ቅዱስን እናስተውል ዘንድ አእምሮአችንን ጌታ አብዝቶ ይክፈተው (ሉቃ 24:44) አሜን፡፡***

☞ ***ዳዊት ፋሲል***

**ስ.ቁ. 0917804407**

***ፖ.ሣ.ቁ.* 67 *ጅማ***

E-mail – niguye2004@yahoo.com

# መንፈስ ቅዱስ



## ለማስተማሪያ
## እና
## ለጥናት የተዘጋጀ

በዳዊት ፋሲል ተዘጋጀ

1999 ዓ.ም.

# መንፈስ ቅዱስ

## 1. መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስን በተለያየ ስያሜ ይጠራዋል።

- መንፈስ — ማር 1:10, ገላ 5:5, ራዕ 22:17
  - ✓ እርሱ መንፈሳዊ አካል ያለው መለኮት እንጂ የሚጨበጥ፣ የሚዳሰስ አካል የለውም።
- መንፈስ ቅዱስ — ኢሳ 63:10-11, ሉቃ 11:13, 1ተሰ 4:8
  - ✓ ሌሎች ርኩሳን የሆኑ መናፍስቶች መኖራቸውን የሚያሳይና እርሱ ግን ፍጹም ቅዱስ፣ ንጹህ መንፈስ መሆኑን መግለጫ ነው።
- የእግዚአብሔር መንፈስ — ዘፍ 1:2, ኢዩ 2:28, ሮሜ 8:14, 1ቆሮ 3:16 ኢሳ 63:14
  - ✓ እርሱ ፍጹም አምላክ ወይም እግዚአብሔር መሆኑን የሚገልጥ ስም ነው።
- የአባት መንፈስ — ማቴ 10:20
  - ✓ በእግዚአብሔር ልጆች(አማኞች) ውስጥ ሆኖ የሚናገር ስለጌታ ኢየሱስም የሚመሰክር ነው።
- የልጁ መንፈስ — ገላ 4:6
  - ✓ ኢየሱስ አባት ሆይ ብሎ የጸለየበት መንፈስ ሲሆን በአማኞች ውስጥ ያለውም ራሱ በኢየሱስ ውስጥ የነበረው መንፈስ ነው።
- የልጅነት መንፈስ — ሮሜ 8:15
  - ✓ የልጁ የኢየሱስ መንፈስ ራሱ በአማኝ ውስጥ የገባ ሲሆን አማኙ ልክ እንደ ኢየሱስ እግዚአብሔርን አባቴ ብሎ ይጠራዋል።
- የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ — ፊል 1:19
  - ✓ ደህንነት የሚሰጥ መንፈስ ነው።
- የክርስቶስ መንፈስ — 1ጴጥ 1:11
  - ✓ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ስለሚመጣው መሲህ (ክርስቶስ) አብዝተው ይናገሩ ነበር ስሙ ኢየሱስ የተባለው ከተወለደ በኋላ መሆኑ ይታወቃል።
- የጌታ መንፈስ — 2ቆሮ 3:17
  - ✓ የቤተክርስቲያን ጌታዋ ክርስቶስ እንጂ ሙሴ አይደለም። በመሆኑም አማኝ ከሕግ ባርነት አርነት ወጥቶ በመንፈስ ቅዱስ ሕግ (መመሪያ) መሠረት ይኖራል።

- የእውነት መንፈስ ዮሐ 14:17, 15:26, 1ዮሐ 5:6
    - ✓ ወደ እግዚአብሔር ዕውቀት እና እውነት ሁሉ አማኙን ይመራል።
- የሕይወት መንፈስ ሮሜ 8:2
    - ✓ የሙሴ ሕግ የሞትና የባርነት ሕግ ሲሆን የመንፈስ ቅዱስ መመሪያ እና ድምጽ ግን ወደ ሕይወት ይመራናል።
- የክብር መንፈስ 1ጴጥ 4:14
    - ✓ ሰዎች በክርስቶስ ምክንያት ቢያዋርዱንም መንፈስ ቅዱስ ግን በክብር ይሞላናል።
- አጽናኝ ዮሐ 14:16, 16:7
    - ✓ ጌታን በዓይናችን እስከምናየው ድረስ ልባችንን እያጽናና እስከ ጌታ መምጣት ድረስ በጽናት ያቆየናል።
- የተስፋው መንፈስ ኤፌ 1:13
    - ✓ የሚመጣው ርስት በተስፋ ቃል የተነገረን ሲሆን እንደምንወርሰው ማረጋገጫችን መንፈስ ቅዱስ ነው።
- የእግዚአብሔር፣ የጥበብ፣ የማስተዋል፣ የምክር፣ የኃይል፣ የእውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ኢሳ 11:2
    - ✓ በጌታ በኢየሱስ ላይ ያለው ምሉዕ የሆነው መንፈስ ቅዱስ፣ የበጉ ሰባት (ፍጹም) ዓይኖች ናቸው።

**2. የመንፈስ ቅዱስ ስም ከእግዚአብሔር ጋር በተመሳሳይ ይጠቀሳል ምክንያቱም እርሱ ራሱ እግዚአብሔር ስለሆነ።**

- መንፈስ ቅዱስን መዋሸት ሐዋ 5:3
    - ⇨ እግዚአብሔርን መዋሸት ሐዋ 5:4
- የመንፈስ ቅዱስ ቤተመቅደስ 1ቆሮ 6:19, 20
    - ⇨ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ 1ቆሮ 3:16, 17
- መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን ከሙታን ለይቶ አስነሳው ሮሜ 8:11
    - ⇨ እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሙታን ለይቶ አስነሳው ሐዋ 2:24, 32
- በመንፈስ ኃይል መስበክ 1ቆሮ 2:4
    - ⇨ በእግዚአብሔር ኃይል መስበክ 1ቆሮ 2:5 (በአዲሱ ትርጉም)

**3. መንፈስ ቅዱስ አምላክ ስለሆነ መለኮታዊ ባህርያት አሉት።**

- ፈጣሪ ነው — ዘፍ 1:2, ኢዮ 33:4
- ሁሉን ያውቃል (Omniscient) — 1ቆሮ 2:10-11, ዮሐ 16:13
- ኃያል ነው — ሉቃ 1:35, ሮሜ 15:19
- ሁሉን የሚችል ነው (Omnipotent) — ኢዮ 33:4
- ዘላለማዊ ነው — ዕብ 9:14
- በሁሉ ቦታ ይገኛል (Omnipresent) — መዝ (139):7
- ከአብና ከወልድ ጋር ባለመነጠል ተጠርቷል — ማቴ 28:19, 2ቆሮ 13:14

**4. መንፈስ ቅዱስ እንደ አብና ወልድ ሁሉ ራሱን የቻለ ማንነት እና <u>አካል ያለው መለኮት</u> እንጂ የሆነ "ኃይል ብቻ" ወይም "ተጽዕኖ" አይደለም።**

ስለዚህ እርሱ የራሱ የሆነ ማንነት ስላለው

1. ማወቅ አለው
2. ስሜት አለው
3. ፈቃድ አለው

- እርሱ ተብሏል (ሰብዓዊ ተውላጠ ስም) — ዮሐ 16:13-14, ዮሐ 15:27
  He (personal pronoun)
- እርሱም ተብሏል (ሰብዓዊ ተውላጠ ስም) — ኤፌ 1:14, ዮሐ 14:17
  Whom ይላል What አይልም
- ሌላ አጽናኝ ተብሏል — ዮሐ 14:16
- ያስተምራል፣ የተማሩትን ያስታውሳል — ዮሐ 14:26
- የጸጋ ስጦታን በራሱ ፈቃድ እንደወደደ ይሰጣል — 1ቆሮ 12:11
- በመቃተት በአማኞች ውስጥ ሆኖ ይማልዳል (ይጸልያል) — ሮሜ 8:26
- ያዝናል (ስሜት) — ኤፌ 4:30
- ያጽናናል — ሐዋ 9:31
- ይናገራል — ሐዋ 13:2
- ይከለክላል — ሐዋ 16:6

**5. የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች በአሮጌው (ብሉይ) ኪዳን ዘመን**

- በፍጥረት ሥራ ላይ — ዘፍ 1:2
- ለተለያዩ ሰዎች ትንቢትን ይሰጥ ነበር — ሕዝ 2:2, 8:3, 11:1-5
  - በለዓም — ዘኁ 24:2-9
  - ሳዖል — 1ሳሙ 10:6,10
  - ዳዊት — ሐዋ 1:16

- ጥበብንና ችሎታን ይሰጥ ነበር
    - ✓ ለባስልኤል እና ኤልያብ የእጅ ጥበብ ሙያ ዘጸ 31፡1-6
- ሕዝብን የመምራት እና የአስተዳደር ጥበብ/ችሎታ
    - ✓ ለዮሴፍ ዘፍ 41፡38-44
    - ✓ ለሙሴና 70 ሽማግሌዎች ዘኁ 11፡14-17, 25-29
    - ✓ ለጎቶንያል መሳ 3፡9-10
    - ✓ ለጌዴዎን መሳ 6፡34
    - ✓ ለሳምሶን መሳ 14፡19, 15፡14
    - ✓ ለሳዖል 1ሳሙ 10፡10
    - ✓ ለዳዊት 1ሳሙ 16፡13
- ለነቢያት ትንቢትን ይሰጥ ነበር ሕዝ 2፡14, 11፡1,5

## 6. የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች ጌታ ኢየሱስ በምድር በነበረበት ዘመን

- አጥማቂው ዮሐንስ
    - በማኅጸን ሳለ መንፈስ ቅዱስን ተሞላ ሉቃ 1፡15
    - መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ላይ ሲመጣ አየ ማቴ 3፡16, ዮሐ 1፡32
    - ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ እንደሚያጠምቅ ተናገረ ማር 1፡7-8

- ጌታ ኢየሱስ
    - ጌታ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ተጸነሰ ሉቃ 1፡35, ማቴ 1፡18
    - መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ላይ በአካል መልክ ወረደ ሉቃ 3፡21-22
    - ጌታ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ
    - ወደምድረበዳ ሄደ ማር 1፡12, ማቴ 4፡1
    - በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይጓዝ ነበር ሉቃ 4፡14
    - በመንፈስ ቅዱስ ቅባት ተቀብቶ ሰበከ ሉቃ 4፡18
    - በመንፈስ ቅዱስ አጋንንትን ያወጣ ነበር ማቴ 12፡28
    - በመንፈስ ቅዱስ ሐሴት ያደርግ ነበር ሉቃ 10፡21
    - በመንፈስ ቅዱስ ራሱን ለመስዋዕትነት አቀረበ ዕብ 9፡14
    - በመንፈስ ቅዱስ ከሙታን ተለይቶ ተነሳ ሮሜ 8፡11

## 7. መንፈስ ቅዱስና ቤተክርስቲያን

- መንፈስ ቅዱስ በአዲስ ኪዳን አማኞች ሁሉ ላይ እንደሚወርድ በትንቢት መጻሕፍት ተጽፎ ነበር። ኢዩኤል 2:28, ሕዝ 36:27, ኢሳ 44:3
- ጌታ ኢየሱስ ስለመንፈስ ቅዱስ ያስተማረው ትምህርት።
  - በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ መንፈስ ቅዱስን ይቀበላሉ — ዮሐ 7:39
  - መንፈስ ቅዱስ ለዘላለም ከቤተክርስቲያን ጋር ይኖራል። — ዮሐ 14:15
  - የሚኖረውም በአማኙ ሥጋ ውስጥ ነው — ቁ 17, 1ቆሮ 6:19
  - አብ መንፈስ ቅዱስን የሚልከው በኢየሱስ ስም ነው — ቁ 25
  - መንፈስ ቅዱስ የመጣው ከአብ ዘንድ ነው — ዮሐ 15:26
  - የተማርነውን ያስታውሳል፣ ያልተማርነውን ደግሞ ያስተምራል — ዮሐ 14:26
  - ስለ ኢየሱስ ይመሰክራል — ዮሐ 15:27
  - ዓለምን በሶስት ጉዳዮች ይወቅሳል — ዮሐ 16:8

    ስለ ኃጢአት - በኢየሱስ አያምኑምና

    ስለ ጽድቅ - ኢየሱስ ወደአብ ሄዷልና። በዚህም ኃጢአተኛ ወደ አብ መድረስ የሚችለው በቀኙ በተቀመጠው በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መሆኑን ያሳውቃቸዋል።

    ስለ ፍርድ - የዚህ ዓለም ገዢ ዲያብሎስ ተፈርዶበታልና። በመሆኑም ሰዎች በኢየሱስ አማካይነት ከሰይጣን ኃይል ነፃ መውጣት ይችላሉ።
  - ወደ እውነት ሁሉ ይመራል፣ ከኢየሱስ ወስዶ ይነግረናል፣ ኢየሱስን ያከብራል — ዮሐ 16:12

## 8. አማኝና መንፈስ ቅዱስ

መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ሕይወት ውስጥ የሚፈጽማቸውን ልዩ ልዩ አሠራሮች መጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ስያሜ ይጠራቸዋል። ከእነዚህ አሠራሮች ውስጥ የመጀመሪያዎቹ አራቱ አማኙ አንድ ጊዜ የሚካፈላቸው ሲሆኑ "በመንፈስ ቅዱስ መሞላት" ግን በእድሜ ዘመኑ ሁሉ ቀጣይ የሆነ አሠራር ነው።

<u>*መንፈስ ቅዱስን "መቀበል"*</u>

- ጌታ አማኞች መንፈስ ቅዱስን እንደሚቀበሉ አስቀድሞ ተናገረ። ዮሐ 7:39, 20:22
- ኃይልን፣ ስጦታን መቀበል ተብሏል — ሐዋ 1:8, 2:38
- አማኞች መንፈስን ተቀበሉ — ሐዋ10:47,19:2,1ቆሮ 6:19
- <u>ዓላማው</u>:- አማኝ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሕብረት መጀመሩን ማረጋገጫ ነው። የአማኙም ሥጋ ቤተመቅደስ መሆኑን ያበስራል።

**<u>በመንፈስ ቅዱስ "*መጠመቅ*"</u>**

- 4 ጊዜ በወንጌላት 2 ጊዜ በሐዋ *ሥራ* ተጽፏል
- በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው
  ማቴ 3:11, ማር 1:8, ሉቃ 3:16, ዮሐ 1:33
- አማኞች ተጠመቁ ሐዋ 1:5, 11:16
- <u>ዓላማው</u> አማኙን በክርስቶስ አንዲት አካል (ዓለማቀፋዊቷ ቤተክርስቲያን) ውስጥ ብልት አድርጐ መግጠም ነው:: 1ኛቆሮ 12:13

**<u>በመንፈስ ቅዱስ "*መታተም*"</u>**

- ቃሉን ሰምቶ በኢየሱስ ያመነ ሁሉ ይታተማል ኤፌ 1:13
- <u>ዓላማው</u>:- በሰማይ ለተዘጋጀልን ርስት መያዣ ነው:: ኤፌ 1:14
  ለቤዛ ቀን ዋስትና እንዲሆነን ነው:: ኤፌ 4:30

* ከእግዚአብሔር አስፈሪ ፍርድ የምናመልጠው በመታተማችን ምክንያት ነው::

**<u>በመንፈስ ቅዱስ "*መቀባት*"</u>:-** መሾም፣ ሥልጣን መቀበልን ያሳያል::

- በብሉይ ኪዳን የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ በሆነው የተቀደሰ ቅባት የሚቀቡ ካህናትና ነገሥታት ነበሩ:: ዘፀ 28:41
- ክርስቶስ እኛን በደሙ መንግሥትና፣ ካህናት አድርጐናል:: ራዕ 5:9,10, 20:4-6
- ክርስቶስ የተቀባ ማለት ነው::
- ጌታ ራሱ በመንፈስ ቅዱስ የተቀባ ነበረ ሉቃ 4:19, ሐዋ 4:26
  ምክንያቱም እርሱ ካህንም ንጉሥም ነው ዘካ 6:13
- አማኞችም ከዚሁ ቅባት (መንፈስ ቅዱስ) ተቀብለዋል 1ዮሐ 2:20
- የተቀበሉትም ቅባት በእነርሱ ውስጥ ይኖራል 1ዮሐ 2:27

**<u>ዓላማው</u>:-**

* መቀባት እግዚአብሔር የሰጠንን የአገልግሎት ዓላማ ለመፈጸም ይጠቅማል ሉቃ 4:19

* የእግዚአብሔርን እውነት ሁሉ ለማወቅ ይጠቅማል ዮሐ 2:20

## በመንፈስ ቅዱስ "መሞላት"

- አንድን የእግዚአብሔር ሥራ ለመሥራት አማኝ የግድ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ይኖርበታል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ከተሞሉ በኋላ የሚፈጽሙት አንድ ተልዕኮ ይኖራቸው ነበር፡፡
  - ባስልኤል + መንፈስ ሞላበት = የመቅደሱን ዕቃ ሠራ ዘፀ 31:1-6
  - ኢያሱ + መንፈስ ሞላበት = ሕዝቡን መራ ዘዳ 34:9
  - አጥማቂው ዮሐንስ + መንፈስ ሞላበት = ሕዝቡን ወደአምላክ መለሰ ሉቃ 1:15
  - ኤልሳቤጥ + መንፈስ ሞላባት = ስለማርያምና ስለጌታ ተናገረች ሉቃ 1:41
  - ዘካርያስ + መንፈስ ሞላበት = ትንቢት ተናገረ ሉቃ 1:67
  - ሐዋርያት + መንፈስ ሞላባቸው = በልሳኖች ተናገሩ ሐዋ 2:4
  - ሐዋርያት + መንፈስ ሞላባቸው = ቃሉን በግልጥ ተናገሩ ሐዋ 4:31
  - እስጢፋኖስ + መንፈስ ሞላበት = ኢየሱስን በሰማይ ቆሞ አየ ሐዋ 7:55
  - አማኞች + መንፈስ ይሙላባችሁ = ለጌታ ዘምሩ ኤፌ 5:18

- የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በተደጋጋሚና በቀጣይ በአማኙ የሕይወት ዘመን ሁሉ የሚፈጸም ነው፡፡
  - ሐዋርያት መንፈስ ሞላባቸው ሐዋ 2:4
    - ✓ በሐዋ ሥራ ምዕራፍ 2 ላይ ካለው የአገልግሎት ሸክም እና ስፋት የበለጠ ሥራና ፈተና ስለተጋረጠባቸው የበለጠ ልምምድ ያስፈልጋቸው ነበር፡፡
  - ሐዋርያት በድጋሚ መንፈስ ሞላባቸው ሐዋ 4:31
  - እስጢፋኖስ መንፈስ ቅዱስ የሞላበት ሰው ነበረ ሐዋ 6:5
    - ✓ የመጣበትን የሞት አደጋ በምስጋና ለመቀበል እና ጠላቶቹን ለመባረክ እንዲችል ተጨማሪ ሙላት እና ኃይል ያስፈልገው ነበር፡፡
  - እስጢፋኖስ መንፈስ ሞላበት ሐዋ 7:55
  - አማኞች ሁል ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ ታዘዋል ኤፌ 5:18

- በሰው ኃይልና ብርታት የእግዚአብሔርን ሥራ መሥራት ፈጽሞ ስለማይቻል እና በእርሱም ዘንድ ያለ መንፈስ ቅዱስ የሆነ አገልግሎት ተቀባይነት ስለማያገኝ አማኝ ሁል ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ይኖርበታል፡፡ ዘካ 4:6

**9. መንፈስ ቅዱስ አማኙን ባለማቋረጥ ይረዳዋል /ያግዘዋል/**

**ከመዳኑ በፊት:-**

1. ወደ ደህንነት/የዘለዓለም ሕይወት/ ይመራዋል::
   - ሀ. ኢየሱስን ባለማመኑ ይወቅሰዋል ዮሐ 16:8-11
   - ለ. በዳግመኛ ውልደት ያድሰዋል ቲቶ 3:5

**ከዳነ በኋላ:-**

2. ሀ. ከኃጢአት ኃይል ተጽዕኖ ነፃ ያወጣዋል ሮሜ 8:2-10, ቲቶ 2:12
   - ቅጽበታዊ - የኃጢአት ኃይል ከሆነው ሕግ ነፃ ይወጣል 1ቆሮ 15:56, ሮሜ 8:2
   - ቀጣይ - ከኃጢአት ልምምድ እየተላቀቀ ጽድቅን ይለማመዳል ኤፌ 6:17, ዮሐ 8:31

   ለ. የዘላለም ሕይወት እንዳገኘ ለውስጡ ይመሰክርለታል ሮሜ 8:16, 1ዮሐ 5:6,8

   ሐ. መንፈሳዊ ሕይወት እንዲኖረው ኃይልን ይሰጠዋል

   መ. ወደ እውነት ሁሉ ይመራዋል ዮሐ 16:13

   ሠ. ሁሉን ነገር ያስተምረዋል ዮሐ 14:26, 1ዮሐ 2:27

   ረ. ለአገልግሎት ኃይልን ይሰጠዋል ሐዋ 1:8

   ሰ. የጸጋ ሥጦታዎችን ይሰጠዋል 1ቆሮ 12:7-11

   ሸ. ለጸሎት ኃይልን ይሰጠዋል ይሁ 20, ኤፌ 6:18, ሮሜ 8:26

   በ. እግዚአብሔርን ለማመስገን እና ለማምለክ እንዲችል ብቃትን ይሰጠዋል::
   ሐዋ 2:11, ሐዋ 10:46, ፊል 3:3, ኤፌ 5:18, ዮሐ 4:24

   ተ. የመንፈስ ፍሬዎችን እንዲያፈራ ያደርገዋል ገላ 5:22

   ቸ. ለሚሞት ሥጋው ሕይወትን ይሰጠዋል ሮሜ 8:11

**10. የመንፈስ ቅዱስ የአሠራር ለውጦች በሁለቱ ኪዳኖች**

የኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ላይ ደም እና የመቤዥት ሥራ መንፈስ ቅዱስ በሚሠራው ሥራ ላይ ሁለት ዓይነት ታላላቅ ለውጦችን አስከትሏል::

**<u>በብሉይ ኪዳን ዘመን</u>**

1. በሁሉም የእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ መንፈስ ቅዱስ አይመጣም ነበር:: የሚመጣባቸው ነቢያት ወይም ነገሥታት ነበሩ::
2. ሥጋቸው በዋጋ ባለመገዛቱና የራሳቸው በመሆኑ መንፈስ ቅዱስ አስፈላጊ ሲሆን ጥሏቸው ይሄድ ነበር::

<u>በአዲስ ኪዳን</u>

1. በሥጋ ለባሹ አማኝ ሁሉ ላይ ይፈሳል:: ሐዋ 2:17
2. የአማኙ ስጋ በዋጋ ስለተገዛና፣ የራሱ ሥጋ ስላይደለ መንፈስ ቅዱስ ለዘላለም በአማኙ ውስጥ ይኖራል:: ዮሐ 14:15-17, 1ቆሮ 6:19

## 11. የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች

የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች የምንላቸው እግዚአብሔር ለአማኞች በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ልዕለ ተፈጥሮአዊ (Supernatural) የሆኑ ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን ነው::

- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመነ አማኝ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታ ይሰጠዋል 1ቆሮ 12:7, 11; 14:26, 31, 1ጴጥ 4:10
- አማኞች ሁልጊዜ በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ ታዘዋል ኤፌ 5:18
- የሚበልጥን የጸጋ ስጦታ እንዲፈልጉ ታዘዋል 1ቆሮ 12:31, 1ቆሮ 14:5
- ስለመንፈስ ስጦታ አጠቃቀም እንዲያውቁ ተመክረዋል 1ቆሮ 12:1
- መንፈሳዊ ስጦታን በብርቱ ፈልጉ ተብሏል 1ቆሮ 14:1
- በተሰጣቸው ስጦታ መጠን እንዲያገለግሉ ታዘዋል 1ጴጥ 4:10
- በጸጋ ስጦታ ለመጠቀም ቅድመ ሁኔታው ፍቅር ነው 1ቆሮ 13:1-1

ፍቅር - ለእግዚአብሔር (ከአገልግሎታችን ይልቅ እርሱን መውደድ)
ፍቅር - ለሕዝቡ (በጸጋ ሥጦታችን መታነጽ እንጂ መሰናከል የለባቸውም)

### የጸጋ ስጦታዎች ዓላማ

### ለምን የጸጋ ስጦታ ለአማኞች ሁሉ ተሰጠ?

ሀ. የክርስቶስን አካል /ቤተክርስቲያንን/ ለማነጽ 1ቆሮ 14:12
ለ. ቤተክርስቲያን ጌታዋ እስኪመጣ ድረስ የተሰጣትን ኃላፊነት እንድትወጣ 1ቆሮ 1:7
ሐ. የአማኙን ሕይወት ለማነጽ 1ቆሮ 14:4

☞ አማኙ በጸጋ ስጦታዎች ቤተክርስቲያንን ካገለገለ በኋላ ክብሩን ሁሉ ለእግዚአብሔር በመስጠት ራሱን በትህትና ዝቅ ማድረግ አለበት ሉቃ 17:10

**የጸጋ ስጦታዎች ዝርዝር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ**

1. <u>ሐዋርያነት</u>
2. <u>ነቢይነት</u>
3. ወንጌላዊነት
4. እረኝነት
5. አስተማሪነት

(1–5) The 5 Offices
5ቱ ቢሮዎች

- ሐዋርያት እና የአዲስ ኪዳን ነቢያት በዋነኛነት የአንዲቷን ዓለማቀፋዊት ቤተክርስቲያን መሠረት (አስተምህሮ) ለመመሥረት ያገለገሉ ሲሆን (1ቆሮ 3:10, ኤፌ 2:20) የቀሩት ደግሞ በተመሠረተው መሠረት ላይ የሚያንጹ ናቸው። (1ቆሮ 3:10-14)

6. ተዓምራት ማድረግ
7. የመፈወስ ስጦታ
8. እርዳታ ማድረግ (Helps)
9. መግዛት፣ ማስተዳደር (Administration)
10. በልዩ ልዩ ልሳኖች መናገር
11. ልሳኖችን መተርጐም
12. ጥበብን መናገር
13. እውቀትን መናገር
14. እምነት
15. መናፍስትን መለየት
16. ትንቢት (1ቆሮ 14:31)
17. አገልግሎት (Serving)
18. መምከር (Encouraging)
19. መስጠት (Contributing)
20. ምህረት ማድረግ
21. መዝሙር
22. መግለጥ
23. ማግባት
24. አለማግባት

**ጥቅሶች፡-** 1ቆሮ 12:28, 1ቆሮ 12:8-10, ኤፌ 4:11, ሮሜ 12:6-8, 1ቆሮ 7:7, 1ቆሮ 14:26

**በልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖች መናገር**

ከጸጋ ስጦታዎች ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ልዩ ማብራሪያ እና ትምህርት የተሰጠበት ስጦታ በ"**ልሳኖች መናገር**" የተባለው ስጦታ ነው:: ይህ ስጦታ የተሰጣቸው አማኞች ስለስጦታው ምንነትና አጠቃቀም ዕውቀት ከሌላቸው ጉባኤውን ስለማያንጹበት ጌታ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ምዕራፍ የሚሸፍን ማብራሪያ ሰጥቶበታል::

1. በልሳኖች መናገር አስቀድሞ ትንቢት የተነገረለት ስጦታ ነው:: ኢሳ 28:11, 1ቆሮ 14:21
2. ጌታ ኢየሱስም በእርሱ የሚያምኑ ከሚቀበሏቸው ስጦታዎች አንዱ በአዲስ ቋንቋ መናገር እንደሆነ ተናግሮ ነበር ማር 16:17
3. መንፈስ ቅዱስ በወረደባቸው ወቅት ሰዎች በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ነበር:: ሐዋ 2:4; 10:46; 19:6
4. ልሳን ቋንቋ ተብሏል

| | | |
|---|---|---|
| ሐዋ 2: | ቁ 4 | በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር |
| | ቁ 6 | እያንዳንዱም በገዛ ቋንቋው ሲናገሩ ይሰማ ስለነበር |
| | ቁ 8 | የተወለድንበትን የገዛ ቋንቋችንን እንዴት ... |
| | ቁ 11 | በልሳኖቻችን ሲናገሩ እንሰማቸዋለን |

ሐዋ 10:46, 11:15

<u>የልሳን አጠቃቀም በጉባኤ (በጌታ የተሰጠ መመሪያ) (1ቆሮ 14:)</u>

- ልሳን ካልተተረጐመ ጉባኤውን አያንጽም ቁ 1-5
- ንግግሩ ባይተረጐም በልሳኖች ከሚናገር የትንቢት ቃል የሚናገር ይበልጣል ቁ 5
- ትርጉሙ ካልተገለጠ ለንፋስ እንደመናገር ይቆጠራል ቁ 9
- በልሳን የሚናገር እንዲተረጉም መጸለይ ይገባዋል ቁ 13
- በማህበር እልፍ ቃላት በልሳን ከመናገር አምስት ቃላት በሚታወቅ ንግግር መናገር ይሻላል ቁ 19
- በልሳኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት እንዲሆን እንጂ ለሚያምኑ አይደለም ቁ 21
- ሁሉም በልሳኖች ቢናገሩ የማያምኑ ሰዎች "**አብደዋል**" ይላሉ እንጂ በዚህ ጉዳይ እግዚአብሔርን አያከብሩም ቁ 23
- በማህበር ጊዜ ሁለት ቢበዛ ሦስት ሆነው በተራ እንዲናገሩ ጌታ አዟል ቁ 27
- እነዚህም የሚናገሩት ተርጓሚ ከተገኘ ብቻ ነው ቁ 28
- እግዚአብሔር የሰላም አምላክ ነው እንጂ የሁከት አምላክ አይደለም ቁ 33
- ትዕዛዙ የወጣው ለሁሉም አብያተክርስቲያናት ነው ቁ 33
- ይህ ትዕዛዝ የጌታ ትዕዛዝ ነው:: ቁ 37
- መሪዎች በልሳን መናገርን እንዳይከለክሉ ተጽፏል ቁ 39

## 12. በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚሠሩ ኃጢአቶች

1. *መንፈስ ቅዱስን መሳደብ ማቴ* **12:31**
   - *ኢየሱስ ያደረጋቸውን ተአምራቶች መካድ እና የእርሱን ሥራ ከአጋንንት ሥራ ጋር ማመሳሰል በምድርም በሰማይም ስርየት የሌለው ኃጢአት ነው፡፡*

<u>*ማሳሰቢያ*</u>፡- *መንፈስ ቅዱስን መሳደብና መንፈስን መመርመር እጅግ በጣም የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በመሆኑም አማኝ ሁልጊዜ መንፈስን የመመርመር ግዴታ አለበት* (1ዮሐ 4:1)

2. *መንፈስ ቅዱስን ማታለል / መዋሸት ሐዋ* 5:3,4
   - *በቅዱሳን መካከል የሚደረግ ውሸት እና መንፈስ ቅዱስ አያውቅም ብሎ ማሰብ*
3. *መንፈስ ቅዱስን መፈታተን ሐዋ* **5:9**
4. *መንፈስ ቅዱስን መቃወም ሐዋ* **7:51**
   - *እግዚአብሔር የሚያመጣውን ቃል፣ አለመስማት*
5. *መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን ኤፌ* **4:31**
   - *ከባህሪ ችግር የተነሳ የሚመጣ ኃጢአት ነው ለምሳሌ ቁጣ፣ ንዴት፣ ብስጭት፣ መራርነት ወዘተ* ...
6. *መንፈስ ቅዱስን ማስመረር ኢሳ* **63:10**
   - *ተደጋጋሚ የሆኑ በደሎችን መፈጸም፣ ከጥፋት አለመመለስ*

7. *መንፈስን ማጥፋት 1ተሰ* **5:19**
   - *የጸጋ ስጦታን አለማነሳሳት እና አለመጠቀም ነው፡፡* (2ጢሞ 1:6)

<u>**ከአዘጋጁ**</u>፡- "*መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ*"

*ኤፌ 5:18*


*ዳዊት ፋሲል*

ስ.ቁ. **0917804407**

*ፖ.ሣ.ቁ.* **67** *ጅማ*

**E-mail – niguye2004@yahoo.com**

# የ
# ሥላሴ
# (ሦስትነት)
# አስተምህሮ



**ለማስተማሪያ**
**እና**
**ለጥናት የተዘጋጀ**

በዳዊት ፋሲል

1997/ጅማ

# የ«ሥላሴ»/ሦስትነት ትምህርት

- "ሥላሴ" የሚለው ቃል የግዕዝ ቃል ሲሆን በአማርኛ "ሦስትነት" የሚለውን ፍች ይሰጣል:: በእንግሊዘኛ ቋንቋ **Trinity** የሚለው ሲሆን ይህም **Three-Unity** ወይም "ሶስትነት"-በአንድነት የሚለውን የተሻለ ማብራሪያ ይሠጣል::
- ሥሳሴ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፈጽሞ አይገኝም:: ይሁንና ሀሳቡን የሚገልጥ ትምህርት ግን እናገኛለን::
- በዓለም ላይ ከክርስትና እምነት በስተቀር በየትኛውም ኃይማኖት "ሦስት አካላት ያሉት አንድ አምላክ" የሚል አስተምህሮ አይገኝም:: ይህም ክርስትናን ከሌሎች እምነቶች የሚለየው ዋናው ትምህርት ነው::
- ቃሉ ሲብራራም "**ሦስት አማልክት በአንድነት**" ማለት ሳይሆን "**አንድ አምላክ በሦስት አካላት**" ማለት ነው::
- በሦስትነት የተገለጡት አካላት "አባት" "ልጁ" እና "ቅዱስ መንፈሱ" ናቸው ማቴ **28:19**
- ሦስቱም አካላት እኩል መለኮታዊ ባህርያት አሏቸው:: ማለትም
- ሦስቱ አካላት - በዘለዓለማዊነት
  - በፈጣሪነት
  - ሁሉን በማወቅ (Omniscient)
  - በሁሉ ቦታ በመገኘት (Omnipresent) ወዘተ ፍፁም እኩልነት አላቸው::
- በመለኮታዊ ዕቅድ ሁሉ ውስጥ እያንዳንዱ አካል ተሳትፎ አለው:: እንዲሁም በአንዱ ዕቅድ ውስጥ እያንዳንዱ አካል የተለየ የራሱ የሆነ የሥራ ድርሻ አለው::

በዚህ መሠረት: አባት(አብ) - ዕቅድ አውጪ (The Planner)
ልጁ (ወልድ) - ዕቅዱ የሚፈጸምበት (Agent)
ቅዱስ መንፈሱ - ዕቅዱ ወደ ተግባር እንዲመጣ ኃይል የሚያደርግ ነው:: (Revealer)

**ምሳሌ 1** አብ - ዓለማትን ሊፈጥር ወደደ
ልጁ - አባት በርሱ ዓለማትን ፈጠረበት
ቅዱስ መንፈስ - ሥራውን ያስፈጽም ነበር::
ዕብ **1:1-2**, ቈላ **1:15-17**, ዮሐ **1:3**, ዘፍ **1:2**

**ምሳሌ 2** አብ - ዓለምን ለማዳን ወደደ ልጁን ላከው
ልጁ - ዓለምን ለማዳን ሥጋ ለበሰ
ቅዱስ መንፈስ - ኢየሱስ ራሱን በዘላለም መንፈስ አቀረበ
ዮሐ **3:16**, ዮሐ **1:14**, ዕብ **10:5**, ዕብ **9:14**

## ጥቅሞች

- የሥላሴን ትምህርት በአግባቡ ማወቅ ብዙ ጥቅሞች ያሉት እና መሠረታዊው ጉዳይ ሲሆን ዋነኛ ጥቅሞቹ ግን የሚከተሉት ናቸው፡፡
  1. የምናመልከውን እንድናውቀው ዮሐ 4:22
  2. ስለ ክርስቶስ ማንነት (Christology) እንድናውቅና ራስን ከተቃዋሚው መንፈስ ለመጠበቅ 1ዮሐ 4:1-4
  3. ስለመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ማንነት በመረዳት ከእርሱ ጋር ላለን ሕብረትና ለክርስቲያናዊ ሕይወታችን ጥንቃቄ እንድናደርግ ይጠቅመናል፡፡

## ታሪክ

- በመጀመሪያ አንድ አማኝ ልብ ሊለው የሚገባ ነገር ቢኖር «ሥላሴ» የሚለው ቃል የእግዚአብሔር መጠሪያ ስም አለመሆኑን ነው፡፡ "**ሥላሴ**" የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት የሚያስተምረው የትምህርት ርዕስ እንጂ መጠሪያ ስም አይደለም፡፡ የቃሉ ትርጉም "**ሦስትነት**" ማለት እንደሆነ ልብ ይሏል፡፡
- "**ሥላሴ**" የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመበት ሰው "**ተርቱሊያን**" /Tertulian/ /ከ160-220 ዓ.ም./ የተባለው የቤተክርስቲያን መሪ ነበር፡፡
- ቱርቱሊያን በርሱ ዘመን ለተነሱትና በእግዚአብሔር የአንድነት ሶስትነት ጉዳይ ላይ ግራ ለገባቸውና ጥያቄ ላነሱ ሰዎች በተለይ ኘራግዚያስ/Praxeas/ - ለተባለው ሰው ክህደት ነገሮችን ለማስተማር እና የአምላክን በሦስት አካላት የተገለጠ አንድ አምላክነት ለማብራራት ሲል "በሦስትነት አንድነት" Tri-Unity የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ ተጠቅሟል፡፡
- የሥላሴ አስተምህሮ ወደመሠረታዊ ትምህርትነት እንዲያድግ ያደረገው ቤተክርስቲያን በተለያየ ጊዜ ባደረጋቻቸው ስብሰባዎች ያስተላለፈቻቸው የእምነት መግለጫና ውሳኔዎች ናቸው፡፡ በወቅቱም ቤተክርስቲያን አጠቃላይ ስብሰባዎች እንድታደርግ ያነሳሿት 3 ዋና ዋና ርዕሰ ጉዳዮች ነበሩ
  1. የአምላክ አንድነት እና በሦስት አካላት መገለጥ
  2. የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት
  3. የመንፈስ ቅዱስ አካልነት እና አምላክነት ጥያቄ ነበሩ፡፡

- በእነዚህ ጉዳዮች ላይ እንድትወያይም ዋነኛ ምክንያት የሆኑት በዘመኑ ተነስተው የነበሩ የተለያዩ እንግዳ ትምህርቶች ነበሩ፡፡ እነዚህም አስተምህሮዎች

**1ኛ. ሞናርኪያኒዝም (Monarchianism)**

**1.1 ራስን መለወጥ** (Modalistic Monarchianism)

ይህም አንድ አካል ያለው አምላክ ራሱን በመለዋወጥ እንደ ሦስት ሆኖ ሠራ እንጂ ሦስት አካላት የሉም የሚል ትምህርት

**1.2 በመክበር አምላክ መደረግ** (Adoptionistic monarchianism)

ኢየሱስ በራሱ አምላክ አይደለም:: ነገር ግን እግዚአብሔር በጥምቀት ጊዜ ከፍ ከፍ አድርጎት፣ በማክበር አምላክ አደረገው የሚል ትምህርት

**2ኛ. አርዮሳውያን (Arianism)**

ኢየሱስ ፈጽሞ የባህሪይ አምላክ አይደለም የአብ ፍጥረት እንጂ ከአብ ጋር በመጀመሪያ አልነበረም የሚል ትምህርት

- ከላይ የተዘረዘሩት በወቅቱ እንግዳ የነበሩ ትምህርቶች እየተስፋፉ ሲመጡ ቤተክርስቲያን ደግሞ እውነተኛውን አስተምህሮ ለማስጠበቅ ስትል በ325 ዓ.ም. በኒቂያ ከተማ አጠቃላይ ጉባኤ በማድረግ "ኢየሱስ ክርስቶስ ከአባቱ ጋር እኩል የሆነ መለኮታዊ ባህሪይ አለው" በማለት ወሰነች::
- እንዲሁም በ381 ዓ.ም. መንፈስ ቅዱስ የራሱ የሆነ አካል ያለው መለኮት እና በመለኮታዊ ባህሪይ ከአብና ከልጁ ጋር እኩል እንደሆነ የሚያረጋግጥ ውሳኔ አስተላለፈች::
- እንግዲህ ከእነዚህ ጊዜያት በኋላ የሥላሴ /ሦስት አካላት አንድ አምላክ/ ትምህርት በቤተክርስቲያን የተጠናከረ ትምህርት ተሰጥቶበታል::

## <u>መንፈሳዊውን ነገር በመንፈስ መመርመር</u>

- የመጽሐፍ ቅዱስ አጥኚ የሆነ ደቀመዝሙር የሥላሴን ትምህርት በቀጥታ ዓረፍተነገር የሚገልጽ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ባያገኝም ነገር ግን ይህንኑ አስተምህሮ የሚያብራሩ የተለያዩ ጥቅሶችን ከተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ያገኛል::
- ስለዚህ ደቀመዝሙሩ እግዚአብሔር የሰወራቸው ብዙ ምስጢሮች እንዳሉና (ዘዳ 29:29) እነዚህንም መረዳት የሚችለው በመንፈስ ቅዱስ ላይ በመደገፍ ብቻ እንደሆነ ሊያውቅ ያስፈልጋል:: (1ቆሮ 2:13)
- ሰዎች አንድን ነገር ለማመን (ለመቀበል) የተለያዩ መንገዶችን ይጠቀማሉ::
  - Rationalism /ምክንያታዊነት/ - ተጨባጭ የሆኑ ማስረጃዎችን ወይም ምክንያቶችን በማግኘት ማመን
  - Empiricism (በመሞከር ማረጋገጥ) ለምሳሌ የስሜት ሕዋሳቶችን በመጠቀም በመዳሰስ፣ በመቅመስ ወዘተ ማረጋገጥ
  - Faith (እምነት) - የእግዚአብሔር ቃል ብቻውን መንፈሳዊ ነገሮችን ለመበየን ሥልጣን እንዳለው በማመን መቀበል:: ተጨባጭ በሆኑ ምክንያቶችና፣ በሙከራ የማይደረስባቸውን መንፈሳዊ ነገሮች የምንረዳው በቃሉ ውስጥ የተፃፉትን ሁሉ ያለጥርጥር አምኖ በመቀበል ነው::

## መለኮታዊ ባህርያት

- የሥላሴ አስተምህሮን (The Doctrine of the trinity) በአግባቡ ለመረዳት የመለኮታዊ ባህሪያትን (Divine Essence) ምንነት ማጥናት አስፈላጊ ይሆናል::
- መለኮታዊ ባህርያት የምንላቸው አምላክ ብቻ ሊኖሩት የሚችሉ እና የትኛውም ከአምላክነት ያነሰ ወይም ፍጹም አምላክ ያልሆነ ሊኖረው የማይችል ባህርያት ናቸው::
- እንግዲህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሦስት የተለያዩ አካላት አባት፣ ልጁ፣ እና ቅዱስ መንፈሱ መኖራቸው ግልጽ ሲሆን እነዚህ አካላት ፍፁም መለኮት ለመሆን እነዚህን ባህርያት ሊያሟሉ ይገባቸዋል ማለት ነው::

1. **ሁሉን ማወቅ (Omniscience)**:- ሁሉንም ነገር ማወቅ አምላክ ብቻ ሊኖረው የሚችል ባህርይ ሲሆን ሦስቱም አካላት ይህንን ባህርይ ያሟላሉ::

   አባት: 1ሳሙ 2:3, መዝ 139:1-5, ሮሜ 11:33

   ልጁ: ዮሐ 2:24,25 ሉቃ 6:8, ዮሐ 16:30

   ቅዱስ መንፈሱ: 1ቆሮ 2:10

2. **ሁሉን ማድረግ መቻል (Omnipotent)**

   አባት: ዘፍ 17:1, ኢዮ 42:2, ኤር 32:27

   ልጁ: ዮሐ 1:3, (መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ተአምራት በሙሉ)

   ቅዱስ መንፈሱ: ሉቃ 1:35,ዘካ 4:6

3. **በሁሉ ቦታ መገኘት (Omnipresence)**

   አባት: መዝ 139:7-11, አሞ 9:2-3, ኤር 23:23

   ልጁ: ማቴ 28:20, ቈላ 1:27, 2ቆሮ 3:17, ማቴ 18:20

   ቅዱስ መንፈሱ: መዝ (139):7

4. **ፈጣሪነት**

   አባት: ዘፍ 1:1, ኢሳ 40:28, ኢሳ 44:24

   ልጁ: ዮሐ 1:3, ቈላ 1:15-17, ዕብ 1:10

   ቅዱስ መንፈሱ: ዘፍ 1:2, ኢዮ 33:4, መዝ 104:30

5. **ዘላለማዊነት**

   አባት: ኢሳ 41:4, ኢሳ 44:6, መዝ 90:2

   ልጁ: ራዕ 1:17, ራዕ 22:13

   ቅዱስ መንፈሱ: ዕብ 9:14 (eternal Spirit)

**ማስታወሻ**:- የአምላክን ዘላለማዊነት ከፍጥረት ዘላለማዊነት የሚለየው አምላክ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም (የነበረና የሚኖር) ሲሆን ለእኛ የተሰጠን ዘላለማዊነት ግን ከተፈጠርንበት ቀን ጀምሮ ብቻ የሚኖረው የወደፊቱ ዘላለም ብቻ ነው::

## <u>ሥላሴ በብሉይ ኪዳን</u>

- እግዚአብሔር ሦስት አካላት ያሉት አንድ አምላክ ነው ካልን እርሱ በብሉይ ኪዳን ዘመንም ያው እርሱ ነውና ራሱን ከአንድ በላይ በሆነ አካላት ሲገልጥ ማግኘት ይኖርብናል።
- ብዙ ሰዎች ሥላሴ የአዲስ ኪዳን ትምህርትና መገለጥ ብቻ ይመስላቸዋል። አምላክ ግን በብሉይም ኪዳን ራሱ ከአንድ ወይም ከሁለት አካላት በላይ እንዳሉት በሚያሣይ መልኩ ተገልጧል።
- ይሁን እንጂ አምላክ እስራኤሎችን በዙሪያቸው ካሉት የአህዛብ የአምልኮ ልማድና ከብዙ አማልክት ራሳቸውን እንዲጠብቁ ለማድረግ የእሱን አንድ አምላክነት አጥብቆ ይነግራቸው ነበር። ዘዳ 6:4 ( አንድ አምላክ እንጂ አንድ አካል አይልም)።
- ይህም የሆነበት ምክንያት ከላይ እንደተጠቀሰው አህዛብ ጐረቤቶቻቸው ብዙ አማልክት አምላኪ (Polytheists) ስለነበሩ ነው። በአህዛብ እምነት ሁሉም ነገሮች ለምሳሌ ባህር፣ ሜዳ፣ ተራራ፣ ሰማይ፣ መብረቅ፣ ዝናብ ወዘተ ለእያንዳንዳቸው የየራሳቸው የሆነ አምላክ አላቸው ብለው ያስቡ ነበር። ከዚህም እምነት (henotheism) እስራኤል እንዲጠበቁ እግዚአብሔር ብቻውን የሁሉም ነገሮች አምላክ እንደሆነ ያሳስባቸው ነበር። ኢሳ 45:22, መዝ (96):5

## ሀ. በብሉይ ኪዳን የሚገኙ በርካታ ጥቅሶች እግዚአብሔር ከአንድ በላይ በሆነ አካላት መገለጡን ያሳያሉ።

**1. ዘፍጥረት 1:1 እግዚአብሔር (Elohim)**

“እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ” የሚለው ምንባብ በዋናው የእብራይስጡ (Original) መጽሐፍ ላይ ኤሎሂም ሰማይንና ምድርን ፈጠረ በማለት ይገልጸዋል። በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥም እግዚአብሔር ተብሎ የተተረጐመው ስም በአብዛኛው ሙሴ “ኤሎሂም” ብሎ የፃፈው ነው። (አዲሱ መደበኛ ትርጉምን ተመልከት)

**ኤሎሂም** - የሚለው ቃል የዕብራይስጥ ቃል ሲሆን ይህም ለብዙ ቁጥር የሚያገለግል ነው።

**ኤል** - ኃያል አምላክ (ነጠላ ቁጥር)

**ኤሎሂም** - ኃያላን አምላኮች (ብዙ ቁጥር) የሚለውን ስሜት ሲሰጥ ይህም በአንድ ማሠሪያ አንቀጽ ፈጠረ በሚል መዘጋቱ አንዱ አምላክ ከአንድ በላይ በሆነ አካላት እንደተገለጠ ያሳያል።

**2. ዘፍጥረት 1:26 እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) አለ ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር።**

አለ - *ነጠላ ቁጥር*

በመልካችን እንደምሳሌያችን - ***ብዙ ቁጥር***

- አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር እንፍጠር ብሎ የተማከረው ከመላእክት ጋር ነው ይላሉ። እግዚአብሔር ግን ከማንም ጋር አይመካከምር። እንዲሁም መላእክት በመፍጠር ሥራ ተሳታፊ አይደሉም። ራሳቸው ፍጡራን ናቸውና። ኢሳ 40:13-14, ኢሳ 44:24, ኤፌ 1:11

**3. ዘፍጥረት 3:22 እግዚአብሔር አምላክም አለ ...አዳም ከእኛ እንደአንዱ ሆነ**

አለ - *ነጠላ ቁጥር*

ከእኛ እንደአንዱ - ***ብዙ ቁጥር***

**4. ዘፍጥረት 11:7 እግዚአብሔርም አለ... ኑ እንውረድ ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው**

አለ - *ነጠላ ቁጥር*

ኑ እንውረድ/እንደባልቀው - ***ብዙ ቁጥር***

- ከሁለት አካላት በላይ መሆኑን ያሳያል። ሁለት አካላት ብቻ ቢሆኑ ና! እንውረድ እንጂ ኑ! እንውረድ አይልም ነበርና።

**5. ኢሳያስ 6:8**

*ማንን እልካለሁ* - *ነጠላ ቁጥር*

*ማንስ ይሄድልናል* - ***ብዙ ቁጥር***

## ለ. ሌሎች ጥቅሶች ደግሞ በጣም ግልጽ በሆነ ሁኔታ አምላክ ወይም ጌታ የተባሉ የተለያዩ አካላት መኖራቸውን ያሳያሉ

**1. *መዝሙር* (45):6**

አምላክ ሆይ ዙፋንህ ለዘለዓለም ነው (አንድ አካል)

እግዚአብሔር አምላክህ የደስታ ዘይት ቀባህ (ሌላ አካል)

ይህም አንደኛው አካል እግዚአብሔር አብ ሌላውን የአምላክ አካል ጌታ ኢየሱስን በሥጋው ወራት እንደቀባው ያሳያል (**ዕብ 1:8**)

**2. *መዝሙር* (110):1 "ጌታ ጌታዬን ..."**

- ኢየሱስ አይሁድ እንደሚያስቡት እርሱ ሰው ብቻ (የዳዊት ልጅ) ብቻ ሳይሆን የዳዊት ጌታ፣ የአምላክ አንዱ አካል መሆኑን ለማስረዳት ጥቅሱን በማስረጃነት ተጠቅሞበታል (**ማቴ 22:41-46**)

**3. ኢሳያስ 48:12-16** - በጣም በሚደንቅና በሚገርም ሁኔታ ሶስቱ አካላት የተገለጡበት ጥቅስ ነው።

- *ፊተኛና ኋለኛው ነኝ* - ጌታ ኢየሱስ
- ጌታ እግዚአብሔር - እግዚአብሔር አብ
- *መንፈሱ* - *መንፈስ* ቅዱስ (ሙሉውን ቁጥር በጥንቃቄ አንብበው)

## ሐ. የእግዚአብሔር መልአክ/ THE ANGEL OF YAHWEH

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት በብሉይ ኪዳን ዘመን ውስጥ ራሱን በተለያየ መንገድ ለሰዎች ገልጧል:: ይህም መገለጥ በሥነ-መለኮት ቋንቋ "Theophany" የመለኮት መገለጥ ይባላል:: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው እግዚአብሔር አብን አንድ ስንኳ ያየው እንደሌለና ሊያየውም እንዳይቻለው ይናገራል:: **ዮሐ 1:17** አብን የሚገልጠው ግን ሌላኛው አካል ወልድ (ኢየሱስ ክርስቶስ) ነው:: **ዮሐ 6:46, 14:9 ቈላ 1:15-17,** *ዕብ 1:3*

ኢየሱስ ክርስቶስ (እግዚአብሔር ወልድ) በአዲስ ኪዳን በሥጋ ከመገለጡ አስቀድሞ በብሉይ ኪዳንም ውስጥ በተለያዩ ሁኔታዎች ለሰው ልጆች ይገለጥ ነበር:: ይህም እርሱ ሌላኛው የመለኮት አካል መሆኑን በግልጥ ያሳያል::

- ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን ዘመን ከተገለጠባቸው (Theophany) መንገዶች አንዱ የእግዚአብሔር መልአክ በመሆን ነው::
- (መልእክተኛ) መልአክ መስሎ መገለጡ ግን በአምላክነት ባህሪይ እንጂ በመልአክ ባህሪይ አልነበረም:: ምክንያቱም ኢየሱስ አምላክ እንጂ መልአክ አይደለምና **(ዕብ 1:1-14)**
- <u>ትኩረት</u> የሚከተሉትን ጥቅሶች ስናጠና በመልአክ መልክ የተገለጠው መለኮታዊ አካል እንጂ መደበኛ መልአክ እንዳይደለ በሚያሳየው መለኮታዊ ባህርያት ማወቅ እንችላለን::

**የእግዚአብሔር መልአክ (The Angel of YaHWeH)**

1. ራሱን እግዚአብሔር ብሎ ይጠራል
2. የአብርሃም፣ የይስሐቅ፣ የያዕቆብ <u>አምላክ ነኝ</u> ይላል
3. ስግደት ይቀበላል መደበኛ መላዕክት ግን ስግደት አይቀበሉም (ራዕ 19:10, 22:8)
4. መለኮታዊ የመባረክ ሥልጣን (እኔ) አለው
5. እግዚአብሔር ስለሆነ ለእግዚአብሔር ብቻ የተፈቀደውን መስዋዕት ይቀበላል ወዘተ ...

ከላይ በርዕሱ የተዘረዘሩት ባህርያት ደግሞ የመለኮት ብቻ ባህርያት ሲሆኑ ፍጡር ከቶውኑም እነዚህ ባህርያት ሊኖሩት አይችልም::

**ጥቅሶቹን ልብ ብለህ አጥና**

1. ዘፍጥረት 16:7-14 (መጀመሪያ አንብበው)
   - ሀ. ዘርሽን እጅግ አበዛዋለሁ (ቁ. 10)
   - ለ. ይናገራት የነበረውን የእግዚአብሔርን ሥም (ቁ. 13)
   - ሐ. ኤል - ሮኢ - እግዚአብሔርን አየሁት

2. ዘፍጥረት 22 (መጀመሪያ አንብበው)

ሀ. እግዚአብሔርም ... ቁ. 1 እና ቁ. 11ን አነጻጽር

ለ. የእግዚአብሔር መልአክ (ቁ. 11) አንድ ልጅህን <u>ለእኔ</u> አልከለከልክምና እግዚአብሔርን የምትፈራ እንደሆንህ (ቁ. 12)

ሐ. ያህዌ - ይርኤ - እግዚአብሔር ያያል (ቁ. 14)

መ. መለኮታዊ መባረክ (ቁ. 15-18)

3. ዘፍጥረት 31፡11-13 (መጀመሪያ አንብብ)

ሀ. የእግዚአብሔርም መልአክ በሕልም (ቁ. 11)

ለ. የቤቴል አምላክ እኔ ነኝ (ቁ. 13) ከዘፍ 28፡12-22 ጋር አነጻጽር

4. ዘፍጥረት 32፡22-30 (መጀመሪያ አንብበው)

ሀ. አንድ ሰውም እስከ ንጋት ድረስ ቁ. 24

ለ. ከእግዚአብሔር ከሰውም ጋር ታግለህ (ቁ. 28)

ሐ. እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁ (ቁ. 30)

መ. ጵኒኤል - የእግዚአብሔር መገለጥ (ራዕይ) (ቁ. 30) (ሆሴዕ 12፡4-6)

5. ዘጸአት 3፡2-6 (መጀመሪያ አንብበው)

ሀ. የእግዚአብሔርም መልአክ ... ታየው (ቁ. 2)

ለ. እግዚአብሔር እርሱ (ሙሴ) ይመለከት ዘንድ እንደመጣ ባየ ጊዜ (ቁ. 4)

ሐ. እኔ የአባትህ አምላክ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ (ቁ. 6)

መ. ሙሴም እግዚአብሔርን ያይ ዘንድ ፈርቷልና (ቁ. 6)

ሠ. እግዚአብሔርም አለ (ቁ. 7)

ረ. ያለና የሚኖር (ጀሆቫህ ወይም ያህዌህ) እኔ ነኝ (ቁ. 14)

ሰ. የዕብራውያን አምላክ ተገለጠልን (ቁ. 18)

6. ዘኁልቁ 22 (መጀመሪያ አንብበው)

ሀ. ሲሰገድለት አልተቃወመም (ቁ. 31) ራዕ 19፡10, 22፡8

ለ. ቁ. 35 እና ቁ. 38 አነጻጽር

ሐ. ም. 22 35 እና ም 23፡3-7 አነጻጽር

7. መሳፍንት 2፡1-5 (መጀመሪያ አንብበው)

ሀ. ከግብጽ አውጥቻችኋለሁ (ቁ. 1)

ለ. ለአባቶቻችሁም ወደማልሁላቸው ምድር (ቁ. 1)

ሐ. ከእናንተ ጋር ያደረግሁትን ቃልኪዳን (ቁ. 1)

8. መሳፍንት 6:11-25 (መጀመሪያ አንብበው)

ሀ. እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው (ቁ. 12)

ለ. እግዚአብሔርም ወደ እርሱ ዘወር ብሎ (ቁ. 14)

ሐ. እግዚአብሔር በእርግጥ ከአንተ ጋር እሆናለሁ ... አለው (ቁ. 16)

መ. የምትናገረኝ አንተ እንደሆንህ (ቁ. 17)

ሠ. ቁርባን ይቀበላል (ቁ. 18) (ዘሌ 9:24)

ረ. እስራኤል የእግዚአብሔር መልአክ ማን እንደሆነ ግንዛቤ ነበራቸው ቁ. 22

9. መሳፍንት 13 (መጀመሪያ አንብበው)

ሀ. ማኑሄ ቁርባን ሳይሆን ግብዣ ለማድረግ ፈለገ (ቁ. 16)

ለ. የእግዚአብሔር መልአክ ግን ስለሚቃጠል መስዋት አመለከተው (ቁ. 16)

ሐ. ማኑሄ እግዚአብሔር እንደተገለጠለት ገና አላወቀም ነበር (ቁ 16)

መ. ስሜ ድንቅ ነው (ቁ.18) ከኢሳ. 9:6 ጋር አነፃፅር

ሠ. እግዚአብሔርን አይተናልና ሞት እንሞታለን (ቁ. 22)

ረ. የሚቃጠለውን መሥዋትና የእህሉን ቁርባን ከእጃችን ባልተቀበለን ነበር (ቁ.23)

**መስዋዕት የሚቀበል አምላክ ብቻ እንደሆነ ልብ በል።**

**ፍፁም የሆነ የሶስት አካላት መገለጥ በአዲስ ኪዳን**

- የጌታ ኢየሱስ የምድር አገልግሎት የሚጀምረው ግልፅ በሆነ የሶስት አካላት በአንድነት መገለጥ ነው።
- እንዲሁም በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ በልዩ ልዩ ሥፍራዎች ላይ ሶስቱን አካላት የሚገልጡ ጥቅሶች እናገኛለን።

1. ማቴ 3:16-17 (አንብብ)
    - ልጅ (ወልድ) - በምድር ላይ በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ ይጠመቃል።
    - አባት (አብ) - በሰማይ ውስጥ የምወደው ልጄ ይህ ነው ሲል ይመሰክራል።
    - መንፈስ ቅዱስ - እንደ ርግብ ከሰማይ በልጁ ላይ ይመጣና ያርፋል።
2. ጌታ ኢየሱስ የምድር አገልግሎቱን ሲጨርስም ሥላሴን ያካተተ ትዕዛዝ አዘዛቸው **ማቴ 28:19**

    "በአብ፣ በወልድና፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው።" ከሶስቱ አካላት ያልተጠቀሱ፣ ወይም ያንሳል ተብሎ ያልተካተተ የለም። አንባቢው በዚህ የማጥመቂያ ስልጣን ባለው ስም ውስጥ የፍጥረት ስም ሊገባ ይችላል ብሎ ማሰብ እንዴት ይችላል?
3. 1ቆሮ 12:4-6
    - መንፈስ አንድ ነው (ራሱን የቻለ አንድ አካል)
    - ጌታም አንድ ነው (ራሱን የቻለ አንድ አካል)
    - እግዚአብሔርም አንድ ነው (ራሱን የቻለ አንድ አካል)

4. 2 ቆሮ 13፡14
    - የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ (ወልድ)
    - የእግዚአብሔር ፍቅር (አብ)
    - የመንፈስ ቅዱስ ሕብረት (መንፈስ ቅዱስ)
5. ኤፌ 4፡4-6
    - አንድ መንፈስ (አንድ አካል መንፈስ ቅዱስ)
    - አንድ ጌታ (አንድ አካል ወልድ)
    - አንድ አምላክ የሁሉም አባት (አንድ አካል አብ)
6. 1ጴጥ 1፡1-2
    - እግዚአብሔር አብ
    - መንፈስ
    - ኢየሱስ ክርስቶስ (ወልድ)
7. ይሁዳ 20 - 21
    - በመንፈስ ቅዱስ እየፀለያችሁ
    - የኢየሱስ ክርስቶስ ምህረት (ወልድ)
    - በእግዚአብሔር ፍቅር (አብ)

## የሥላሴ ትምህርት ሶስት መሠረታዊ መግለጫ ነጥቦች

1. እግዚአብሔር ሶስት አካላት አሉት
2. እያንዳንዱ አካል ሙሉ የሆነ መለኮታዊ ባህርያት አሉት
3. እግዚአብአብሔር አንድ አምላክ ነው፡፡

## 1. እግዚአብሔር ሦስት አካላት አሉት

እግዚአብሔር ሦስት አካላት አሉት ስንል አንዱ አካል ራሱን እየለዋወጠ በሶስት አካላት መልክ ይገለጣል ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን እያንዳንዱ ራሱን የቻለ ሶስት አካላት አሉት ማለት ነው፡፡ ይህም አብ ወልድ አይደለም ወልድ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ አይደለም ማለት ነው፡፡ ይልቁንም አብ ራሱን የቻለ አንድ አካል፣ ወልድም ሌላ አካል፣ መንፈስ ቅዱስም ሌላኛው አካል ማለት ነው፡፡

**ጥቅስ**፡- ዮሐ 1፡1, ዮሐ 17፡2, 1ዮሐ 2፡1, ዕብ 7፡25, ዮሐ 14፡26

**2. እያንዳንዱ አካል ሙሉ የሆነ መለኮታዊ ባህርያት አሉት**

አስቀድመን እንዳጠናነው መለኮታዊ ባህርያት ስንል ፍፁም አምላክ ከሆነ ከእግዚአብሔር በቀር ማንም ፍጥረት ሊኖረው ወይም ከአምላክ ጋር ሊጋራው የማይችል ብቸኛ ባህርያት ማለት ናቸው። ከአምላክ ያነሰ ወይም ፍጡር እነዚህ ባህርያት ሊኖሩት አይችሉም። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱሳችንን በጥንቃቄ ስናጠና እግዚአብሔር አብ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እያንዳንዳቸው እነዚህ ፍፁም መለኮታዊ ባህርያት አሟልተው እናገኛለን።

**ጥቅስ፡-** **ዘፍ 1፡1, ዮሐ 1፡3, ኢዮ 33፡4, ዘካ 14፡3-5, 1ተሰ 3፡11-13, ኢሳ 44፡6, *ራዕ* 1፡17, *ሐዋ* 5፡3,4, ሮሜ 8፡11, *ሐዋ* 2፡24, 32, 1ቆሮ 2፡10-11 ወዘተ...**

**3. እግዚአብሔር አንድ አምላክ ነው።**

በሦስት አካላት የተገለፀው እግዚአብሔር በሰብአዊ ስሌት የሚሰላ ማንነት የለውም። ስለሆነም አንድ አይነት መለኮታዊ ባህርያት ያሉት፣ የማይነጣጠል መለኮታዊ ሥልጣን ያለው አንድ አምላክ ነው። እግዚአብሔር አንድ አምላክ እንጂ ሦስት አማልክት ፈጽሞ አይደለም።

**ጥቅስ፡-** **ዘዳ 6፡4, *ማር* 12፡29, *ያዕ* 2፡19, ዮሐ 10፡30, ዮሐ 5፡44, ይሁ 25, 1ቆሮ 8፡4-6, 1ጢሞ 2፡5**

## የጥንታዊቷ ቤተክርስቲያን የእምነት መግለጫ

**የሐዋርያት የእምነት መግለጫ** (The Apostles creed)
(3ኛና 4ኛ መቶ ክ.ዘ.)

"ሰማይንና ምድርን በሠራ፣ ሁሉን ማድረግ በሚችል በእግዚአብሔር አብ (አባት) አምናለሁ"
"አንድያ ልጁ በሚሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስም አምናለሁ፣ በመንፈስ ቅዱስ በተፀነሰ፣ ከድንግል ማርያም በተወለደ፣ በፖንቲየሱ ጲላጦስ መከራን በተቀበለ፣ በተሰቀለ፣ በሞተ፣ በተቀበረ፣ በሶስተኛ ቀን ከሙታን በተነሳው፣ ወደሰማይ ባረገው፣ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ(አባት) ቀኝ በተቀመጠው፣ በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ ዳግመኛ በሚመጣው።"

"በመንፈስ ቅዱስም አምናለሁ" በአንዲት ቅድስት ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን በቅዱሳን አንድነት "በኃጢአት ይቅርታ፣ በሙታን ትንሣኤ፣ እና በዘላለም ሕይወት አምናለሁ"

-አሜን-

ይህ በጥንታዊቷ ቤተክርስቲያን አማኞች ሁሉ ዘንድ ይታወቅ የነበረ የእምነት መግለጫ ነው። በኋላም በኒሲያ አገር (325 ዓ.ም.) እና በኮንስታንቲኖፕል አገር (በ381 ዓ.ም.) ይኸው የእምነት መግለጫ በተብራራ መልኩ የቤተክርስቲያን የእምነት መግለጫ እንዲሆን ተወስኗል።

"አንባቢ ሆይ ከላይ የተዘረዘረውን የእምነት መግለጫ ከልብህ የምታምን ከሆነ አንተ ከጥንታዊቱ ቤተክርስቲያን አባላት አንዱ ነህ ማለት ነው።"

"This is a subject on which we know nothing except what is revealed"

Christian Catechism

## ዋቤ መጻሕፍት
## (References)


1. ቄስ ኮሊን ማንሰል (1995) "ትምህርተ እግዚአብሔር" አ.አ
2. ቄስ ኮሊን ማንሰል (1998) "ትምህርተ ክርስቶስ" አ.አ
3. ቄስ ኮሊን ማንሰል (1999) "ትምህርተ መንፈስ ቅዱስ" አ.አ
4. Macled. D (2005), Shared Life – The trinity and the fellowship of God's people.
5. Grudem W. (1999) "Bible doctrine" Michigan.
6. Lawson R. (2003) "Christian Catechism, London.


<u>ከአዘጋጁ</u>:- "የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከአንተ/ከአንቺ ጋር ይሁን"

አሜን


☞ ***ዳዊት ፋሲል***

**ስ.ቁ. 0917804407**

***ፖ.ሣ.ቁ. 67 ጅማ***

E-mail – niguye2004@yahoo.com

# ሕግ እና ፀጋ

# (Law Vs Grace)





ለማስተማርያና ለጥናት
የተዘጋጀ
በዳዊት ፋሲል

# <u>ሕግ እና ጸጋ (Law Vs Grace)</u>

*"ኃጢአት አይገዛችሁምና ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁምና" ሮሜ 6:14*

## 1. ሕግ ምንድን ነው?

**<u>የሕግ አከፋፈል</u>:-**

**ሕግ**

**የተፈጥሮ ሕግ (God's Natural Law)**

<u>አይሻሩም አይለወጡም</u>

- በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ በብዛት ይገኛሉ ለምሳሌ:- የጨለማና ብርሃን መፈራረቅ፣ የተክሎች መብቀል፣ የሴቶች በጭንቅ ፅንሶ መውለድ፣ የሚስት ፈቃድ ወደባል መሆንና የእርሱ ገዥነት ወዘተ... 1ቆሮ 14:34፣ ኤፌ 5:22
- የዓለም ሕዝብ ሁሉ የሚጠቀምባቸው ናቸው::

**የሙሴ ሕግ (ትዕዛዝ) (Mosaic Law)**

ለእስራኤላዊያን የተሰጠ የሥነ-ምግባርና የአምልኮ መመሪያ ነበር (ሮሜ 3:1-2፣ 9:4)

**የሙሴ ሕግ ለሦስት ይከፈላል**

**(Codex 1)**

**የኃይማኖት ሕጎች (Religious laws)**

በአብዛኛው በዘፀአትና በዘሌዋውያን መጻሕፍት ውስጥ ይገኛሉ::

**Codex 2)**

**10ቱ ትዕዛዛት (The Ten Commandments)**

የሁለቱ ሕጎች መጠቅለያ ሃሳቦች የሆኑ ሕጎች ናቸው:: ዘፀ 20:1-17

**(Codex 3)**

**የማሕበረሰብ ሕጎች (Social laws)**

በአብዛኛው በዘዳግም ውስጥ ይገኛሉ::

**<u>የሙሴ ሕግ</u>:-**

- የሙሴ ሕግ "የሕግ ሥራ" ወይም "የሥራ ሕግ" ብለን ልንጠራው እንችላለን (ሮሜ 3:20፣ 27-28 ገላ 2:16)
- ምክንያቱም እንደ ጸጋ "በእምነት" የሚገኝ ሳይሆን ሕጉን በሙሉ መፈጸም (ሥራ) ስለሚጠይቅ ነው ገላ3:10
- የሙሴ ሕግ "ትዕዛዝ" ተብላም ትጠራለች (ሮሜ 7:9-11)
- የተሻረው ሕግ ይሄው የሙሴ ሕግ እንጂ የተፈጥሮ ሕጎች ፈጽሞም አይሻሩም፣ በቀጣይነት እስከ ዓለም ፍጻሜ ይዘልቃሉ::
- የሙሴ ሕግ (ትዕዛዝ) ግን ሰውን ለማጽደቅ የማትጠቅም ስለሆነች ተሽራለች (ዕብ7:18)

## 2. የሕግና የጸጋ ተቃርኖ

ሕግና ጸጋ በተለያዩ አገላለጾች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተቃርኖ ባለው መልኩ ተነጻጽረው ተቀምጠዋል።

| ሕግ (ሥራ) | ጸጋ (እምነት) |
|---|---|
| በሙሴ ተሰጥቶ ነበር | በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ (ዮሐ1:17) |
| እስራኤልና አባቶቻቸው ሊሸከሙት ያልቻሉት ቀንበር (ሐዋ15:10፣ ገላ5:1) | ልዝብ ቀንበር (ክርስቲያናዊ ነጻነት ነው (ማቴ 11:28-30፣ ገላ5:1) |
| ልብን የሚያውክና የሚያናውጥ (ሐዋ15:24) | ሰላም ይሰጣል (ሮሜ 5:1-2) |
| ከሰዎች ጽድቅ ይጠይቅ ነበር (ሮሜ 10:3) | የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው (ሮሜ3:21) |
| ከሥራ የሆነ ጽድቅ ነበር (ሮሜ9:30-33) | ከእምነት የሆነ ጸድቅ ነው (ሮሜ3:22፣27) |
| አሮጌው የፊደል ኑሮ | አዲሱ የመንፈስ ኑሮ (ሮሜ 7:6) |
| የኃጢአትና የሞት ሕግ | የሕይወት መንፈስ ሕግ (ሮሜ8:2) |
| የሞት አገልግሎት | የመንፈስ አገልግሎት (2ቆሮ3:7) |
| የኩነኔ አገልግሎት | የጽድቅ አገልግሎት (2ቆሮ3:9) |
| ይሻር የነበረ | ጸንቶ ሚኖር (2ቆሮ3:11) |
| በክብር ነበረ | እጅግ ይልቅ በክብር የሆነ(2ቆሮ3:10-11) |
| ሞግዚት | እምነት/ክርስቶስ(ገላ 3:23) |
| ባርያይቱ አጋር | ጨዋይቱ (ሣራ) ገላ 4:21-31) |
| የመስቀል እንቅፋት (ገላ 5:11) | የመስቀሉ ቃል (1ቆሮ1:18) |
| ከሥራ (የሆነ ጽድቅ) | የእግዚአብሔር ስጦታ ኤፌ 2:8 |
| በእጅ የተደረገ መገረዝ ኤፌ 2:11 | በእጅ ያልተደረገ የሥጋን ሰውነት በመግፈፍ መገረዝ ቈላ2:11 |
| ክርስቶስን ለሚያውቅ እንደጉዳት የሚቆጠር | ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ ኤፌ 3:4-9 |
| የዕዳ ጽሕፈት | መስቀል ቈላ 2:14 |
| ጥላ | ክርስቶስ ቈላ 2:16-17 |
| ዓለማዊ፣ የተናቀና፣ የመጀመሪያ ትምህርት ገላ 4:9-11፣ ቆላ 2:21 | ከክርስቶስ ጋር መሞት ቈላ 2:21 |
| ወንጌልን ለሚቃወሙ የተሰራ (1ጢሞ1:8-11) | በኢየሱስ ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ (ሮሜ 3:24) |
| በሙሴ ዘመን የተሰጠ | ከዘለዓለም ዘመናት በፊት የተሰጠን (2ጢሞ 1:9-11፣ ቲቶ 1:1-3) |
| በመላእክት የተነገረ ቃል | በጌታ የተነገረ (ዕብ2:1-3) |
| የምትደክም የማትጠቅምም | ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ የሚሻል ተስፋ (ዕብ 7:18-19) |
| አሮጌ እና ውራጅ | አዲስ (ዕብ8:6-13) |
| እውነተኛ ሳይሆን ጥላ የነበረ | በጎ ነገር (ዕብ10:1) |
| ኃጢአትን ያስታውሳል | የዘላለም ፍጹማን ያደርጋል (ዕብ10:1-4፣14) |
| የናቀው ሰው ያለርኅራኄ ይገደላል | ይልቅ፣ የሚብስ ቅጣት ይገባዋል (ዕብ10:28-31) |

## 3. ሕግ ለምን ተሰጠ?

የሚያደርገው ቢኖር በሕይወት ሊኖርበት(ዘሌ18:5፣ሕዝ20:10፣21 ሮሜ10:5፣ ገላ3:12)

የሰው በደል ብዙ መሆኑ እንዲታወቅ (ሮሜ5:20)

ኃጢአት ምን እንደሆነ ይታወቅ ዘንድ (ሮሜ 3:20፣ 7:7)

- ትንንሽ የሚመስሉ ኃጢአቶች ውጤታቸው ተመሳሳይ (ርግማንና ሞት) ነውና::

ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ እስራኤልን እንደሞግዚት ይጠብቅ ዘንድ(ገላ3:23-25)

የተስፋው ዘር እስኪመጣ ድረስ ስለሕግ መተላለፍ ተጨመረ (ገላ3:19)

አሁንም በዚህ ዘመን ወንጌልን ለሚቃወሙ (ኢ-አማንያን) የተሠራ ነው(1ጢሞ1:6-11)

ሰው ሕግን መፈፀም ሲያቅተው ሌላ መዳኛ መንገድ ይፈልግ ዘንድ(ሮሜ7:14-25)

## 4. በሕግ (በሥራ) ፈጽሞ መጽደቅ የማይቻልበት ምክንያቶች

ምክንያት:-

ሀ. በሕግ መጽሐፍ በተጻፉት ሁሉ ጸንቶ መኖርና ማድረግ (መፈጸም) ካልተቻለ እርግማን ያመጣልና (ገላ 3:10)

ለ. ሰው ሁሉንም ትዕዛዛት ቢጠብቅና አንዲቱን ግን ቢተላለፍ በሁሉ በደለኛ (ተጠያቂ) ይሆናልና (ያዕ 2:10)

| ኃይማኖቶች ነጥብ ሲሰጡ | | | |
|---|---|---|---|
| ሰው | የፈጸመው ሕግ መጠን | ነጥብ | ውጤት |
| 1 | 0/100 | N.G (0) | እጅግ በጣም ኃጢአተኛ |
| 2 | 25/100 | 25 | መደበኛ ሰው |
| 3 | 50/100 | 50 | ጻድቅ |
| 4 | 75/100 | 75 | በጣም ጻድቅ |
| 5 | 99/100 | 99 | እጅግ በጣም ጻድቅ |

- ኃይማኖቶች የሰውን የጽድቅ ሥራ የሚመዝኑት ሰውን ከሌላ ሰው በማነጻጸር ነው::

| የሕግ የነጥብ አሰጣጥ | | | |
|---|---|---|---|
| ሰው | የፈጸመው ሕግ መጠን | ነጥብ | ውጤት |
| 1 | 0/100 | 0 | F ኃጢአተኛ |
| 2 | 25/100 | 0 | F ኃጢአተኛ |
| 3 | 50/100 | 0 | F ኃጢአተኛ |
| 4 | 75/100 | 0 | F ኃጢአተኛ |
| 5 | 99/100 | 0 | F ኃጢአተኛ |

- መጽሐፍ ቅዱስ የሰውን የጽድቅ ሥራ የሚመዝነው በእግዚአብሔር ፊት ነው::

- ሰው "በእግዚአብሔር ፊት" ጻድቅ ሊሆን ወይም "በእርሱ ፊት" ሊነጻ አይችልም ኢዮ4:17
- በዚህ መስፈሪያ ሰው ሲታይ ውጤቱ "ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሏቸዋል" የሚለው ይሆናል(ሮሜ3:23)

ሐ. እንዲህም ቢሆን እንኳ ሕጉ የተሰጠው "ለእስራኤል ሕዝብ" ብቻ ነበር (ሮሜ9:4)

## 5. ማንም ሰው ሕግን ሊፈጽምና ሊጸድቅ አይችልም

1. በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ መሆን አይቻልም:: (ኢዮ 4:17፣ 9:2 ሮሜ 3:20)
2. ከሰው ልጆች መካከል አንድም ስንኳ ጻድቅ የለም:: መዝ(14):2-3)
3. በምድር ላይ ኃጢአትን አድርጎ የማያውቅ ጻድቅ ፈጽሞ አይገኝም:: (መክ7:20)
4. እንኳንስ ኃጢአታችን ጽድቃችንም ብቃትና ተቀባይነት የለውም:: (ኢሳ64:6)
5. ሕግ የእስራኤል አባቶች ሊሸከሙት ያልቻሉት ቀንበር ነው:: (ሐዋ15:10)
6. ሕግን መስበክ የአማኙን ልብ ማወክና በቃል ማናወጥ ነው:: (ሐዋ15:24)
7. አንድም ስንኳ ጻድቅ የለም:: (ሮሜ3:11)
8. ሥጋ የለበሰ <u>ሁሉ</u> ሕግን ሊፈጽምና ሊጸድቅ አይችልም:: (ሮሜ 3:20)
9. በሥራዬ እጸድቃለሁ ማለት ትምክህት ብቻ ነው:: (ሮሜ3:27)
10. ሥጋ የለበሰ ሁሉ የሚወደውን ትቶ የሚጠላውን ያደርጋል:: (ሮሜ7:15-20)
11. በሥጋ ለባሽ ሁሉ ውስጥ የኃጢአት ሕግ (ባህርይ) አለ:: (ሮሜ7:20-25)
12. በሥራ ጽድቅን ማግኘት አይቻልም:: (ሮሜ9:30)
13. ጽድቅ በሥራ ከሆነ ጸጋ "ጸጋ" መሆኑ ይቀራል:: (ሮሜ11:56)
14. ሰው ፈጽሞ የራሱ የሆነ የጽድቅ "ብቃት" የለውም:: (2ቆሮ3:4)
15. ሕግ የሞት እና የኩነኔ አገልግሎት ነው:: (2ቆሮ3:7-9)
16. ሕጉ ክርስቶስን የሚጋርድ መጋረጃ ነው:: (2ቆሮ3:14-16)
17. ሕግን የሚሰብኩ ሐሰተኞች ወንድሞች ብቻ ናቸው:: (ገላ2:4-5)
18. ሕግ የወንጌልን እውነት ይቃወማል:: (ገላ2:5፣14)
19. በሕግ ሥራ መኖር ግብዝነት ሲሆን ሥጋን የለበሰ ሁሉ ፈፅሞ ሊፀድቅበትም አይችልም:: (ገላ2:12-16)
20. ጽድቅ በሥራም ጭምር ከሆነ የክርስቶስ መሞት አስፈላጊ አይደለም:: (ገላ2:21)
21. በሥራ ለመጽደቅ የሚፈልጉ ሁሉ የተረገሙ ናቸው:: (ገላ3:10)
22. ሕግ ከእምነት ጋር ተካፋይነት የለውም:: (ገላ3:12)
23. ሕግ ሕያው ሊያደርግ አይችልም:: (ገላ3:21)
24. ክርስቲያኖች በሕግ ሞግዚትነት ስር አይደሉም:: (ገላ3:23-29)
25. በሕግ ሥራ የሚኖሩ የባርያይቱ የአጋር ልጆች ስለሆኑ አይወርሱም:: (ገላ4:21-31)
26. በሕግ ሊጸድቁ የሚፈልጉ ከክርስቶስ ተለይተዋል፣ ከጸጋውም ወድቀዋል:: (ገላ5:4)
27. ደህንነት የእግዚአብሔር ስጦታ እንጂ በሰው የጽድቅ ሥራ የሚገኝ አይደለም:: (ኤፌ2:8-10)
28. ለሕግ ተገድለን ከሕግ ተፈትተናል:: (ሮሜ 7:1-6)

**የወንጌል እውነት (ኤፌ 2:8)**

**ውጤቶች**

**ፀጋ +እምነት = የዘለዓለም ሕይወት (ሮሜ 3:22)**
**ፀጋ +እምነት = መልካም የጽድቅ ሥራ (ቲቶ 2:11-13)**
**ፀጋ +እምነት = እግዚአብሔርን መምሰል ወዘተ (ቲቶ 2:11-13)**

**ልዩ ወንጌል (ገላትያዊነት- Galatianism) (ገላ 1:6)**

**ውጤቶች**

ሥራ+እምነት = የዘለዓለም ሕይወት

ሥራ+የሥጋ ጥረት (ድካም) = መልካም የጽድቅ ሥራ (ገዳማዊነት-Celibacy)
(1ጢሞ4:1-5)

ሥጋን ማጎሳቆል = እግዚአብሔርን ለመምሰል (Hermitism) (ቈላ 2:16-23)

- ይህን ልዩ ወንጌል በቤተክርስቲያን የሚያስተምሩና ትምህርቱን የሚቀበሉ ቢኖሩ
  1. የሳቱና፣ የሚናገሩትን የማያስተውሉ ናቸው (1ጢሞ 1:6-7)
  2. ትምህርታቸው ከንቱ ነው(1ጢሞ1:7)
  3. እግዚአብሔርን የሚፈታተኑ፣ልብን የሚያውኩ እና በቃል የሚያናውጡ ናቸው ሐዋ15:10፣24፣ ገላ 5:11
  4. የተረገሙ ናቸው ገላ 1:6-9
  5. ሾልከው በስውር የገቡ ሐሰተኞች ወንድሞች ናቸው ገላ 2:4
  6. ግብዞች ናቸው ገላ 2:13፣1ጢሞ 4:1-2
  7. ትምክህተኞች ናቸው ሮሜ 3:27፣ ኤፌ 2:10

## 6. ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ (ቲቶ 2:11)

**ጸጋ ምን ማለት ነው?**

- ጸጋ ማለት ለማይገባው ማንነት (ሰው) የሚሰጥ ነጻ ስጦታ ማለት ነው (ሮሜ. 3፣23)
- ጸጋ በሰው ልፋትና የጽድቅ ሥራ የሚገኝ ሳይሆን እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሠራውን የተጠናቀቀ የደህንነት ሥራ በማመን ብቻ የራሳችን የምናደርገው ለኃጢአተኞች የተዘጋጀ የደህንነት መንገድ ነው:: (ሮሜ.4:4)
- በመሆኑም እጅግ ንጹሕና ቅዱስ የሆነው ፈጣሪ አምላክ እጅግ በጣም ኃጢአተኛ ከሆነ ሰው ጋር የሚገናኝውና ሕብረት የሚያደርገው በጸጋ አማካኝነት ብቻና ብቻ ነው::

- ጸጋ በዓለም ላይ ከሚፈጸመው ኃጢአት በሙሉ ከመጠን ይልቅ የሚበልጥና በእምነት ለሚቀበሉት ሁሉ ደህንነትን (የዘላለም ሕይወትን) የሚያሰጥ የእግዚአብሔር የማዳን አሠራር ነው። (ሮሜ 5፡15-21)
- ጸጋ እኛ በጎ ወይም ክፉ በማድረጋችን የምናገኘው ወይም የምናጣው ሳይሆን (ሮሜ 9፡10-18) ኢየሱስ ክርስቶስን የግል አዳኛችን አድርገን በእምነት በመቀበል ብቻ የምናገኘው በመሆኑ በሥራ እንደጸደቀ ሰው ፈጽሞ በራሳችን ልንመካ አንችልም። ጸጋው ያለምንም ሥራ አድኖናልና። (ኤፌ 2፡8)
- ሰው በቅዱሱ እግዚአብሔር ፊት ኃጢአተኛ መሆኑን በማመን ይህንን የዘለዓለም ሕይወት ነፃ ስጦታ በእምነት መቀበል ይችላል።

## ሰው የሚጸድቀው ጸጋውን በእምነት በመቀበል ብቻ ነው

1. **እሥራኤል (ሐዋርያትን ጨምሮ) የዳኑት በጸጋ ብቻ ነው (ሐዋ15፡11)**
2. **የእግዚአብሔር ጽድቅ የሚገኘው የኢየሱስን ቤዛነት በማመን በጸጋ ብቻ ነው (ሮሜ 3፡21)**
3. **በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ጸድቀናል (ሮሜ 3፡24)**
4. **ሰው ያለሕግ ሥራ በእምነት ይጸድቃል (ሮሜ 3፡27-29)**
5. **የዳንነው በጸጋ እንጂ እግዚአብሔር ግዴታ (ዕዳ) ስላለበት አይደለም (ሮሜ 4፡4)**
6. **እግዚአብሔር ያለሥራ (በጸጋ) ጽድቅን ቆጥሮልናል (ሮሜ 4፡5-8)**
7. **ያለሥራ ጽድቅ የሚቆጠርለት ሰው ብጹዕ ነው(ሮሜ 4፡6-8)**
8. **ሥራ በጸጋ የመጽደቃችን ማኅተም እንጂ የመጽደቂያ መንገድ አይደለም** (**ሮሜ** 4፡9-12)
9. **እምነታችን ጽድቅ ሆኖ የሚቆጠረው ከመሥራታችን አስቀድሞ ነው (ሮሜ 4፡11)**
10. **እምነት ጽድቅ ሆኖ የተቆጠረው ለአብርሃም ብቻ ሳይሆን ለእኛም ነው** (**ሮሜ**.4፡23-25)
11. **በእምነት ስለጸደቅን ሰላም ሊኖረን ይገባል (ሮሜ 5፡12)**
12. **እግዚአብሔር ጸጋውን የላከው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ስለሆነ በአዳም ከመጣብን ኃጢአት ይልቅ ጸጋው እኛን ለማጽደቅ እጅግ ብልጫ አለው።** (**ሮሜ**.5፡12-21)
13. **የምንጸድቀው በአንድ ሰው (በኢየሱስ )መታዘዝ ነው (ሮሜ 5፡18-21)**
14. **አማኝ ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደለምና ኃጢአት አይገዛውም (ሮሜ 6፡14)**
15. **በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት ኩነኔ ፈጽሞ የለባቸውም** (**ሮሜ**.8፡1)
16. **ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት ወጥተናል (ሮሜ 8፡2)**

17. የሚያጸድቀን ራሱ እግዚአብሔር ነው (ሮሜ 8:30፣33)
18. ጽድቅ ከጠሪው እንጅ ከሥራ አይደለም (ሮሜ 9:10-13)
19. ምህረት ለወደደ ወይም ለሮጠ አይደለም (ሮሜ 9:14-18)
20. በእምነት ጽድቅን ማግኘት ሲቻል በሥራ ግን ፈጽሞ አይቻልም (ሮሜ 9:30)
21. የሚያምኑ ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ክርስቶስ የሕግ ፍፃሜ ነው (ሮሜ 10:3-4)
22. ደህንነት የሚገኘው በልብና በአፍ ላይ በተዘጋጀው በእምነት ቃል እንጂ ሕግን በማድረግ አይደለም። (ሮሜ.10:8-10)
23. ከእስራኤልም የሚመረጡት በጸጋ እንጂ በሥራ አይደለም (ሮሜ 11:5-6)
24. እሥራኤል የተቆረጡት ባለማመናቸው ነው (ሮሜ 11:20)
25. ምህረት አለመታዘዝ ያመጣው ነገር ነው (ሮሜ 11:30-36)
26. የተጠራነው በክርስቶስ የጸጋ ወንጌል ነው (ገላ 1:6)
27. ከጸጋ ወንጌል ውጭ የሚሰብክ ማንኛውም ፍጥረት በመለኮታዊ ርግማን ሥር ነው። (ገላ.1:6-9)
28. በጸጋ ከዳንን የሕግ ሰባኪዎች አርነታችንን (ነጻነታችንን) እንዲሰልሉ ልንፈቅድላቸው ፈጽሞ አይገባም (ገላ 2:3-5)
29. የወንጌል እውነት ጸንቶ እንዲኖር ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች እንኳን ወደ ሥራ ሕግ ፈቀቅ ቢሉ ሊወቀሱ ይገባቸዋል። (ገላ.2:11-21)
30. ሰው በኢየሱስ ክርስቶሰ በማመን እንጂ ሕግን በመፈጸም ከቶ ሊጸድቅ አይችልም። (ገላ 2:16)
31. የእግዚአበሔርን ፀጋ መጣል አይገባም (ገላ 2:21)
32. ጽድቅ የሚገኘው ሕግን በመፈጸም ከሆነ ክርስቶስ መሞት አያስፈልገውም ነበር። (ገላ 2:21)
33. መንፈስ ቅዱስን የተቀበልነው፣ ምልክቶችና ተአምራት የሚደረጉት ቃሉን በእምነት በመስማታችን እንጂ ሕጉን በመጠበቃችን አይደለም። (ገላ 3:1-5)
34. በእምነት የጸደቁ በሙሉ የአብርሃም ልጆች ናቸው። (ገላ 3:6-9)
35. ጻድቅ በእምነት ይኖራል እንጂ በሥራው አይመካም። (ገላ 3:11)
36. የተስፋው ቃል ለሚያምኑ ብቻ ይሰጣል። (ገላ 3:21-22)
37. የሕግ ሰባኪዎች እና ትምህርቱን የተቀበሉ ወደ ውጭ ሲጣሉ የተስፋው ቃል ልጆች ግን ይወርሳሉ። (ገላ 4:21-31)
38. ከሕግ ትምህርት ነጻነት ወጥተናል። (ገላ 4:8-11, 5:1)
39. ከሥራ ሳይሆን ከእምነት የጽድቅን ተስፋ እንጠባበቃለን። (ገላ 5:5)

40. ከዚህ እውነት የሚያናውጡን (ሐዋ 15፡24) ፍርዱን ይሸከማሉ ፡፡(ገላ 5፡9-11)

41. የተመረጥነው ስለመልካም ሥራችን ሳይሆን ገና ዓለም ሳይፈጠር በፊት ነበር፡፡ ስለዚህ ጸጋው እንዲያው የተሰጠን ነው እንጂ በጽድቃችን ያገኘነው አይደለም፡፡ (ኤፌ1፡4-6, 2፡1-5)

42. ጸጋው በእምነት ብቻ አድኖናልና በሥራችን አንመካም፡፡ (ኤፌ2፡8-10)

43. እኛ በአደረግነው ሥራ ሳይሆን በጸጋው ጸድቀናል፡፡ (ቲቶ 3፡3-7)

44. ይህ በሁሉ ዘንድ የታወቀ ካልሆነ ጥፋት ይሆናል (ሐዋ13፡38-43)

## 7. በሥራ የሚገለጠው እውነተኛ እምነት

**የጸጋው ብርታት፡** ዳግመኛ የተወለዱ የእግዚአብሔር ልጆች በሙሉ የሚያውቁት አንድ እውነት አለ፡፡ ይኸውም ጸጋው አንድን ኃጢአተኛ የዘላለም ሕይወት እንዲያገኝ ካደረገው በኋላ አስደናቂ የሆነ የሕይወት ለውጥ በዚያ ሰው ላይ የማምጣቱ እውነት ነው፡፡

**የጸጋው ቀጣይና ተከታታይ ሥራዎች፡-**

1. ኃጢአተኛውን ሰው ከፍርድ ያድነዋል
2. ኃጢአተኛነትንና ዓለማዊን ምኞት ያስክደዋል
3. ጌታ እስኪገለጥ ድረስ ራስን መግዛትንና፣ ጽድቅን፣ እግዚአብሔርንም መምሰል ያስተምረዋል፡፡ (ቲቶ.2፡11-14)

- ምንም እንኳ ደህንነታችን የሚፈጸመው በጸጋውና በእምነታችን ብቻ ቢሆንም፡ ትክክለኛውን አማኝ ከአፍአዊ አማኝ የምንለይበት ዋነኛ መንገድ ጸጋው ሰውየውን ካዳነ በኋላ የሚሠራቸውን ሥራዎች በሰውየው ሕይወት ላይ በመፈለግ ነው፡፡
- ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች በጸጋ ብቻ እንደጸደቁ ከአረጋገጠላቸውና ለመዳን ብለው የሕግን ሥራ ለመፈጸም እንዳይሞክሩ በታላቅ ማስጠንቀቂያ ከጻፈላቸው በኋላ “ብቻ አርነታችሁ ለሥጋ ምክንያትን አይስጥ በማለት ጸጋውን ለኃጢአት መፈጸምያ ፈቃድ እንዳያደርጉት ነገሯቸዋል፡፡” (ገላ 5፡13)
- በጸጋ የዳነ ሰው ለመታዘዝ ባርያ ይሆናል እንጂ ኃጢያትን ለመስራት ባርያ አይሆንም (ሮሜ 6፡15-19)
- ጸጋውን ለክፋት መሸፈኛ ማድረግ አይገባም፡፡ (1ጴጥ.2፡16)
- ጸጋው በእምነት ለዳነው ሰው በሕይወቱ ውስጥ ኃጢአተኛነትንና ዓለማዊን ምኞት የሚያስክድ ኃይል ስለሚሰጠው አማኝ እምነቱን በሥራ የመግለጥ ችሎታ አለው፡፡

- **እምነት አለኝ የሚል ነገር ግን ሥራ የሌለው ሰው (አፍአዊ አማኝ) የጸጋውን ወንጌል በእምነት ለመቀበሉ ማረጋገጫ የለውም:: (ያዕ 2:14)**
- **ሕያው ያልሆነ የሞተ እምነት ሥራ ሊከተለው አይችልም (ያዕ 2:17)**
- **በእምነት በእግዚአብሔር ፊት የጸደቀ እምነቱን በሰው ፊት የሚገልጠው በሥራ ነው (ያዕ 2:18)**
- **አጋንንታዊ እምነት በጸጋ ስለማይደገፍ የሚታይ ፍሬ የለውም (ያዕ 2:19)**
- **እምነት በሥራ ይፈጸማል ሁለቱም አብረው ይሄዳሉ (ያዕ 2:21-22)**
- **ሥራው የመጽደቃችን ምክንያት ሳይሆን የመጽደቃችን ማረጋገጫ ነው:: ይህም ማለት ሥራችን በእምነት ለመጽደቃችን ማረጋገጫ ነው:: (ያዕ 2:23)**
- **እምነት ፈጽሞ ያለሥራ ብቻውን ተገልጦ አያውቅም (ያዕ 2:24-26)**

***"ተፈፀመ"***


**<u>ከአዘጋጁ</u>**:- "ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታችንም ከኢየሱስ ክርስቶስ

*ፀጋና ሰላም*

ለእናንተ ይሁን" (ገላ 1:3)

አሜን!

☞ ***ዳዊት ፋሲል***
ስ.ቁ. 0917804407
*ፖ.ሣ.ቁ. 67 ጅማ*
E-mail – niguye2004@yahoo.com



# የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት

# The Person of Christ (Christology)

*ለዚችም ዓለም ገዦች አንዱ እንኳ ይህን ጥበብ አላወቀም፤ አውቀውስ ቢሆኑ የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር።*
*(1ቆሮ 2:8)*

*በዳዊት ፋሲል* *2003 ዓ.ም.*

# የኢየሱስ ክርስቶስ ስሞችና መጠርያ ማዕረጉች

**ኢየሱስ፡-** የግሪክ ቃል ሲሆን "መድኃኒት፣ አዳኝ" ማለት ነው፡፡ በዕብራይስጥ "የሹዋህ" Yeho-shuah ትርጉሙ "ያህዌ" አዳኝ ነው፣ "እግዚአብሔር አዳኝ ነው" ማለት ነው፡፡ (ማቴ 1:21)

**ክርስቶስ፡-** የተቀባ፣ የተሾመ ማለት ነው፣ ይህም የተላከበትን ዓላማና ሥራ ሁሉ ለመፈጸም ሥልጣን እንዳለው የሚገልጥ ማረጋገጫ የሥልጣን ስም ነው፡፡ ክርስቶስ ከስምነት ይልቅ የኢየሱስን ማዕረግ እና ስልጣንን ይገልጣል፡፡ (ማቴ 16:16, ሐዋ 2:36)

**አማኑኤል፡-** "ትሥጉትን" (አምላክ በሥጋ መገለጡን) እና በሕዝቡ መካከል መኖሩን የሚገልጥ ስም ነው፡፡ ትርጉሙም "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር" ማለት ነው (ኢሳ 7:14, ማቴ 1:23)

**የእግዚአብሔር ልጅ፡-** ዘለዓለማዊ የእግዚአብሔር የባህርይ ልጅ፣ ማለትም ፍጹም አምላክ መሆኑን የሚገልጥ መጠሪያ ነው፡፡ (ማቴ 16:16, ዮሐ 20:31)

**የሰው ልጅ፡-** በሥጋ መገለጡንና፣ በሥጋና በደም ከእኛ ጋር የተካፈለበትን ፍጹም ሰውነቱን የሚገልጥበት መጠሪያ ነው፡፡ (ማር 10:45, ማቴ 26:64)

**ጌታ፡-** በግሪኩ ኩሪዮስ የሚለው ቃል የተተረጎመው "ላለና ለነበረው" ለአምላክ ስም ያህዌህ ለሚለው ሲሆን በግሪኩ መጽሐፍ ቅዱስ ፈጣሪና፣ ፍጥረቱን መጋቢ ለሆነ አምላክ የሚቀጸል መጠሪያ ነው፡፡ (ዮሐ 13:13, ሐዋ 2:36)

**መምህር፡-** ከእግዚአብሔር ዘንድ ለሕዝቡ ለእሥራኤል ለአህዛብ ሁሉን ይገልጥ ዘንድ የተላከ ታላቅ አስተማሪ መሆኑን የሚያሳይ (ዮሐ 3:2, ሉቃ 2:29-32, ዮሐ 13:13)

**ንጉሥ፡-** በዳዊት ዙፋን ላይ የሚቀመጥበት፣ በያዕቆብ ቤት ሁሉ ላይ፣ በኢየሩሳሌም በታላቁ ንጉሥ ከተማ የሚነግሥበት ሥልጣኑን የሚያሳይ መጠርያ ነው (የሺው ዓመት መንግሥትን አጥና) ማቴ 2:1-11, 27:37

**የዳዊት ልጅ፡-** እግዚአብሔር ለዳዊት በዙፋኑ ላይ ለዘላለም የሚቀመጥ ልጅ እንደሚያስነሳለት ተስፋ ሰጥቶታል እናም አይሁድ ሁሉ ተስፋ የሚያደርጉት ንጉሣቸው መሆኑን የሚገልጥ መጠርያ ነው፡፡ (መዝ 89:28-37 ማቴ 1:1, ማር 10:48)

## ሌሎች መጠርያዎች

| | |
|---|---|
| የንጋት ኮከብ | ዘኁ 24:17, ራዕ 22:16 |
| ታላቅ ነቢይ | ዘዳ 18:18, ማቴ 21:11 |
| የማዕዘን ራስ ድንጋይ | ኤፌ 2:20, 1ጴጥ 2:6 |
| አለት | ማቴ 16:16-18, 1ቆሮ 10:4 |
| ቃል | ዮሐ 1:1, 14, 1ዮሐ 1:1, ራዕ 19:13 |

# የክርስቶስ ማንነት (The Person of Christ)

**"ኢየሱስ ክርስቶስ ፍፁም አምላክ፣ ፍፁም ሰው በአንድ አካል ነበረ፣ አሁንም እንዲሁ ነው፣ ወደፊትም ለዘለዓለም እንዲሁ ሆኖ የሚኖር ነው።"**

# ክፍል ፩

## <u>የኢየሱስ ክርስቶስ ሰብዓዊነት (ሰው መሆን)</u>

## <u>ማረጋገጫ</u>

**1.1** **<u>በድንግልና መወለድ</u>፡-** ድንግል ከነበረችው ከማርያም፣ በተዓምራዊ ሁኔታ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ያለሰብዓዊ አባት ተጸነሰ፣ (ማቴ 1:18,20)

- ✓ በድንግልና መጸነሱ ብቻ ሳይሆን በድንግልና መወለዱም ለትንቢቶች መፈጸም አስፈላጊ ነበር። (ኢሳ 7:14, ማቴ 1:24-25)
- ✓ በመሆኑም ሕፃኑ ኢየሱስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነበረ (ሉቃ 1:34-34)

**<u>በድንግልና ያለወንድ ዘር የመወለዱ አስፈላጊነት</u>**

ሀ. ደህንነት ፈጽሞ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ብቻ ነው።

- ✓ ሰው በራሱ ጥረት እና ፍላጐት ፈጽሞ መዳን አይችልም ስለሆነም የእግዚአብሔርን በጸጋ ማዳን መጠበቅ ብቻ ነበረበት (ገላ 4:4-5)

ለ. ፍጹም አምላክነትና ፍጹም ሰውነት መዋሀድ የሚችሉበት ብቸኛ መንገድ ነው።

- ✓ ኢየሱስ ያለምድራዊ ወላጅ ከሰማይ ሥጋ እንደለበሰ ሙሉ ሰው ሆኖ ቢገለጥ እንደኛ ያለ ፍጹም ሰው መሆኑን ማረጋገጥ አይቻልም።
- ✓ ኢየሱስ ከእናትና አሥጋ አባት እንደኛ የተወለደ ቢሆን ኖሮ ፍጹም አምላክ መሆኑን ፈጽሞ ማረጋገጥ አይቻልም።

ሐ. ፍጹም ሰውነቱና ከኃጢአት ዘር ነፃ መሆኑ የተረጋገጠበት ነው።

- ✓ ኢየሱስ እንደሌሎች የሰው ዘሮች ከአዳም የተቀጠለ የዘር ተዋረድ የለበትም። ዘር የሚቆጠረው በወንድ እንጂ በሴት በኩል እንዳይደለ ልብ ይሏል።
- ✓ ድንግሊቱ ማርያም ኃጢአት ቢኖርባትም እንኳ ወደ ኢየሱስ ፈጽሞ መተላለፍ እንዳይችል መንፈስ ቅዱስ የመጸለል (የመጋረድ) ሥራ ሠርቷል (ሉቃ 1:35)

## 1.2 የኢየሱስ ክርስቶስ ሰብዓዊ (የሰውነት) ባህርያት

ሀ. ኢየሱስ የሰው አካል ለብሷል

- ✓ እንደ ሕፃን ተወልዷል (ሉቃ 2፡7) እንደልጆች በጥበብ፣ በዕውቀት፣ በቁመት ያድግ ነበር (ሉቃ 2፡40,52)
- ✓ ይደክመው ነበር (ዮሐ 4፡6) ይርበው ነበር (ማቴ 4፡2) ይጠማው ነበር (ዮሐ 19፡28) መላዕክት ያገለግሉት ነበር (ማቴ 4፡11) ነፍሱን በእግዚአብሔር እጅ ላይ አደራ ሰጠ (ሉቃ 23፡46)
- ✓ ከሞትም ሲነሳ ሰብዓዊ አካሉ በሙሉ በትንሣኤ አካል ተነስቷል፡፡ ስለሆነም ሥጋና አጥንት ያለው አካል እንጂ መንፈስ አልነበረም (ሉቃ 24፡39) በፊታቸውም ምግብ በልቷል (ሉቃ 24፡42, ዮሐ 20፡17, 20, 27, ዮሐ 21፡9, 13)
- ✓ ያው የተነሣ አካል ራሱ ሁሉም እያዩት ወደ ሰማይ ወጥቷል (ሐዋ 1፡9) በመሆኑም ኢየሱስ የሚመጣው በአካል እንጂ በመንፈስ አይደለም፡፡

ለ. ኢየሱስ ሰብዓዊ አእምሮ አለው

- ✓ በጥበብ ያድግ ነበር (ሉቃ 2፡52)
- ✓ እንደሌሎች ልጆች ሁሉ መብላት፣ መጠጣት፣ መራመድ፣ ማንበብ ወዘተ እየተማረ አደገ፣ የሚያዘው እርሱ መታዘዝን ተማረ (ዕብ 5፡8)

ሐ. ኢየሱስ ሰብዓዊ የነፍስ ስሜት ነበረው

- ✓ ነፍስ 3 ክፍሎች አሏት
  1. ስሜት
  2. ፈቃድ
  3. ዕውቀት
- ✓ ነፍሱ ትታወክ ነበር (ዮሐ 12፡27) , በመንፈሱ ይታወክ ነበር (ዮሐ 13፡21)
  ነፍሱ ታዝን ነበር (ማቴ 26፡38) , ይደነቅ ነበር (ማቴ 8፡10)
  ያዝንና ያለቅስ ነበር (ዮሐ 11፡35), በመራራ ጩኸትና እንባ ይጸልይ ነበር (ዕብ 5፡7)

## 1.3 ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአት ፈጽሞ የሌለበት ብቸኛው ሰው

- ✓ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ሲሆን ከተበላሸው የሰው ዘር ሁኔታ የሚለየው ፈጽሞ ኃጢአትን ባለማድረጉ ነው።
    - o እግዚአብሔር ሰውን መጀመሪያ በፈጠረው ጊዜ ሰው ኃጢአተኛ አልነበረም ነገር ግን ሰውየው ፍጹም ሰው ነበረ። ስለሆነም ኢየሱስ እንደመጀመርያው ሰው ከኃጢአት ነጻ የሆነ ፍጹም ሰው ነው ማለት ነው።
- ✓ የዓለም ብርሃን ነኝ (ዮሐ 8:12) ብርሃን የእውነተኛነትና የንጽህና መገለጫ ነው።
- ✓ ደስ የሚያሰኘውን ሁልጊዜ አደርጋለሁ (ዮሐ 8:29) የአባቱን ትዕዛዝ ሁሉ ይፈጽም ነበር (ዮሐ 15:10), ጲላጦስ ምንም በደል አላገኘበትም (ዮሐ 18:38)
- ✓ በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ እንጂ ኃጢአተኛ ሆኖ አልተገለጠም (ሮሜ 8:3)
- ✓ ኃጢአት አያውቀውም ነበር (2ቆሮ 5:21) ቢፈተንም ኃጢአትን ከቶ አላደረገም (ዕብ 4:15) እርሱ በክፉ አይፈተንምና (ያዕ 1:13)
- ✓ ቅዱስ እና ነውር የሌለበት፣ ከኃጢአተኞች የተለየ ፍጹም ሰው ነበር (ዕብ 7:26, 1ጴጥ 1:19, 1ጴጥ 2:22, 3:18, 1ዮሐ 2:1, 3:5)
- ✓ የመፈተኑ አስፈላጊነት እኛን ይረዳን ዘንድ ነው (ዕብ 2:18)

## 1.4 የኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰውነት ለምን አስፈለገ?

- ✓ ሐዋርያው ዮሐንስ መልዕክቶቹን የጻፈው ኢየሱስ ፍጹም ሰው አይደለም የሚል የክህደት ትምህርት በተነሳ ጊዜ ነበር። (1ዮሐ 4:2-3)
    - o ዶሴቲዝም (Docetism):- ዶኪዮ በግሪክ መቅረብ፣ መምሰል ማለት ሲሆን ኢየሱስ ሰውን መሰለ እንጂ ሰው አይደለም የሚል የፍልስፍና ትምህርት ነው።

# የኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው የመሆን አስፈላጊነት

## ሀ. በምትክነት ለመታዘዝ (For representative obedience)

- አዳም የሰው ዘሮችን ሁሉ በመወከል ባለመታዘዝ ኃጢአትን አደረገ በመሆኑም ሁሉም ሰው በአዳም መተላለፍ ምክንያት ኃጢአትን አድራጊና ተላላፊ ሆነ:: (ዘፍ 2:15-3:7) የአዳም መተላለፍና መውደቅ

ሦስቱ የኃጢአት መግቢያ መንገዶች (1ዮሐ 2:15-16)

<u>ሴቲቱና ባልዋ</u>

| | |
|---|---|
| የዓይን አምሮት | ለዓይን እንደሚያስጐመጅ |
| የሥጋ ምኞት | ለመብላት ያማረ |
| የሕይወት ትምክህት | ለጥበብም መልካም እንደሆነ አየች |

ክርስቶስ

- ክርስቶስ የሰው ዘሮችን ሁሉ በመወከል ታዘዘ በመሆኑም በእርሱ መታዘዝ ምክንያት የሚያምኑበት ሁሉ ጽድቅ ይቆጠርላቸዋል:: (ሉቃ 4:1-13, ሮሜ 5:18-19)

| | |
|---|---|
| የዓይን አምሮት | የዓለምን ነገሥታት ክብራቸውን አሳየው |
| የሥጋ ምኞች | በራበው ጊዜ ድንጋዩን እንጀራ አድርገው አለው |
| የሕይወት ትምክህት | የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ ከዚህ ወደታች ራስህን ጣል አለው:: |

- ክርስቶስ የኋለኛው አዳም ነው (1ቆሮ 15:45)
- አዳም ፊተኛው ሰው ነበረ ክርስቶስ ሁለተኛው ሰው ነው::

| የፊተኛው አዳም (አዳም) (ሮሜ 5:18-19) | የኋለኛው አዳም (ክርስቶስ) |
|---|---|
| - አልታዘዘም | - ፈጽሞ ታዘዘ |
| - የበደሉ መጠን ከኋለኛው አዳም የጽድቅ መጠን እጅግ በጣም ያነሰ ነው:: | - የጽድቁ ብዛት ከፊተኛው አዳም ይልቅ እጅግ በጣም የበዛ ነው:: |
| - በዚህ ምክንያት ሰዎች ሁሉ ይሞቱ ነበር:: | - በዚህ ምክንያት ሰዎች በሕይወት ለዘለዓለም ይነግሳሉ:: |

## ለ. በምትክነት ለመሞት እና መስዋዕት ለመሆን

- አምላክ አይሞትም በመሆኑም የሚሞት ሥጋ መልበስ አስፈለገው (ዮሐ 1:14)
- በሞቱ አማካይነት ሥልጣናትን ሊሽር በሥጋና በደም መካፈል ነበረበት (ዕብ 2:16-17)
- በመሆኑም የብሉይ ኪዳን መስዋዕቶችን ሁሉ በመተካት ፍጹም የሆነ የኃጢአት ሥርየትን ለመስጠት መሰዋት ነበረበት::
  (ዮሐ 1:29, ዕብ 9:22-28, ዕብ 10:1-18)
- በመሆኑም ኢየሱስ የሞተው በራሱ ምክንያት ሳይሆን በሰዎች ምክንያት በመሆኑ የእርሱ ሞቱ የምትክነት ሞት (Substitutionary death) ይባላል::

## ሐ. በእግዚአብሔርና በሰው መካከል መካከለኛ (ሊቀ ካህናት) ለመሆን ነው::

- እርሱ ፍጹም አምላክ በመሆኑ በእግዚአብሔር ፊት ሊቆም የሚችል፣ ፍጹም ሰው በመሆኑ የአማኞችን ድካም የሚረዳ ሆኗል (1ጢሞ 2:5)
- በሰውነቱ ምክንያት የተፈተነ ነውና ሊራራልን ይችላል (ዕብ 2:18, 4:15-16)

# ክፍል ፪

# የኢየሱስ ክርስቶስ ፍፁም አምላክነት (መለኮትነት)

አምላክነቱ ከሥጋው የተዋሀደበት ትምህርት "ምሥጢረ ሥጋዌ" ወይም "ትሥጉት" Incarnation ይባላል:: ምሥጥረ ሥጋዌ አምላክ ከሥጋ ጋር የተዋሀደበት መለኮታዊ አሠራሩ ነው:: በመሆኑም ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ ሰው ብቻ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ደግሞ ፍፁም አምላክ ነው::

## <u>ማረጋገጫ</u>

## 2.1. የተጠቀሱ መጠሪያ ስያሜዎች

### ሀ. እግዚአብሔር (Theos) (ዮሐ 1:1-3)

- ይህ ቃል ፍፁም መለኮት ለሆነው ለእግዚአብሔር የምንጠቀምበት ቃል ሲሆን በሚከተሉት ጥቅሶች ውስጥ ሁሉ "ቴዎስ" የተጠቀሰው ለኢየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊ ማንነት ነው::

  **(ዮሐ 1:1, 20:28, ሮሜ 9:5, ቲቶ 2:13, ዕብ 1:8 2ጴጥ 1:1)**
- የብሉይ ኪዳን ትንቢቶችም እርሱ አምላክ መሆኑን በግልፅ አሳይተዋል

  **(ኢሳ 9:6, መዝ (110):1, (45):6, (102):2)**

### ለ. ጌታ (Kyrios)

- በክርስቶስ ዘመን ይህ ቃል በግሪክ ሰባው ሊቃውንት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሙበት በዕብራይስጡ ያህዌህ ወይም ጄሆቫህ ለሚለው የአምላክ ስም ነው::
- ኪሪዮስ በግሪኩ ብለይ ኪዳን ውስጥ ጌታ እግዚአብሔር ለሚለው ስያሜ 6,814 ጊዜ ተጠቅሷል:: ይኸው ኪሪዮስ ጌታ ኢየሱስ የሚጠራበት "ጌታ" የሚለው ቃል ነው:: ስለሆነም ማንኛውም ግሪካዊ አንባቢ "ጌታ" ኢየሱስ የሚለውን ቃል የሚረዳው የሁሉ ነገር ፈጣሪና፣ የፍጥረቱ ሁሉ መጋቢ እና አስተዳዳሪ አድርጐ ነው::

  **(ሉቃ 2:11, ማቴ 3:3 - ኢሳ 40:3, ማቴ 22:44, 1ቆሮ8:6, 12:3)**

### ሐ. ኢየሱስ የተጠቀማቸው ቃላቶች እና ስያሜዎች

- አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ "I am" (ዮሐ 8:58)

  የአይሁድ መምህራን እኔ የሚለውን ስያሜ የሚያያይዙት በዘፀአት 3:14 ላይ ከተጠቀሰው ስም ጋር ነው "I am who I am" ስለሆነም ሊወግሩት ድንጋይ አነሱ ቁ 59

✓ *አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ* (*ራዕ* **22:13)**

*መጀመርያና መጨረሻ የሚለው ስያሜ መለኮታዊ ማንነትን የሚገልጥ ሲሆን በብሉይ ኪዳን የተጠቀሰው ለእግዚአብሔር ነው::* (*ኢሳ* **44:6)**

✓ *የእግዚአብሔር ልጅ*

*የእግዚአብሔር የባህርይ ልጅ እና እግዚአብሔር የሆነ ማለት ነው::*

*ማቴ* **11:25-30, 17:5, 1***ቆሮ* **15:28,** *ዕብ* **1:1-3, 5, 8**

- *አባት የሚሠራውን ሁሉ ልጁም ይሠራዋል ዮሐ* **5:20-22, 25, 10:17, 16:15**

**መ. ኢየሱስ/ አማኑኤል**

በዕብራይስጥ "Yehoshuah":: *ያህ የእግዚአብሔር ስም ሲሆን "ዬሆሹዋ" ማለት እግዚአብሔር መድኃኒት ነው ማለት ነው እንዲሁም አማኑ-ኤል፣ ኤል - አምላክ ማለት ስለሆነ "አምላክ ከእኛ ጋር" እንደማለት ነውና እርሱ "እግዚአብሔር አምላክ" ነው::*

## 2.2 የኢየሱስ መለኮታዊ ባህርያት (Divine Essences)

*መለኮታዊ ባህርያት ማለት መለኮት ብቻ ሊኖረው የሚችለው የትኛውም ፍጥረት የማይኖረው የአምላክ መታወቂያና መገለጫ ባህርያቶቹ ናቸው::*

**ሀ. ሁሉን ማድረግ ይችላል (Omnipotent)**

*ማዕበል በቃሉ አዟል ማቴ* **8:26-27**

*ዳቦና አሣ አበርክቷል* (*ማቴ* **14:19)**

*ውኃ ወደወይን ጠጅ ቀይሯል ዮሐ* **2:1-11**

**ለ. ዘለዓለማዊ ነው ዮሐ 8:58, ራዕ 22:13**

**ሐ. ሁሉን ያውቃል (Omniscience)**

*የሰዎችን ሀሳብ* **(***ማር* **2:8)** *አሳልፎ የሚሰጠውን* **(***ዮሐ* **6:64) (***ዮሐ* **2:25, 16:30)**

**መ. በሁሉ ቦታ ይገኛል (Omnipresence) (ማቴ 18:20, 28:20)**

**ሠ. ሉዓላዊ ሥልጣን አለው (Sovereignity)**

*ኃጢአትን ይቅር ማለት* **(***ማር* **2:5-7)** *እግዚአብሔር እንዲህ ይላችኋል ሳይሆን እኔ ግን እላችኋለሁ ይላል* **(***ማቴ* **5:22, 28, 32, 34, 39, 44)**

**ረ. አምልኮን ይቀበል ነበር**

*ከመላዕክት*(*ዕብ* **1:6** *ራዕ* **5:6-19)** *ከሰዎች* **(***ዮሐ* **9:38)** *ጉልበት ሁሉ* **(***ፊል* **2:9-11)** *በአጠቃላይ ኢየሱስ ክርስቶስ የመለኮት ሙላት ሁሉ የተገለጠበት ነው::* **(***ቈላ* **1:19, 2:9)**

## 2.3 ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ የመሆኑ አስፈላጊነት

ሀ. የሚያምኑበትን ሁሉ ፍርዳቸውን ሊሸከም እና ሊያስወግድ የሚችል ፍጹም አምላክ የሆነ ማንነት ብቻ ነው።

ለ. ደህንነት ከእግዚአብሔር ብቻ ነው (ዮናስ 2፡10)

ሐ. ፍጹም አምላክ እና ፍጹም ሰው የሆነ ማንነት ብቻ ነው በሰውም በእግዚአብሔር መካከል መካከለኛ መሆን የሚችለው (1ጢሞ 2፡5)

በመሆኑም ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ባይሆን ኖሮ ደህንነትም፣ ክርስትናም ፈጽሞ አይኖሩም ነበር።

"ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ የለውም" 1ዮሐ 2፡23

"በክርስቶስ ትምህርት ለማይኖር አምላክ የለውም" 2ዮሐ ቁ9

## ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ነው

**ሀ. እግዚአብሔር ፈጣሪ ነው።**

ዘፍ 1:1, ዘፍ 2:7, ኢዮ 33:4, መዝ 33:6, መዝ 104:30, ኢሳ 40:28, ኢሳ 44:24, ኢሳ 45:11-18, ሚል 2:10

**ኢየሱስ ክርስቶስ ፈጣሪ ነው።**

ዮሐ 1:3, 10, 1ቆሮ 8:6, ኤፌ 3:9, ቈላ 1:12-17, ዕብ 1:8-12, ራዕ 4:8-11, ራዕ 10:6, ራዕ 14:6-7, ራዕ 21:5-7, ራዕ 22:3, ራዕ 7:17

**ለ. እግዚአብሔር አዳኝ ነው**

መዝ 78:34-35, ኢሳ 47:4, ኢሳ 44:6,24 43:3-11, 45:21, ኢሳ 49:26, መዝ 106:21, ሉቃ 1:46-47, 1ጢሞ 1:1, ቲቶ 1:1-4, 1ጢሞ 4:10, ቲቶ 2:10-13

**ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝ ነው**

1ዮሐ 4:14, 1ጴጥ 2:21-24, ሐዋ 20:28, ገላ 3:13, ሉቃ 24:21-29, ሉቃ 2:10-11, ዮሐ 4:40-42, ሐዋ 13:23, ፊል 3:20, 1ጢሞ 1:1,2, ቲቶ 1:4, 1ጴጥ 1:10, ይሁዳ 25

**ሐ. እግዚአብሔር ዳግም ይመጣል**

ዘካ 14:3-5, 1ተሰ 4:13-18, መዝ 50:1-6

**ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ይመጣል**

1ተሰ 3:11-13, ማቴ 25:31-46, ቲቶ 2:11-13, ራዕ 19:11, 16

**መ. እግዚአብሔር ዓለት ነው**

ዘዳ 32:3-4, 1ሳሙ 2:2, 2ሳሙ 22:2, መዝ 18:2, መዝ 31:1-4, መዝ 78:35, መዝ 89:26, ኢሳ 17:10

**ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለት ነው**

ማቴ 16:17-19, ሐዋ 4:11-12, ዘኍ 20:1-11, 1ቆሮ 10:4, ኢሳ 28:16, ኤፌ 2:20-22, 1ጴጥ 2:6-8

**ሠ. እግዚአብሔር መጀመርያና መጨረሻ ነው**

ኢሳ 41:4, ኢሳ 43:10-11, ኢሳ 44:6-8 ራዕ 1:8

**ኢየሱስ ክርስቶስ መጀመርያና መጨረሻ ነው**

ራዕ 1:17, ራዕ 22:13

**ረ. እግዚአብሔር "እኔ ነኝ" ይላል**

ዘፀ 3:13-14, ኢሳ 43:10, ኢሳ 43:25

**ኢየሱስ "እኔ ነኝ" ይላል**

ዮሐ 18:5-8, ራዕ 1:17-18, ራዕ 8:24-28

**ሰ. እግዚአብሔር ንጉሥ ነው**

መዝ 47:2, 6, መዝ 44:4, መዝ 74:12, ዘካ 14:9, ኢሳ 44:6, ኤር 10:10

**ኢየሱስ ንጉስ ነው**

ማቴ 2:1-6, ሉቃ 19:35-38, ሉቃ 23:3, ዮሐ 18:37, ዮሐ 19:21, 1ጢሞ 6:13-16, ራዕ 15:1-4, ራዕ 19:11-16

**ሸ. እግዚአብሔር እረኛ ነው**

መዝ 23:1, ኢሳ 40:10-11, ኢሳ 10:3

**ኢየሱስ እረኛ ነው**

ዮሐ 10:8-12, 1ጴጥ 2:21-25, ዕብ 13:20, 1ጴጥ 5:4

## ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሳሳቱ አመለካከቶች

### *ሀ. አፖሊናሪያኒዝም፡- ኢፖሊናሪስ በ361 የሎዶቂያ ጳጳስ ነበር*

ኢየሱስ አካሉ የሰው ቢሆንም ነገር ግን የሰው ሕሊና፣ እና የሰው ባህርያት አልነበሩትም የሚል ነበር፣ መለኮታዊ ባህርያት ብቻ በሰውነቱ ወስጥ ነበረው ይል ነበር፡፡




* ትምህርቱ በ362 ዓ.ም. በአሌክሳንደርያ ጉባኤ፣ በ381 ዓ.ም. በኮንስታንቲኖፕል ጉባኤ ተወግዟል፡፡

### *ለ. ኔስቶሪያኒዝም፡- ሁለት የተለያዩ ማንነቶች በክርስቶስ ውስጥ ነበሩ የሚል ነው፡፡*

ይህም ማለት ሰብዓዊ ማንነት እና መለኮታዊ ማንነት ተነጣጥለው በአንዱ ክርስቶስ ውስጥ ነበሩ ብሏል፡፡ ኔስቶሪየስ በ428 ዓ.ም. በአንጾኪያ ታዋቂ ሰባኪና የኮንሲታንቲኖፕል ጳጳስም ሆኖ ነበር፡፡




### *ሐ. ሞኖፊሲቲዝም/ኢዩቴይኪዝም፡-*

አውጣኬ ከ378-454 ገደማ በኮንስታንቲኖፕል የነበረ የገዳም አለቃ ነው፡፡ ክርስቶስ አንድ ባህሪይ ብቻ ነበረው እንጂ ፈጽሞ ሁለቱም ባህሪያት አልነበሩትም አለ ሰብዓዊ ባህርያቱ በሙሉ ከመለኮታዊ ባህርያቱ ጋር እርስ በርስ ተዋዋጡ ብሎም አስተማረ፡፡ በመሆኑም አዲስ የሆነ ባህርይ ነበረው ይል ነበር፡፡



## አራቱ ወንጌሎች የኢየሱስን ማንነት በዋነኛነት የገለጹበት መንገድ

ማቴዎስ፡- ኢየሱስ የአይሁድ ንጉሥ እና መሲህ
ንጉሥ ስምንት ጊዜ፣ የዳዊት ልጅ ዘጠኝ ጊዜ ተጽፏል
(ማቴ 2፡2, 21፡5, 25፡34, 40, 27፡11, 29,37,42)
(ማቴ 1፡1, 9፡27, 12፡23, 15፡22, 20፡30-31, 21፡9, 15, 22፡42)

ማርቆስ፡- ኢየሱስ ተአምራትና ድንቅ አድራጊ፣ የሰዎችና የእግዚአብሔር አገልጋይ
(ማር 6፡2, 10፡45)

ሉቃስ፡- የሰው ልጅ፡- የሰው ልጆች ወዳጅ፣ የጠፉትን የሚፈልግ
(ሉቃ 19፡10, 10፡30-37, 15፡4-7, 15፡11-32, 18፡10-14, 19፡2-10, 23፡39-43)

ዮሐንስ፡- በየምዕራፉ ላይ በተለያየ ማንነት ገልጾታል
ምዕራፍ 1 የእግዚአብሔር ልጅ # 1-14
ምዕራፍ 2 የሰው ልጅ # 1-10
ምዕራፍ 3 መለኮታዊ መምህር # 2-21
ምዕራፍ 4 ነፍሳትን የሚጠራ # 7-29
ምዕራፍ 5 ታላቁ ሀኪም # 1-9
ምዕራፍ 6 የሕይወት እንጀራ # 32-58
ምዕራፍ 7 የሕይወት ውኃ ምንጭ # 37
ምዕራፍ 8 የኃጢአተኞች እና የደካሞች ደገፋ # 3-11
ምዕራፍ 9 የዓለም ብርሃን # 1-39
ምዕራፍ 10 መልካም እረኛ # 1-16
ምዕራፍ 11 የሕይወት ራስ # 1-44
ምዕራፍ 12 ንጉሥ # 12-15
ምዕራፍ 13 አገልጋይ # 1-10
ምዕራፍ 14 አጽናኝ # 1-3
ምዕራፍ 15 የወይን ግንድ # 1-16
ምዕራፍ 16 መንፈጽ ቅዱስን የሚሰጥ # 1-15
ምዕራፍ 17 ታላቁ ጸሎተኛ እና አማላጅ # 1-26
ምዕራፍ 18 የመከራ ተካፋይ # 1-11
ምዕራፍ 19 የተሰቀለው አዳኝ # 16-19
ምዕራፍ 20 ሞትን ያሸነፈ # 1-31
ምዕራፍ 21 ንስሐ የሚገቡትን የሚጠግን # 1-17

## የኢየሱስ ክርስቶስ በ66ቱ መጽሐፍት በዋነኛነት የተገለጠበት ማንነት

| የመጽሐፍት ስም | የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት |
|---|---|
| 1. ኦሪት ዘፍጥረት | - ፈጣሪ አምላካችን |
| 2. ኦሪት ዘፀአት | - የፋሲካችን በግ |
| 3. ኦሪት ዘሌዋውያን | - የኃጢአታችን መስዋዕት |
| 4. ኦሪት ዘኍልቁ | - በዓላማ ላይ የተሰቀለ |
| 5. ኦሪት ዘዳግም | - እውነተኛው ነቢያችን |
| 6. መጽሐፈ ኢያሱ | - የደህንነታችን ራስ እና መሪ |
| 7. መጽሐፈ መሳፍንት | - ነፃ አውጪ መስፍናችን |
| 8. መጽሐፈ ሩት | - የሚቤዥን የቅርብ ወዳጅ |
| 9,10. መጽሐፈ ሳሙኤል 1ኛ ና 2ኛ | - ንጉሣችን |
| 11,12,13,14, ነገሥትና ዜና መዋዕል | - ንጉሣችን እና ነቢያችን |
| 15. መጽሐፈ ዕዝራ | - የፈረሰውን አዳሽ |
| 16. መጽሐፈ ነህምያ | - የፈረሰውን ጠጋኝ |
| 17. መጽሐፈ አስቴር | - ስለእኛ የሚማፀን |
| 18. መጽሐፈ ኢዮብ | - የሚቤዥን |
| 19. የመዝሙር መጽሐፍ | - ሁሉ በሁሉ የሆነ |
| 20. መጽሐፈ ምሳሌ | - ጥበባችን |
| 21. መጽሐፈ መክብብ | - የነገሮች ሁሉ ፍፃሜና መደምደሚያ |
| 22. መኃልይ መኃልይ | - የነፍሳችን ወዳጅ |
| 23. ትንቢተ ኢሳያስ | - የሚመጣው መሲህ |
| 24, 25. ትንቢተ ኤርሚያስና ሰቆቃው | - ፃድቅ ቁጥቋጥ |
| 26. ትንቢተ ሕዝቅኤል | - የሰው ልጅ |
| 27. ትንቢተ ዳንኤል | - የሚያደቅቅና የሚፈጭ ድንጋይ |
| 28. ትንቢተ ሆሴዕ | - ያፈገፈጉትን የሚመልስ |
| 29. ትንቢተ ኢዮኤል | - የሚያድስ የሚመልስ |
| 30. ትንቢተ አሞጽ | - ሰማያዊ ባል |
| 31. ትንቢተ አብድዩ | - መድኃኒታችን |
| 32. ትንቢተ ዮናስ | - ትንሣኤና ሕይወታችን |
| 33. ትንቢተ ሚክያስ | - እውነተኛና ታማኝ ምስክር |
| 34. ትንቢተ ናሆም | - በመከራ ጊዜ መሸሸጊያ |
| 35. ትንቢተ ዕንባቆም | - የደህንነታችን አምላክ |
| 36. ትንቢተ ሶፎንያስ | - ቀናተኛ አምላክ |
| 37. ትንቢተ ሐጌ | - በአህዛብ ሁሉ የተመረጠ |
| 38. ትንቢተ ዘካርያስ | - ፃድቅ ቁጥቋጥ |
| 39. ትንቢተ ሚልኪያስ | - የፅድቅ ፀሐይ |

40. የማቴዎስ ወንጌል - መሲህና ንጉሥ
41. የማርቆስ ወንጌል - የእግዚአብሔርና የሕዝቡ አገልጋይ
42. የሉቃስ ወንጌል - የሰው ልጅና፣ የጠፉትን የሚፈልግ
43. የዮሐንስ ወንጌል - የእግዚአብሔር ልጅ
44. የሐዋርያት ሥራ - ሕያው ጌታ
45. የሮሜ መልዕክት - ጽድቃችን
46. የቆሮንቶስ መልዕክት - ጌታችን
47. 2ኛ የቆሮንቶስ መልዕክት - ብቃታችን
48. የገላትያ መልዕክት - ነፃነታችን
49. የኤፌሶን መልዕክት - የእኛ ሁሉ ነገራችን
50. ፊልጵስዩስ መልዕክት - ደስታችን
51. የቈላስይስ መልዕክት - ሕይወታችን
52. 1ተሰሎንቄ መልዕክት - ዳግም የሚመጣው ተስፋ
53. 2ተሰሎንቄ መልዕክት - ተመልሶ የሚመጣልን ጌታ
54. 1 ጢሞቴዎስ መልዕክት - መምህራችን
55. 2 ጢሞቴዎስ መልዕክት - የምንመለከተው ምሳሌያችን
56. የቲቶ መልዕክት - የምንለማመደው ምሳሌያችን
57. የፊልሞና መልዕክት - ጌታችንና መምህራችን
58. የዕብራውያን መልዕክት - በዙፋኑ ፊት የቆመ ሊቀካህናችን
59. የያዕቆብ መልዕክት - የአኗኗር ተምሳሌት
60. 1ጴጥሮስ መልዕክት - የከበረ የማዕዘን ራስ ድንጋይ
61. 2ጴጥሮስ መልዕክት - ብርታትና ኃይላችን
62. 1ዮሐንስ መልዕክት - ሕይወታችን
63. 2ዮሐንስ መልዕክት - እውነት
64. 3ዮሐንስ መልዕክት - መንገድ
65. የይሁዳ መልዕክት - የእምነታችን ጠባቂ
66. የዮሐንስ ራዕይ - ድል አድራጊው ንጉሣችን

# ስለኢየሱስ ክርስቶስ የተነገሩ ትንቢቶችና በእርሱ ስለ መፈጸማቸው

| ትንቢቶች | | መፈጸማቸው |
|---|---|---|
| ዘፍ 3:15 | የሴቲቱ ዘር | ገላ 4:4, ሉቃ 2:7 |
| ዘፍ 18:18, 12:3 | የአብርሃም የተስፋ ቃል ዘር | ሐዋ 3:25, ማቴ 1:1, ገላ 3:15-18 |
| ዘፍ 17:19 | የይስሐቅ የተስፋ ቃል ዘር | ማቴ 1:2, ሉቃ 3:34 |
| ዘኁ 24:17,ዘፍ 28:14 | የያዕቆብ የተስፋ ቃል ዘር | ሉቃ 3:34, ማቴ 1:2 |
| ዘፍ 49:10 | ከይሁዳ ነገድ የሆነ | ሉቃ 3:33, ማቴ 1:2-3, ራዕ 5:5 |
| መዝ(89):28-37, ኢሳ 9:7, 11:1-5 | በዳዊት ዙፋን የሚቀመጥ ዘር | ማቴ 1:1, ሉቃ 1:32 |
| ሚክ 5:2 | የትውልድ ሥፍራ | ማቴ 2:1, ሉቃ 2:4-7 |
| ዳን 9:25 | የልደት ጊዜው | ሉቃ 2:1-7 |
| ኢሳ 7:14 | በድንግልና መወለዱ | ማቴ 1:18, ሉቃ 1:26-35 |
| ኤር 31:15 | የሕፃናት መገደል | ማቴ 2:16-18 |
| ሆሴ 11:1 | ወደግብጽ መሸሽ | ማቴ 2:14, 15 |
| ኢሳ 9:1-2 | የገሊላ አገልግሎቱ | ማቴ 4:12-16 |
| ዘዳ 18:15 | ታላቅ ነቢይነቱ | ዮሐ 6:14, ሐዋ 3:19-26 |
| መዝ 110:4 | መልከጼዴቂያዊ ክህነቱ | ዕብ 6:20, 5:5-6, 7:15-17 |
| ኢሳ 53:3 | በአይሁድ ተቀባይነት ማጣቱ | ዮሐ 1:11, 5:43, ሉቃ 4:29, 17:25 |
| ኢሳ 11:2-4 | ባህሪያቱ | ሉቃ 2:52, 4:18 |
| ዘካ9:9 | እንደንጉሥ ወደ ከተማይቱ መግባቱ | ዮሐ 12:13-14, ማነ 21:1-11 |
| መዝ 41:9 | በባልንጀራው መከዳቱ | ማር 14:10 ማቴ 26:14-16 |
| ዘካ 11:12 | በሠላሳ ብር መሸጡ | ማቴ 26:15, ማቴ 27:3-10 |
| ዘካ 11:13 | ገንዘቡ ለሸክላ ሠሪ መሬት እንደተሰጠ | ማቴ 27:6-10 |
| መዝ 109:7-8 | የይሁዳ ሥፍራ በሌላ መተካቱ | ሐዋ 1:18-20 |
| መዝ 27:12, 35:11 | የሐሰት ምስክሮች | ማቴ 26:60-61 |
| ኢሳ 53:7 | ሲከሱት ዝም ማለቱ | ማቴ 26:62-63, ማቴ 27:12-14 |
| ኢሳ 50:6 | መመታቱና መትፋታቸው | ማር 14:65, 15:17, ዮሐ 191-3 |
| መዝ 69:4, 109:3-5 | ያለምክንያት መጠላቱ | ዮሐ 15:23-25 |
| ኢሳ 53:4-5, 6,12 | ታላቅ መከራን መቀበሉ | ማቴ8:16-17, ማቴ 27, ማር 14, |

| | | |
|---|---|---|
| ኢሳ 53:12 | ከኃጢአተኞች ጋር መሰቀሉ | ማቴ 27:38 |
| መዝ 22:16 | እጁና እግሩ መቸንከሩ | ዮሐ 20:27, ዮሐ 19:37 |
| መዝ 22:6-8 | እንደሚላገዱበት | ማቴ 27:39-40 |
| መዝ 69:21 | ሐሞትና የወይን ጠጅ እንደሚቀምስ | ዮሐ 19:29, ማቴ 27:34, 48 |
| መዝ 22:8 | የሚላገዱበት ቃል | ማቴ 27:43 |
| መዝ 109:4 | ለጠላቶቹ እንደሚጸልይ | ሉቃ 23:34 |
| ዘካ 12:10 | ጐኑ በጦር እንደሚወጋ | ዮሐ 19:34 |
| መዝ 22:18 | በልብሱ ላይ እጣ እንደሚጣጣሉ | ማር 15:24 |
| መዝ 34:20 | አጥንቱ እንደማይሰበር | ዮሐ 19:33 |
| ኢሳ 53:9 | ከባለጠጐች ጋር በመቃብሩ እንደሚሆን | ማቴ 27:57-60 |
| መዝ 16:10 | ትንሣኤው | ማቴ 28:9, ሉቃ 24:36 |
| መዝ 68:18 | እርገቱ | ሉቃ 24:50-51, ሐዋ 1:9 |

## <u>የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ የምድር ሕይወት ዘመን ግምት</u>

ልደቱ በ4 ወይም 5 ቅ.ክ.
ወደ ግብጽ ሽሽት በ4 ወይም በ5 ቅ.ክ.
ከግብጽ መልስ ከ3 ወይመ በ4 ቅ.ክ.
በልጅነቱ ቤተመቅደስ የሄደበት ጊዜ ምናልባት በ8 ዓ.ም.
የዮሐንስ መጥምቁ አገልግሎት የተጀመረበት ጊዜ ምናልባት በ26 ዓ.ም.
ኢየሱስ በዮሐንስ የተጠመቀበት ጊዜ ምናልባት በ26 ዓ.ም.
ጌታ ኢየሱስ አገልግሎት የጀመረበት ጊዜ ምናልባት በ26 ዓ.ም.
የጌታ ኢየሱስ ዝናው የወጣበት ጊዜ ምናልባት በ27 ዓ.ም.
ተቃውሞ እየበረታበት የመጣበት ጊዜ ምናልባት በ28 ዓ.ም.
ሞቱና ትንሣኤው ምናልባት በ29 ወይም በ30 ዓ.ም. የመጀመርያው ወር

☞ *ዳዊት ፋሲል*
ስ.ቁ. 0917804407
ፖ.ሣ.ቁ. 67 ጅማ
E-mail – besodiyah@gmail.com ወይም
niguye2004@yahoo.com

# አማኝ ጌታ ኢየሱስን የግል አዳኝ አድርጎ በተቀበለበት ወቅት በእግዚአብሔር ዘንድ የተፈጸሙለት መንፈሳዊ ነገሮች

# Irrevocable Absolutes God Provides Every Believer at the Moment of Salvation

*በዳዊት ፋሲል የተዘጋጀ* *2002/ ጅማ*

1. **በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ ውስጥ ተካትቷል።**
   1.1 አስቀድሞ ታውቋል። (ሮሜ 8፡29, 1ጴጥ 1፡2)
   1.2 አስቀድሞ ተወስኗል። (ሮሜ 8፡29-30, ኤፌ 1፡5-11)
   1.3 አስቀድሞ ተመርጧል። (ሮሜ 8፡33, 1ተሰ 1፡4, ቲቶ 1፡1, 1ጴጥ1፡2)
   1.4 በእግዚአብሔር ተጠርቷል። (ሮሜ 8፡30, 1ቆሮ 1፡9,1ተሰ 5፡24,)
2. **ከእግዚአብሔር ጋር ታርቋል። (The Reconciled)**
   2.1 በእግዚአብሔር የማስታረቅ አሠራር (2ቆሮ 5፡18-19, ቈላ 1፡20)
   2.2 ከእግዚአብሔር ጋር (ሮሜ 5፡10, 2ቆሮ 5፡20, ኤፌ 2፡14-17)
3. **ቤዛ አግኝቷል ከዚህም የተነሣ ተዋጅቷል። (The Redeemed)**

(ሮሜ 3፡24, ቈላ1:14, 1ጴጥ 1፡18)

- **ቤዛ፡-** *ማለት "ምትክ፣ ክፍያ ፣ለማዳን ራስን አሳልፎ መስጠት" ማለት ነው። በመሆኑም አማኝ በእርሱ ፈንታ የኃጢአቱን ቅጣት የተቀበለለትን ቤዛ (ክርስቶስን) አግኝቷል። ጌታ ኢየሱስ ደግሞ የአማኙ ፍርድ ይቀርለት ዘንድ ለእርሱ ምትክ (ቤዛ) ሆኖለታል።* (1ጢሞ 2፡5-6)
- ***መዋጀት፦*** **ሲላላ** *"አንድን ነገር ካለበት ሁኔታ ዋጋ ከፍሎ ነፃ ማውጣት ሲሆን"* **ሲጠብቅ** *"ካሉበት ሁኔታ በተከፈለው ዋጋ ምክንያት ነፃ መውጣት ማለት ነው። ኢየሱስ ቤዛ አድርጐ ራሱን በመስጠት እንዲሁም በደሙ ዋጋ አማኙን በመዋጀት ከኃጢአት ባርነትና ከዘላለም ፍርድ ነፃ አውጥቶታል።* (ሐዋ 20፡28)

4. **ኩነኔ ፈጽሞ የለበትም (የሕግ እርግማንና፣ ሞት ስለማያገኘው)።**

(ሮሜ 8፡1, ዮሐ 3፡18, 5፡24, *ገላ 3፡13*)

5. **ኃጢአቱ በሙሉ ወደ ኢየሱስ ተሻግሮለታል።**

- *ጌታ ኢየሱስ ፈጽሞ ንጹህና ኃጢአት ከቶም የማያውቀው ነው። ነገር ግን እርሱን ለሞት ያበቃው በዓለም ላይ ያለውን የእያንዳንዱን ሰው ኃጢአት ለመሸከም በመፍቀዱ ነበር። በዚህም ምክንያት የእርሱ ሞት "በምትክነት መሞት"* /Substitutionary death/ *ይባላል።*

(ኢሳ 53፡6, ሮሜ 4፡25, *2ቆሮ 5፡21*, ገላ 3፡13, 1ጴጥ 2፡24)

6. **ኃጢአቱ በእግዚአብሔር ችሎታ ተሰርዮለታል:: (Propitiation of sins)**

❖ *ይህም እግዚአብሔር ልጁ በመስቀል ላይ በሰራው የማዳን ሥራ ስለረካ እና በዚህም ምክንያት በልጁ የሚያምኑትን ሁሉ ይቅር በማለቱ የተገኘ ነው::*

(ሮሜ 3፡25-26, 1ዮሐ 2፡2, 4፡10)

7. **ለአሮጌው ሕይወት ሞቷል፣ ለእግዚአብሔር ሕያው ሆኗል::** (Positional change)

7.1 ከክርስቶስ ጋር ተሰቅሏል:: (ሮሜ 6፡6, ገላ 2፡20)

7.2 ከክርስቶስ ጋር ሞቷል:: (ሮሜ 6፡8, ቈላ 3፡3, 1ጴጥ 2፡24)

7.3 ከክርስቶስ ጋር ተቀብሯል:: (ሮሜ 6፡4, ቈላ 2፡12)

7.4 ከክርስቶስ ጋር ተነስቷል:: (ሮሜ 6፡4,7፡4, ቈላ 2፡12, 3፡1)

7.5 ከክርስቶስ ጋር በቀኙ ተቀምጧል:: (ኤፌ 2፡7)

8. **ከሙሴ ሕግ ተጠያቂነትና ፍርድ ነፃ ወጥቷል::**

❖ *አማኙን ከሕግ፣ ተጠያቂነት ነፃ ለማውጣት በእግዚአብሔር የተፈፀመው የምስጢር አሠራር "አማኙን በክርስቶስ የሥጋ ሞት አብሮ እንዲገደል ማድረግ ሲሆን ከዚህም የተነሣ በሞተ ሰው ላይ ሕግ ተፈፃሚነት እንደሌለው ሁሉ አማኙም ከሕግ ባርነት እና ተጠያቂነት ነፃ ወጥቷል አርነት አግኝቷል::*

8.1 ለሕግ ተገድሏል:: (ሮሜ  7፡1-6)

8.2 ሕግ አይገዛውም:: (ሮሜ  7፡6, 6፡14, 2ቆሮ 3፡6-11, ገላ 3፡25)

8.3 በሕግ ሳይሆን በመንፈስ ይመራል:: (ሮሜ 8፡1-4, 8፡14-17)

9. **ከእግዚአብሔር ዳግመኛ (ድጋሚ) ተወልዷል:: (ዮሐ 3፡1-8, ዮሐ 1፡12, ቲቶ 3፡5)**

9.1 በእውነት ቃል (ወንጌል) ተወልዷል:: (ያዕ 1፡18, 1ጴጥ 1፡23)

9.2 ልጅ ሆኗል:: (A child of God) (ሮሜ 8፡16, ገላ 3፡26)

9.3 ልጅ ሆኗል:: (Sons & daughters of God) (ዮሐ 1፡12, 2ቆሮ 6፡18, 1ዮሐ 3፡2)

9.4 አዲስ ፍጥረት ሆኗል:: (2ቆሮ 5፡17, ገላ 6፡15, ኤፌ 2፡10)

10. **የሥጋ ቤዛነትን (በትንሣኤ አካል የሚሆን ልጅነትንም) ወደ ፊት ያገኛል::**

**(ሮሜ 1፡3, 8፡23)**

❖ *ያን ጊዜ እንደመልአክ ይሆናል እንጂ፣ በሥጋ ባህርይ አይገለጥም::* (ማር 12፡24)

**11.በእግዚአብሔር ፊት ሙሉ ተቀባይነትን አግኝቷል።**

11.1 ጸድቋል (ሮሜ 3፡22, 1ቆሮ1፡30, 2ቆሮ5፡21, ፊል 3፡9)

11.2 ተቀድሷል (በእግዚአብሔር ፊት) 1ቆሮ 1፡30, 6፡11)

11.3 ለዘላለም ፍጹም ሆኗል (perfected forever) (ዕብ 10፡14)

11.4 በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ርስት ተካፍሏል። (ቈላ 1፡12, ኤፌ 1፡11)

**12. ጻድቅ ሆኗል (ሮሜ 3፡24/5፡1, 9/ 8፡30, 1ቆሮ 6፡11, ቲቶ 3፡7)**

- ❖ ይህም አማኙ ጸጋውን በእምነት በመቀበሉ ያገኘው እንጂ በራሱ ብቃት ያገኘው አይደለም፣ በራሱ ማንነት ጻድቅ የሆነ ፈፅሞ የለምና። (ሮሜ 3፡11-31)

**13.ከመለኮት ባህርይ ተካፋይ ሆኗል። (1ጴጥ 1፡3)**

- ❖ ይህም ዳግመኛ ከእግዚአብሔር በመወለዱ ምክንያት የተካፈለው ባህርይ ነው። ምክንያቱም በአማኙ ውስጥ የእግዚአብሔር ዘር ስላለበት እርሱን መምሰል ይለማመዳል። (ዮሐ 3፡9, 2ጴጥ 1፡6, 1ጢሞ 6፡6)

**14. ሙሉ ሰማያዊ ዜግነትን አግኝቷል።**

14.1 ለሰማያዊው ጥሪ (ወንጌል) አዎንታዊ ምላሽ ስጥቶአል። (ዕብ 3፡1)

14.2 ስሙ በሰማይ ነዋሪዎች መዝገብ (የሕይወት መጽሐፍ) ላይ ተጽፏል። (ሉቃ10፡20)

14.3 የሰማያዊው ቤተሰብ አባል ነው ።(ኤፌ 2፡14-19)

14.4 አገሩ በሰማይ ነው። (ፊል 3፡20, ዕብ 11፡14-16, ዮሐ 14፡1-3)

**15. ከጨለማ ሥልጣን ነፃ ሆኗል። (ቈላ 1፡13, 2፡15)**

- ❖ ምክንያቱም ኢየሱስ የሕይወት ብርሃን ሆኖለታል። (ዮሐ 8፡12)
- ❖ ጨለማ በሰይጣን መንግሥት ውስጥ ያለ ማንኛውም አሠራር ነው።

<u>ለምሳሌ</u>፦ የሰዎች ክፉ ሥራ፣ የኃጢያት ልምምድ (ዮሐ 3፡19-21)

- ያለተስፋ ከኢየሱስ ውጭ መኖር (ማቴ 4፡12-16)
- ያለዕውቀት መኖር (ሮሜ 2፡20)
- ለእግዚአብሔር ክብር የማይሰጥ ሕይወት። (ሮሜ 1፡20-22)
- ወንጌልን አለመቀበል (2ቆሮ 4፡4-6 ዮሐ 12፡35-36) ወዘተ...

**16. ወደ እግዚአብሔር ልጅ የብርሃን መንግሥት ፈልሷል:: (ቈላ 1፡13)**

16.1 ጌታ ኢየሱስ ለሕይወቱ ብርሃን ሆኖለታል:: (ዮሐ 8፡12)

16.2 ጌታ እግዚአብሔር ብርሃናዊ አባት ሆኖለታል::(ያዕ 1፡16-17)

✓ ስለዚህ ማንኛውንም በጎ ሥጦታና ፍፁም በረከት ከእግዚአብሔር መቀበል ይችላል::

16.3 የእግዚአብሔር ቃል ብርሃን ሆኖ ይመራዋል:: (መዝ 119፡105)

16.4 አማኙ ራሱ የዓለም ብርሃን ሆኗል:: (ኤፌ 5፡8, ማቴ 5፡14)

**17. በፀና መሠረት ላይ ታንጿል:: (1ቆሮ 3፡11፣ 10፡4, ኤፌ 2፡20)**

**18. ከእግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ በስጦታነት ተሰጥቷል::**

(ዮሐ 10፡29, 17፡2, 6, 9, 11,12, 24)

**19. ከኃጢአት ኃይል ነፃ ወጥቷል (ሮሜ 8፡2፣ ፊል 3፡3, ቈላ 2፡11)**

<u>መገረዝ</u>፦ ከኃጢአት ኃይል ነፃ የመውጣት ምሳሌ ሲሆን በውሃ ጥምቀት ይገለፃል::

**20. የእግዚአብሔር እና የክርስቶስ ካህን ሆኗል::**

20.1 ካህን የተደረገው በክርስቶስ ደም ነው:: (ራዕ 1፡6, 5፡9)

20.2 ቅዱስ ካህን ሆኗል:: (መጸለይ፣ ማምለክ ይችላል) (1ጴጥ 2፡5)

20.3 የንጉሥ ካህን ሆኗል:: (ለሰዎች መመስከር ይችላል) (1ጴጥ 2፡9)

**21. የዘላለም ሕይወት ዋስትና (Eternal security) ተሰጥቶታል::**

(ዮሐ 10፡28-29, ሮሜ 8፡32, 5፡8-11, ሮሜ 8፡38-39, ገላ 3፡26-29)

✓ ከእርሱ የሚጠበቀው በዚህ እምነት መጽናት ብቻ ነው:: (ቈላ 1፡21-23, 2ጢሞ 2፡11)

**22. በፈለገው ጊዜ ሁሉ ወደ እግዚአብሔር መግባት ተፈቅዶለታል::**

(ሮሜ 5፡2, ኤፌ2፡18, ዕብ4፡16,10፡19-20)

**23. የተትረፈረፈ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጸጋና በጐነት መገለጫ ነው::**

23.1 የእግዚአብሔር የፍቅሩ መገለጫ ነው:: (ዮሐ 13፡1, ኤፌ 2፡4, 5፡2)

23.2 የእግዚአብሔር የጸጋው መገለጫ ነው::

23.2.1 በጸጋው ድኗል:: (ኤፌ 2፡8-9)

23.2.2 በጸጋው ጸንቶ ይቆማል፣ ይጠበቃል ( ሮሜ 5፡2, 1ጴጥ 2፡9)

23.2.3 በጸጋው ያገለግላል :: (ኤፌ 4፡7፣1ቆሮ 12፡4-11,1ጴጥ 4፡10-11)

23.2.4 በጸጋው ቅድስናን ይለማመዳል (ቲቶ 2፡11-5)

23.3 የእግዚአብሔር የኃይሉ መገለጫ ነው።

(ኤፌ 1፡19, 2፡6-7, 2ቆሮ 10፡10-11, 13፡2-5 ፊል 2፡13)

23.4 የእግዚአብሔር የታማኝነቱ መገለጫ ነው (ፊል 1-6, ዕብ 13፡5, 10፡23)

23.5 የእግዚአብሔር ሰላም መገለጫ ነው ። (ዮሐ 14፡27)

23.6 የእግዚአብሔር ማጽናናት መገለጫ ነው። (2ተሰ 2፡16)

23.7 በሊቀካህናቱ በኢየሱስ ምልጃ ተጠቃሚ ነው። (ሮሜ 8፡34, ዕብ 7፡25, 9፡24)

- ✓ ከላይ የተዘረዘሩትን ነገሮች እግዚአብሔር የሚገልፀው በአማኝ ሕይወት ውስጥ ሲሆን ያልዳኑ ሰዎች ግን የዚህ ሁሉ ጸጋና በጎነት ተጠቃሚ ለመሆን በመጀመሪያ በክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ አለባቸው። (2ቆሮ 5፡18-20, ዕብ 7፡25)

## 24. ከክርስቶስ ጋር አብሮ የእግዚአብሔር ወራሽ ነው።

(ሮሜ 8፡17, ኤፌ 1፡14, 18, ቈላ 3፡24, ዕብ 9፡15, 1ጴጥ 1፡4)

- ✓ ጌታ ኢየሱስ ዓለም ሳይፈጠር በፊት የነበረውን ክብር ሊያወርሰን ስለኛ ወደ አባቱ የጸለየው ፀሎት ለአማኙ የመውረስ መብት አሰጥቶታል። (ዮሐ 17፡24)

## 25. በክርስቶስ የማንነት ሥፍራ ለውጥ ተደርጎለታል። (Positional truth)

25.1 ሕይወቱ በእግዚአብሔር ዘንድ በክርስቶስ ውስጥ ተሰውሯል።(ቈላ 3፡4)

25.2 ከልጁ ጋር ሕብረት ፈጥሯል። (1ቆሮ 1፡9)

25.3 ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ የሚሠራ ሆኗል። (1ቆሮ 3፡9,2ቆሮ 6፡1)

25.4 የአዲስ ኪዳን አገልጋይ ሆኗል። (2ቆሮ 3፡6)

25.5 መልእክተኛ (Ambassador) ነው። (2ቆሮ 5፡20)

25.6 ሕያው መልእክት (The living Epistle ) ሆኗል። (2ቆሮ 3፡3)

25.7 የእግዚአብሔር አገልጋይ ነው። (2ቆሮ 6፡4)

## 26. የዘላለም ሕይወት አግኝቷል።

(ዮሐ 3፡15, 10፡28, 20፡31, ሮሜ 8፡1,ኤፌ 2፡8 , 1ዮሐ 5፡11-12)

27. አዲስ ፍጥረት ሆኗል።

- ከእግዚአብሔር የተወለደ (ዮሐ 1፡12), ከሥጋና ደም ፈቃድ ያልተወለደ (ዮሐ 1፡13)
- ዜግነቱ ሰማያዊ የሆነ (ፊል 3፡20) ግሪካዊ መሆን ያልቻለ (ቈላ 3፡11)
- ከምድራዊ ነገድ፣ ቋንቋ፣ ሕዝብ፣ ወገን እርግማን ነፃ የወጣ (ራዕ 5፡9-10)
- በምድር ላይ አገር የሌለው (ዕብ 13፡14)፣
- በምድር ለሚኖሩ የተላከ መልዕክተኛ (2ቆሮ 5፡20) ሆኗል።

*ማስታወሻ፦ ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ የዓለም ሕዝቦች በሁለት ወገን ይከፈሉ ነበር። አይሁድና አህዛብ። አህዛብ የሚባሉት ከእሥራኤል ውጭ ያሉት አብዛኛው የዓለም ሕዝቦች በመሆናቸው መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉንም ግሪክ በሚለው ስም ጠቅልሏቸዋል። በመሆኑም በሥጋ የአብርሃም ዘር ከሆኑት ከእሥራኤል ውጭ ያለው ሌላው አንባቢ ሁልጊዜም "ግሪክ" እርሱ የተላከበትን የአህዛብን ምድር እንደሚወክል ማወቁ ተገቢ ነው።*

28. በጌታ የዓለም ብርሃን ሆኗል።

28.1 ከጨለማ ሥራ ጋር አይተባበርም ይልቁንም የእርሱ ብርሃንነት ክፉሥራን፣ ጨለማን ሁሉ ይገልጣል። (ኤፌ 5፡7-13) ከብርሃን ኃይላት (መላእክት) ጋር በመተባበር ከሰይጣንና አጋንንቱ ጋር የሚዋጋ በጎ ወታደር ሆኗል።
(Part of Angelic conflict) (2ጢሞ 2፡3, ኤፌ 6፡10-18)

28.2 በመልካም ሥራ ሁሉ ይገለጣል።(ማቴ 5፡14)

28.3 የጌታ ቀን በእርሱ ላይ እንደ ሌባ አይመጣም። (1ተሰ 5፡4-5)

- የአማኝ የተባረከ ተስፋው የጌታ መምጣት ነው። (ቲቶ 2፡12) በመሆኑም የጌታን መምጣት እጅግ ከመጠን ባለፈ ይናፍቃል። (ራዕ 22፡20) እንጂ ስለዚያ ቀን ፍርሃት ፈፅሞ የለበትም። ያ ቀን ለአማኙ የማይነገር ሐሴት ማድረጊያ (ዮሐ 16፡22)፣ የጽድቅ አክሊል መቀበያ (2ጢሞ 4፡8)፣ የሠርግ (ራዕ 19፡7-8) ፣ የንግሥና (ራዕ 20፡6) ጊዜው ነው።

29. ከተስፋው ቃል ከመንፈስ ቅዱስ ተካፋይ ሆኗል።

29.1 ከመንፈስ ቅዱስ ተወልዷል። (ዮሐ 3፡5-8)

29.2 በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቋል። (ሐዋ 1፡5, 1ቆሮ 12፡13)

29.3 የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ (መቅደስ) ነው
(ዮሐ 7፡39, ሮሜ 5፡5,8፡9, 1ቆሮ3፡16, 6፡19, ገላ 4፡6, 1ዮሐ 3፡24)

29.4 በመንፈስ ቅዱስ ታትሟል። (2ቆሮ 1፡22, ኤፌ 4፡30)

29.5 በመንፈስ ቅዱስ ተቀብቷል። (1ዮሐ 2፡20, 27)

29.6 የጸጋ ስጦታ (ልዕለተፈጥሯዊ ስጦታዎች) ተሰጥተውታል።
(1ቆሮ 12፡11, 27-11 13፡1-2)

30. **በእግዚአብሔር ፊት ከብሯል:: (Glorified) (ሮሜ 8፡30)**

31. **በክርስቶስ ሙሉ፣ ፍፁም እና በእግዚአብሔር ፊት እንከን አልባ ሆኗል::**
(Complete- KJV, Perfect-NIV, full-NIV, blameless-NIV)
(ኤፌ 1፡4, ቆላ 2፡10, ዕብ 10፡14)

32. **በመንፈሣዊ በረከቶች ሁሉ ተባርኳል:: (ኤፌ 1፡3)**

33. **ኃጢአቱ በሙሉ ይቅር ተብሎለታል:: (ሮሜ 4፡6-8, ዕብ 10፡14-18)**

34. **በጠላት (በሰይጣን) ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ተሰጥቶታል::**
    34.1 እባቡን (የሰይጣንን የተንኰል እና የስህተት አሠራር) እና ጊንጡን (ሰይጣን በሰው አካላዊ ማንነት ላይ የሚያደርሰውን ጥቃት) መርገጥ (መቆጣጠር ማሸነፍ) ይችላል:: (ሉቃ 10፡17-19)
    34.2 በኢየሱስ ስም አጋንንትን ከሰዎች ውስጥ ያወጣል:: (ማር 16፡17)
    34.3 በበሽተኞች ላይ እጁን ይጭናል እነርሱም በጌታ ፈቃድ ይፈወሳሉ:: (ማር16፡18, ያዕ 5፡14)
    34.4 ለሰዎች ሁለንተናዊ ስኬት ይጸልያል:: (3ዮሐ 2)

35. **መንፈሱ ሕያው ሆኗል::**
   - ❖ አዳም ትዕዛዝ በተላለፈበት ወቅት ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን መንፈሳዊ ሕብረት አጣ:: ይህም የሕብረት መቋረጥ <u>የመንፈስ መሞት ይባላል</u>:: የሰው ልጆች ሁሉ ኃጢአት በማድረጋቸው መንፈስ ከሆነው ከእግዚአብሔር ጋር ሙሉ ሕብረት ማድረግ አልቻሉም ነበር:: ሰው ጌታን ኢየሱስን የግል አዳኝ አድርጎ ሲቀበል ተቋርጦ የነበረው የመንፈስ ሕብረት መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ውስጥ በመግባቱ የተነሳ ይቀጥላል:: ያን ጊዜ የሰው መንፈስ መንፈስ ከሆነው ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ያደርጋል:: ይህም "<u>የሰው መንፈስ ሕያው መሆን</u>" ይባላል:: (ዮሐ 5፡25, ሮሜ 8፡16)

    35.1 በመንፈሱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሕብረት ያደርጋል:: መንፈሱ መንፈስ ቅዱስን ማዳመጥ ይችላል:: (ሮሜ 8፡16, 1ቆሮ 2፡12)
    35.2 መንፈሱ ሕያው ከመሆኑ የተነሣ የእግዚአብሔር ሥራ ሲሠራ እረፍት ይሰማዋል:: (2ቆሮ 7፡13) እግዚአብሔር የሚጠላውን ነገር ሲያይ ደግሞ ይበሳጫል:: (ሐዋ 17፡16)

36. **በሕይወት ዘመኑ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ተፈቅዶለታል፤ ይሞላልም:: (ኤፌ 5፡18)**

37. **ከአባት ከልጁ እና ከቅዱስ መንፈሱ (ሥላሴ) ጋር ሕብረት አንድነት ፈጥሯል።**

37.1 ከእግዚአብሔር አባት ጋር (ዮሐ 14፡23, ኤፌ 4፡6)

37.2 ከክርስቶስ ጋር (ዮሐ 14፡20, ቈላ 1፡27)

37.2.1 የክርስቶስ አካል የቤተክርስቲያን ብልት (አባል) ሆኗል።(1ቆሮ 12፡13)

37.2.2 የግንዱ፣ የክርስቶስ ቅርንጫፍ ሆኗል። (ዮሐ 15፡5, ሮሜ 11፡17-20)

37.2.3 በሕያው ሕንፃ፣ ጉባኤ ውስጥ ሕያው ድንጋይ (አባል) ሆኗል። (ኤፌ 2፡21-22, 1ጴጥ 2፡5)

37.2.4 በመንጋው ውስጥ በግ ሆኗል። (ዮሐ 10፡27-29)

37.2.5 የሙሽራዪቱ ክፍል ሆኗል። (ኤፌ 5፡25-27, ራዕ 19፡6-8, 21-9)

37.2.6 በመንግሥቱ ውስጥ ካህን ሆኗል። (1ጴጥ 2፡9, ራዕ 1፡6, 5፡9)

37.3 ከመንፈስ ቅዱስ ጋር (ሮሜ 8፡9, ዮሐ 14፡16, 7፡37-39)

38. **የፊተኛው ትንሣኤ አካል ዋስትና ተሰጥቶታል።**

(1ቆሮ 15፡ 40-54, ዮሐ 11፡25, 6፡39, 1ቆሮ 15፡23, ራዕ 20፡56)

**ከአዘጋጁ መልዕክት፡-**

"አግሪጳም ጳውሎስን፡- "እንዲህ በቀላሉ ክርስቲያን የምታደርገኝ ይመስልሃልን?" አለው። ጳውሎስም፡- "በቀላሉም ሆነ በብዙ፣ አንተ ብቻ ሳትሆን ዛሬ የሚሰሙኝ ሁሉ፣ ከዚህ ከታሰርኩበት ሰንሰለት በስተቀር፣ እንደእኔ (ክርስቲያን) ይሆኑ ዘንድ እግዚአብሔርን እለምናለሁ።" አለ

*ሐዋ 26፡28 (አ.መ.ት.)*

**ዳዊት ፋሲል**

**ስ.ቁ. 0917804407**

***ፖ.ሣ.ቁ. 67 ጅማ***

**E-mail – niguye2004@yahoo.com**